5 ትእግስት
የፅናት ፍሬ

ትምህርት

ፈውስን፣ እርኒትን፣ ምሪትን፣ መሠልጠንና ይህን የመሳሰሉትን ነገሮች በትእግስት መጠበቅ ቀላል ነገር አይደለም። ነገሮቻችን ወደፊት ሳይሆን አሁኑኑ እንዲከናወኑልን እንፈልጋለን። አንድ ነገር እንዲሆንልን በምንጠብቅበት ጊዜ ወይም የምንጠብቀው ሰው እንዲደርስልን በፈለግን ጊዜ ስዓቱ በጣም የሚነተት ይመስለናል። ነገር ግን መልካም ነገሮች ትእግስት የሚጠይቁ ይመስላሉ። አንድ ሰው ህኪም ለመባል ስባት ወይም ክዚያ የበለጡ ዓመታት በትዕግሥት መማር አለበት። ወላጆች ልጆቻቸውን በተደጋጋሚ አንድ ትምህርት እስኪገባቸው ድረስ ማስተማር ይኖርባቸዋል። ብዙዎቻችን ለእኛ ጠቃሚ የሆነውን ነገር ለማግኘት ለረጅም ጊዜ በትጋት እየሰራን ገንዘብ እናጠራቅማለን። በመንፈስ የተሞላ ክርስቲያን ሰሀይወቱ ክርስቶስን የመምሰል ባህርይ እንዲኖረው ከፈለገ የትእግስትን ምስጢር መማር ይኖርበታል።

ስዎች ብዙ ጊዜ ስለ ኢዮብ ስላም ሲናገሩ ይስማሉ። ኢዮብ እስኪፈወስ እና ቤተሰቡ እና ንብረቶቹ እስኪመለሰለት ድረስ ጌታን በትእግስት ጠብቋል። ሙሴ ለጌታ የሚጠቅም እገልጋይ ከመሆኑ በፊት ለ40 ዓ መታት በትእግስት ትምህርት ቤት አሳልፏል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ሲል ይመክረናል። "ታገሱ፣ ልባችሁንም አፅኑ የጌታ መምጣት ቀርቧልና" (ያዕ 5:8)። በውስጣችን የስላም ማደሪ ክርስቶስን የመምሰል እንደኛው ጠቃሚ ክፍል ነው (2ጴጥ 1:5-8ን ተመልከት)።

ይህ ትምህርት የትእግስትን ጠቃሚነት እንድትመለከትና መንፈስ ቅዱስም ፍሬውን ሰውስጥህ እንዲያፈራ የምትተባበርበትን መንገድ ያሳይሃል። ትእግስት የፅናት ውጤት ነው። በእምነት መፅናት፣ መቆየትና እግዚአብሔርን መጠበቅ ነው።

የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል
- የትእግስት ምንነት
- ትእግስት ሲገለፅ
- ትእግስት በምሳሌ

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህንን ትምህርት ባጠናቀቅክ ጊዜ የሚከተሉትን ማድረግ መቻል ይኖርብሃል።

- የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሆነውን የትእግስትን ሁስት አቅጣጫዎች መግለጽና ለእያንዳንዱ አቅጣጫ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎች መስጠት።
- እግዚአብሔር ለሰዎች የሚያሳየውን የትእግስት ምሳሌዎች በመግለፅ ለታላቁ ትዕግስቱ ምክንያቱን ማብራራት።

- በመንፈሳዊ ሕይወትህ የምታየውን በትዕግሥትና ስሌሎች መንፈሳዊ ባህርያት መካከል ያለውን ዝምድና ማጤን።

የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. ያለፉትን ትምህርቶች ስታጠና በነበረበት መልክ ይህንንም ትምህርት አጥና። የትምህርቱን ዝርዝር እንብብ፣ የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎችን መልስ። ከመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱትን ጥቅሶችም እንብብ።
2. የሙከራ ፈተናውን ከስራህ በኋላ መልሶችህን አመሳክር።

የትምህርቱ ዝርዝር

የክርስቶስ ምሳሌነት

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጉም

ዓላማ 1 የመንፈስ ፍሬ የሆነውን የትእግስትን ገፅታዎች ምንነት ለመግለጽ።

"የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ስላም፣ ትዕግስት. . . ነው።" ገላ 5:22።

የመጀመርያዎቹ ሶስቱ የመንፈስ ፍሬ ዓይነቶች እንደ ፍቅር፣ ደስታ እና ስላም ያሉት አስፈላጊ የመንፈሳዊ ሕይወታችን የውስጥ ክፍሎች ናቸው። እነዚህም በልባችን የሚሆኑት እኛ ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግላዊ ግንኙነት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ ሲኖር ነው። ከትእግስት ጀምሮ ያሉት የሚቀጥሉት ሶስቱ የመንፈስ ፍሬዎች የፍቅር፣ የደስታና የስላም ውጪያዊ መገለጫዎች ናቸው፤ ከሰዎች ጋር ያለንን ግንኙነት ያሳያሉ።

ማክሮቶምያ (ማክሮስ ማለት ረጅም ሲሆን ቱሚያ ማለት ደግሞ ባህሪ ወይም ጠባይ ማለት ነው) የሚለው የመጀመርያው የግሪክ ቃል ትእግስት ተብሉ ተተርጉሟል። ይህ ቃል በትእግስት መዕናትንና መረጋጋት የሚለውን መስኮታዊ ሀሳብ ይዟል። በሌላ አባባል መንፈስ ቅዱስ ሰውበጡ የትእግስት ፍሬን እያፈራለት ያለ ሰው ተበፋ ሳይቆርጥ ጌታን የሚጠብቅ ወይም ቁጣ ሳይገዛው ጌታን መጠበቅ የተማረ ነው።

ትእግስት የመንፈስ ፍሬ እንደመሆኑ መጠን አማኝ ፈተና ስሚገጥመው ጊዜ ራሱን እንዲገዛ ያበችለዋል። ለመቅጣት ወይም ለመበቀል እይቸኩልም። እንዲሁም በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ እጅ አይሰጥም ወይም እይንበረከክም። ቀጥለን እንደምናየው ትእግስት በዚህ ገፅታው ከመከራ ጋር ይያያዛል። በመከራችን ውሰጥ ነው የትእግስት መንፈስ ወይም ዕናት በውስጣችን የሚያድገው። እነዚህ ሁሉ የትእግስት ገፅታዎች ክርስቶስን ወደ መምሰል የሚያደርሱን የእድገት ክፍሎች ናቸው። ይህም በ2ጴጥ 1:5-8 የተገለፀው ጉዳይ ነው።

ስለዚህም ምክንያት ትጋትን ሁሉ እያሳያችሁ በእምነታችሁ በጎነትን ጨምሩ፣ በበጎነትም እውቀትን በእውቀትም ራስን መግዛት፣ ራስን በመግዛትም መፅናትን፣ በመፅናትም እግዚአብሔርን መምሰል፣ እግዚአብሔርንም በመምሰል የወንድማማችን መዋደድ፣ በወንድማማች መዋደድም ፍቅርን ጨምሩ። እነዚህ ነገሮች ስለናንተ ሆነው ቢበዙ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እውቀት ስራ ፈቶችና ፍሬ ቢሶች እንዳትሆኑ ያደርጓችኋልና።

(1). ከላይ ከጠቀስነው በመነሳት በራስህ አባባል እነዚህን የትእግስት ገፅታዎች ወይም ምንነት ግለፅ።

ሀ. ጽናት
ለ. ቻይ ወይም የረጋ

መጽሐፍ ቅዱሳዊ አጠቃቀሙ

ዓላማ 2 የመንፈስ ፍሬ የሆነውን የትእግስትን ፍሬ ባህርያት የሚገልጽ ዐረፍተ ነገሮችን ለይቶ ለማወቅ።

በትእግስት እና በሌሎች የክርስትና ህይወት መገንዶች መካከል ጠንካራ የሆነ ግንኙነት አለ። ከመጽሐፍ ቅዱስ አባባል በመነሳት ጥቂቶቹን እንመለከታለን።

1. *ትእግስት እና መከራ።* ማንም ሰው ቢሆን በሕይወት ሲኖር መከራ ይገጥመዋል። ይህም እንዱ የመማሪያችን መንገድ ነው። ዘማሪው እንደሚለው፦ ስርዐትህን እማር ዘንድ ያስጨነቅከኝ ለመልካም ሆነልኝ (መዝ 119:71)። የክርስቲያን ፈተና በጎችን ከሚጠብቅ ውሻ ጋር ይመሳሰላል። በጎችን ከአረኛው አጠገብ ይጠብቃቸዋል። ፈተና ቅድስናውን እንድንካፈል የሚያደርግ ወዳጃችን የሆነው የሰማይ አባታችን ቅጣት መሆኑን ዕብ 12:7-11 ይገልፃል።

> "ለመቀጣት ታገሡ፣ እግዚአብሔር እንደልጆች ያደርግላችኋልና፣ አባቱ የማይቀጣው ልጅ ማነው? ነገር ግን ሁሉ የቅጣት ተካፋይ ሆኖአልና፣ ያስ ቅጣት ብትኖሩ ዲቃላዎች እንጂ ልጆች አይደላችሁም። ከዚህም በላይ የቀጡን የሥጋችን አባቶች ነበሩን እናፍራቸውም ነበር፤ እንዴትስ ይልቅ ስመናፍስት አባት አብልጠን ልንገዛና በህይወት ልንኖር ስተገባን? እርሱ ግን ከቅድስናው እንድንካፈል ስጥቅማችን ይቀጣናል። ቅጣት ሁሉ ለጊዜው የሚያሳዝን እንጂ ደስ የሚያሰኝ እይመስልም፣ ዳሩ ግን በኋላ ለለመዱት የሰላምን ፍሬ እርሱም ፅድቅን ያፈራላቸዋል"

በነፋስ ወደፊት እና ወደኋላ የሚወዛወዝ ስጋ አትከልት ጠንካራ እና ጥልቅ የሆነና ስር እየሰደደ ይሔዳል፤ በዚህ ህይወት ውስጥ ያለው ነፋስ ስክርስቲያን ስክርስቶስ ስር እንዲሰድና እንዲገዛ ያደርገዋል።

ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ከፍሎች እንደሚያሳዩን ክርስቶስን መከተል መስቀልም እስው። በ1ጴጥ 2:21 ሐዋርያው ሲፅፍ "የተጠራችሁስት

ስዚህ ነውና ክርስቶስ ደግሞ ፍስጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ አናንተ መከራን ተቀብሎአልና" ብሏል።

(2). ማቴ 10:38፣ ማቴ 16:24፣ ማር 8:34፣ ሉቃ 9:23 እና 14:27ን አንብብ። በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ የክርስቶስ መልእክት ምንድን ነው?

የምንኖረው ስመንፈሳዊ ነገር ጥላቻ ባለው ዓለም ውስጥ ስለሆነ ሁልጊዜ መሸነፍ የሚገባቸው ጠላቶች አሉ። ኢየሱስ ከውጭ አግዚአብሔርን በማያውቀው ጲላጦስ እጅና ቁጣን በተሞላው ህዝብ እጅ መከራን ተቀበለ። ከውስጥ ደግሞ በክዳተኛው ይሁዳ ምክንያት መከራን ተቀበለ። ትእግስትን ለመማር ከክርስቲያኖች ህብረት ውስጥ ብንፈተን ወይም በዓለም ባለው መከራ ብንፈተን ኢየሱስ ምሳሌያችን ነው። በሰይጣን በተፈተነ ጊዜ ከመስቀል ውጭ የቀረበለትን የዙፋን ጥያቄ ውድቅ አደረገ (ማቴ 4:1-11)። እንደዚያም ከፊቱ ያለውን መከራ ቢያስብም መከራን ሳስመቀበል ወደኋላ አላለም (ዮሐ 16:17-33)።

(3). ከታች የተጠቀሱትን እያንዳንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን አንብብና እያንዳንዱ ምንባብ ስስ ትእግስትና መከራ ስስ ሽልማቱም ምን እንደሚል ግለፅ።

ሀ. ሮሜ 5:3-4
ለ. ያዕ 1:3-4
ሐ. ያዕ 5:10-11
መ. 1ጴጥ 2:20

የኤሽላዋ ቅድስት ቴሬሳ በአስራ ስድስተኛው ከፍለ ዘመን የነበረች የስፔይን ክርስቲያን ናት። ህይወቷም በመከራ የነበረ የትእግስት ምሳሌ ነው። ወጣት በነበረችበት ጊዜ ለሞት በሚያበቃት ህመም ተመታች፤ እናም ብርቱ የልብ ችግር እና ሽባነት ስለደረሰባት ለሶስት አመታት ሽባ ነበረች። ቀስ በቀስም እጆቿን እና እግሮቿን መጠቀምና እየዳኸችም መንቀሳቀስ ጀመረች። ይህች ቤት ስለ መከራዋ ስትናገር "በዚህ ሁኔታ ስዘለአለም ቢተወኝም እንኳ ስእግዚአብሔር ፈቃድ እገዛለሁ" ብላለች። ከመሞቷ በፊት በዓፈችው በመጨረሻው ደብዳቤዋ እንዲህ ብላ ነበር። "አ ነፍሴ ያገኘችውን ለሳም እና ፀጥታ በትከከል መግለፅ እችላለሁ፤ እንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ውስጣዊ ምኞት ሳይስማኝ እንደፈተን ቢፈቅድም ፈቃዴ ግን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ፈቀቅ አላስም።" በደብዳቤዋ ላይም ፊርማዋን ስታኖር አሁን በታሪክ በምትታወቅበት መጠሪያ ሳይሆን "የክርስቶስ ቴርሳ" በማስት ነበር።

2. *ትእግስት እና ፅናት።* ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች ትእግስት እና ፅናት የተባሉትን ቃላት እየለዋወጡ ይጠቀሙበታል። ፅናት የሚናገረው ምንም ይሁን ምን ላመንክበት ነገር መቆምን ነው። አንድ ሰው እንደተናገረው ማክሮቶሚያ ስመከራ ውስጥ እንኳን በትእግስት የሚጠብቅ ፍቅር ነው። ቆሳ 1:9-11 እንዴት በትእግስት መፅናት እንዳስብን ይነግረናል።

> ስለዚህ እኛ ደግሞ ይህን ከስማንስት ቀን ጀምረን የፈቃዱ እውቀት መንፈሳዊ ጥበብንና አእምሮን ሁሉ እንዲሞሳባችሁ

እየለመንን ስለ እናንተ ፀሎትን እልተውንም። በበጎ ስራ ሁሉ ፍሬ እያፈራችሁ በእግዚአብሔር እውቀት እያደጋችሁ ከደስታ ጋርም ሁሉ ለመጽናት ለመታገስ እንደ ክብሩ ኀይል በሀይል ሁሉ እየበረታችሁ፣ በቅዱሳንም ርስት በብርሃን እንድንካፈል ያበቃንን አብን እያመሰገናችሁ በነገር ሁሉ ደስ ልታሰኙ ለጌታ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እንለምናለን።

3. *ትእግስት፣ ደስታ እና ተስፋ።* በሮሜ 5፥3-4 መከራ፣ ደስታ፣ ትእግስት እና ተስፋ በእንድ ላይ ተመድበው እናያለን። "መከራ ትእግስትን እንዲያደርግ ፣ትእግስትም ፈተናን ፈተናም ተስፋን እንዲያደርግ እያወቅን በመከራችን ደግሞ እንመካለን።" እነዚህ ጥቅሶች ክርስቲያን በእድገት ወይም በብስለት ውስጥ ስትእግስት ሊያልፍ ወደ ተስፋ እንደሚያመራ ያሳዩናል። ነገሮቻችን የሚከናወኑልን ሲመስለን ተስፋ ማድረግና መጠበቅ እያስቸግረንም ነገር ግን መከራችንን የሚያቃልልን ነገር ሲጠፋ ተስፋ መቁረጥና ማዘን የተለመደ ተፈጥሮአዊ ሁኔታ ነው። ትእግስት የመንፈስ ፍሬ እንደመሆኑ ሐዘንተኛ ወይም በጭፍን እንዲሁ ሁኔታዎችን የሚቀበል እየደሰም፣ ነገር ግን የዚህ ተቃራኒ ነው። በደስታ ተሞልቶ በሕይወታችን ውስጥ የሚሰራውን ጌታን በመተማመን መጠበቅና ከዘማሪው ጋር እንዲህ ማለት ነው።

"አቤቱ እኔ ግን በአንተ ታመንሁ እንተ እምላኬ ነህ አልሁ ርስቴ በእጅህ ነው" (መዝ 31፥14-15)።

4. *ትእግስት እና ጥበብ።* ምሳ 14፥29 እንደሚለው ለትእግስተኛ ሰው ብዙ ማስተዋል አለው፣ ቁጡ ሰው ግን በንፍናውን ከፍ ከፍ ያደርጋል። ትእግስተኛ ሰው ወደ ፍርድ እና ድምዳሜ ከመድረሱ በፊት የችግሩን ሁኔታ ለመረዳት ይሞክራል። ይህ ባህርይ ቤተሰብ ልጆቹን በደንብ እንዲገራ ያደርገዋል። በክርስቶስ አካል ውስጥም ሰላምን ያሰፋፋል፣ እያንዳንዳችንም እለት እለት ከሰዎች ጋር ባለን ግንኙነት ይረዳናል።

5. *ደስታ እና ሰላም።* የመንፈስ ፍሬ የሆነው ደስታ ሁኔታዎችን ፀጥ የማድረግ ሀይል አለው። ምሳ 15፥18 እንዲህ ሲል ይገልጻል። "ቁጡ ሰው ጠብን ያነሳሳል፤ ትእግስተኛ ሰው ግን ፀጥ ያሰኘዋል። "ይህ የለሳም ሰው ወይም እስታራቂ ወደሚለው ባለፈው ትምህርት ወዳጠናነው ሀሳብ ይወስደናል። ትእግስተኛ ሰው በቁጣው እይገዛም፣ ነገር ግን በድርጊቱ፣ በቃላቶቹና ለሰዎች ባለው አሳቢነት የእግዚአ ብሔርን ሰላም ያሳያል።

6. *ትእግስት እና ጥንካሬ።* ስላለም ጠንካራ ሲባል የሚታሰበው ጠንካራ ስውነት ያለው ሰው ወይም ብርቱ ጠባቂዎችና መከላከያ ያለው ነው። ምሳ 16፥32 እንደሚለው "ትእግስተኛ ሰው ከሃያል ሰው ይሻላል፣ በመንፈሱም ላይ የሚገዛ ከተማን ከሚወስድ ይበልጣል።" በመንፈሳዊ እመለካከት ጠንካራ ሰው ስንል ትእግስተኛ ሰው ማለታችን ነው።

7. *ትእግስት እና ይቅርታ።* እርስ በርሳችን እንድንቻቻልና ይቅር እንድንባባል የመንፈስ ፍሬ የሆነው ትእግስት ያስፈልገናል። በቆላ 3፥12-

13 ሐዋርያው ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን እንዲህ ሲል ይመክራል። "እንግዲህ እንደ እግዚአብሔር ምርጦች ቅዱሳን ሆናችሁ፣ የተወደዳችሁም ሆናችሁ፣ ምህረትን፣ ርህራሄን፣ ቸርነትን፣ ትህትናን፣ የዋህነትን፣ ትእግስትን አድርጉ። ማንም በባልንጀራው ላይ የሚነቅፈው ነገር ካለው ይቅር ተባባሉ፤ ክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ።"

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ (በማቴ 18፥21-35) ራሱ ይቅር ተብሎ ባልንጀራውን ግን ይቅር በላላለው ጨካኝና ምስጋና ቢስ ሰው ምሳሌ ነግሯቸዋል። ኢየሱስ እንዳለው ጌታው ይህንን በው እዳውን ሁሉ እስኪከፍል በወህኒ አኖረው። ኢየሱስም በቁጥር 35 ስመቀጠል ሲናገር "ከእናንተ እያንዳንዱ ወንድሙን ከልብ ይቅር ካላሰ እንዲሁ ደግሞ የበማዩ አባቴ ያደርግባችኋል።"

ቁጡ ሰው ይቅርታ ማድረግ ይከብደዋል። የመንፈስ ፍሬ የሆነው ትእግስት የይቅርታ መሰረት ነው። ስስዚህ ትእግስትና (ትእግስተኝነት) ያለማጉረምረም የይቅርታን መንፈስ ያጠቃልላሉ። በ1ቆሮ 13 እንደምናነበው ፍቅር ይታገሳል፣ እይበሳጭም፣ በደልን እይቆጥርም፣ በሁሉ ይፀናል። ሁሉም የመንፈሳዊ ትእግስት ገፅታዎች እዚህ ተካትተዋል።

8. *እምነት ትእግስት ሲጨመርበት።* እምነት ለክርስቲያን ዋነኛ ነገር ነው። ምክንያቱም ፃድቅ የሚኖረው በእምነት ስለሆነ ነው። ነገር ግን ፈተናን የምናልፈው በትእግስት በስለሆነ እምነት በትእግስት ጠርቶ መረጋገጥ አለበት።

እምነት፣ ትእግስት እና የእግዚአብሔር የተሰፋ ቃሉች በዕብራውያን (6፥11-12) ተጠቅበዋል። "በእምነትና በትእግስትም የተሰፋውን ቃል የሚወርሱትን እንድትመስሉ እንጂ ዳተኞች እንዳትሆኑ ተስፋ እስኪሞላ ድረስ እያንዳንዳችሁ ያን ትጋት እስከ መጨረሻ እንድታሳዩ እንመኛለን።"

(4). የመንፈስ ፍሬ ከሆነው ከትእግስት ጋር ከተያያዙት እውነተኛ ዐ ረፍተ ነገሮች ፊት ያለውን ፊደል አክብብ።

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ መከራና ፈተና ስክርስቲያን በጎ ውጤት እንዳለው ያስተምራል።
ስ. ትእግስት የክርስቲያንን ባህሪይ ያሳድጋል።
ሐ. እግዚአብሔር ከክርስቲያኖች ጋር ትእግስትን እንድናደርግ ሲጠብቅብን ከአለማውያን ጋር ግን ትእግስት እንድናደርግ አይጠብቅብንም።
መ. ታጋሽ መሆን ስቁጣ መዘግየትን ያካትታል።
ሠ. ትእግስታችን ባነበች መጠን ፈተናችን ይበዛል።
ረ. ሌሎች ሁለት የትእግስት ቃላት ፅናት እና መቆየት ናቸው።
በ. ትእግስተኛ ሰው ብዙ ጊዜ ቁጣን ያነሳሳል።

የእግዚአብሔር ትእግስት

ዓላማ 3 ከእግዚአብሔር ታላቅ ትእግስት በመነሳት የሚያስፈልግህን የትእግስት መጠን እንድታውቅ ራስህን ለመመርመር።

በመጀመርያ የእግዚአብሔርን ትዕግሥት ብንረዳ የመንፈስ ፍሬ የሆነው የትእግስትን ጠቀሜታ የበለጠ ልትረዳ ትችላለህ። በገላ 5:22 የምናየው የእግዚአብሔርን ባህርይ የሚገልጽ ነው። እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ሲል ራሱን ገለፀ (ዘጸ 34:6)። "እግዚአብሔር፣ እግዚአብሔር መሀሪ፣ ሞገስ ያለው፣ ታጋሽም ባለብዙ ቸርነትና እውነት፣ እስከ ሺህ ትውልድም ቸርነትን የሚጠብቅ ኃጢአትንም ይቅር የሚል።" በጥቅሱ ውስጥ የተገለፁት ቃላት እግዚአብሔር ለሰዎች ያለውን እምላካዊ ትእግስት ያሳያሉ።

የእግዚአብሔር ትእግስት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁሉ ተደጋግሞ የሚታይ መሪ ሀሳብ ነው። እነዚህን ምሳሌዎች ተመልከት።

1. ሐዋርያው ጴጥሮስ እንደዓፈው፣ በኖህ ዘመን የነበሩ ሰዎች እጅግ ኃጢአተኞች ነበሩ (ዘፍ 6:1-12 ተመልከት) "የዳኑበት መርከብ ቢዘጋጅ፣ የእግዚአብሔር ትእግስት በኖህ ዘመን በቆየ ጊዜ ቀድሞ አልታዘዙም" (1ጴጥ 3:20)። የእግዚአብሔር ትእግስት ታላቅ ስለነበረ ኖህና ቤተሰቦቹ ወደ መርከቢቱ ከገቡ በኋላ ዝናብን ሳይልክ ለሰባት ቀናት ቆየ (ዘፍ 7:9-10)። በዚህም ጊዜ እንኳን ከውጭ የቀሩት ኃጢአተኛ ሰዎች ከጥፋት ለማምለጥ ልባቸውን አላቀኑም።

2. የእግዚአብሔር ትእግስት ከእስራኤላውያን ጋር በነበረው ግንኙነት በበፊው ታይቷል። እስራኤላውያን በበረሃ ባመፁ ጊዜና ወደ ግብፅ መመለስ በፈለጉ ጊዜ ሙሴ እግዚአብሔር የተናገረውን በማሳሰብ ጸለየ። "እግዚአብሔር ታጋሽና ምህረት የበዛ እቤሳንና መተላለፍን ይቅር የሚል" (ዘኁ 14:18)። በዘሌ 26 የተገለፀው የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሉች ለእስራኤላውያን እንደሚያሳየው ቢታዘዙ እንደሚባረኩ ባይታዘዙ ግን እንደሚቀጡ ነው። ነገር ግን ትእግስቱ በቁጥር 40 -42 በተጠቀሱት ጥቅሶች ላይ ይታያል። "በእኔም ላይ በእንቢተኝነት በለሄዱብኝ የበደሉኝን በደል ኃጢአታቸውን፣ የአባቶቻቸውንም ኃጢአት ይናዘዛሉ። እኔ ለያዕቆብ የማልሁትን ቃል ኪዳኔን አስባለሁ።"

3. ንጉስ ዳዊት ታላቅ ኃጢአት አድርጎ ነበረ። ምት እንደሚገባው ተረድቶ እንዲህ አለ፡ "እግዚአብሔርን በድያለሁ" (2ሳሙ 12:13)። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ምህረትና ትዕግሥት በለታመነ ይቅር ተባለ። ብዙዎቹ መዝሙሮቹ የእግዚአብሔርን ትእግስትና ይቅርታ ይናገራሉ።

"እምላኬ ሆይ እንዳንተ ያለ ማን ነው፥ ብዙ ጭንቀትንና መከራን እሳይተኸኛልና፣ *ተመልሰህ ሀያውም አደረግሽኝ ከምድር ጥልቅም እንደገና አወጣሽኝ። ፅድቅህንም ለብዛው፣ ተመልሰህም ደስ አሰኘኝ፣ ከጥልቅም እንደገና አወጣሽኝ።* እኔም በሰገና ስለ እውነትህ

አመሰግንሃለሁ። የእስራኤል ቅዱስ እምላክ ሆይ በመስንቆ አዘምርልሃለሁ"።

ይህ መዝሙር ደጋግሞ እንደሚያመለክተው እግዚአብሔር ደጋግሞ ዳዊትን ለመመለስና ከመከራ ለማዳን ታጋሽ መሆኑን ነው።

4. ነህምያ የህዝቡን አስጸያፊ ኃጢአቶች ባወቀ ጊዜ የምልጃ ፀሎት አቅርቦ ለእምላኩ ሳይ የነበረውን እምነት ለእነዚህ ቃላቶች ገለፀ። "እንተ ግን ይቅር ባይ፣ ቸርና መህሪ አምላክ፣ ለቁጣም የምትዘገይ፣ ምህረትንም የምታበዛ ነህ አልተውሃቸውም፣ ያስተምራቸው ዘንድ መልካሙን መንፈስህን ሰጠሃቸው፣ መናህንም ከአፋቸው አልከለከልህም ለጓርባ እመታት በምድረ በዳ መገብሃቸው" (ነህ 9:17፣ 19-21)። የእስራኤላውያንን የምድረበዳ ጉዞ ታሪክ ብታነብ እግዚአብሔር ለእነሱ የነበረውን የትእግስት ታላቅነት ትመለከታለህ።

5. ሐዋርያው ጴጥሮስ በሁለተኛው መልእክቱ ስለ እግዚአብሔር ትእግስት እንዲህ ሲል ይናገራል። "ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደ ሚመስሰቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፣ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሀ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እስዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሳል" (2ጴጥ 3:9)። የጌታችንም ትእግስት መዳናችሁ እንደሆነ ቁጠሩ (2ጴጥ 3:15)።

(5). ሐዋርያው ጴጥሮስ ከዓፈው (2ጴጥ 3:9፣ 15) በመነሳት እግዚአብሔር በምሳሌ እንደታየው ለኖህ ዘመን ሰዎች፣ ለእስራኤላውያንና ለንጉስ ዳዊት ለምን ታላቅ ትእግስቱን እንዳሳየ ግለፅ።

(6). ከእግዚአብሔር ትእግስት በመነሳት ራስህን መርምር። አንተን በሚገልፅ ሳጥን ውስጥ የ✓ ምልክት እድርግ።

እኔ	በፍፁም አልፎ አልፎ	አንዳንድ ጊዜ	ብዙ ጊዜ	ሁል ጊዜ
ሀ. ርህሩህ ነኝ				
ለ. ቸር (ለጋስ) ነኝ				
ሐ. ለቁጣ የዘገየሁ ነኝ				
መ. እፍታሪ ነኝ				
ሠ. ታማኝ ነኝ				
ረ. ይቅር ባይ ነኝ				
ሰ. ለመጠበቅ ፈቃደኛ ነኝ (ትእግስተኛ ነኝ)				

ክርስቲያን እና ትእግስት

ዓላማ 4 ሰተብጡት ምሳሌዎች የሚያስፈልጉትን የትእግስት ገፅታዎች ለመግለጽ።

የመንፈስ ፍሬ የሆነው ትእስት በውጭ ከሰዎች ጋር ባለን ግንኙነት ሲሰራ በውስጣችን ደግሞ እኛ በምንፈተንበት ጊዜ ይሰራል። ዕብ 12:7-11 ፈተናችንን በፅናት እንድንወጣና እግዚአብሔር ራሳችንን ለእርሱ

እንድናስገዛ እኛን ለመግራት የሚጠቀምባቸው ትምህርቶች አድርገን ልንወስዳቸው ይገባል። ስለዚህም መከራን መታገስ ክርስቶስን የመምሰል ባህሪ በውስጣችን እንዲያድግ የሚያደርግ የሂደት አካል ነው።

ቤተሰባዊ ግንኙነት ውስጥ ትእግስት አስፈላጊ ነው። የትእግስትን ፍሬ ለመፈተሽ ትክክለኛው ቦታ ቤተሰብ ነው። ልጆችን በፍቅር ለማሳልጠንና በትክክል ለማረቅ ብቁ ትእግስት ይጠይቃል። ባልና ሚስት ፍቅር የተሞላው ህብረታቸውን ለመጠበቅ ትእግስት ያስፈልጋቸዋል።

የገለፅናቸው የትእግስት ገፅታዎች መታገስ፣ መፅናት፣ መረጋጋት ለቁጣ መዘግየት፣ ራስን መግዛት፣ መቆየት፣ መጠበቅና የይቅርታ መንፈስ ሁሉ በውስጣችን የሚያድሩት ለመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ሲሆን ከሰዎች ጋር ባለን ግንኙነት እለት እለት እንድንለማመዳቸው ተጠርተናል። ጠቃሚው ነገር ትእግስት የሚጠይቅ ሁኔታን ሲገጥመን ወደመንፈስ ቅዱስ እርዳታ መጠየቅ ነው። 1ተሰ 5፡15 እንደሚለው "ሰውን ሁሉ ታገሱ።" ይህ ማለት እያንዳንዱን የቤተሰባችንን አባል፣ የቤተክርስቲያንን ቤተሰቦችና በየእለቱ የሚገጥሙንን ሰዎች መታገስ ማለት ነው። በተፈጥሮአችን ይህ አስቸጋሪ ጉዳይ ነው። ነገር ግን የእግዚአብሔር ባህርይ በመንፈስ ቅዱስ ሰውስጣችን ሲሰራ ለማንኛውም ሰው ትእግስት ልናሳይ እንችላለን።

(7). ለሚከተሉት ምሳሌዎች የትኛው የትእግስት ገፅታ ወይም ገፅታዎች እንደሚያስፈልግ ግለፅ።

ሀ. የለሎሜ ባለቤት የመጠጥ ሱሰኛ ነው። ድኅነት እንዲያገኝ ለብዙ ዓመታት ብትፀልይም እርሱ ግን በኃጢአት ኑሮ ውስጥ መዓዙን ቅጥሏል። ስለዚህም እርሷ ተስፋ ወደ መቁረጥ ተቃርባለች። ለለሎሜ የሚያስፈልጋት ምንድን ነው?

ለ. ዮሐንስ በመኪናው ለአሥር ዓመታት ተገልግሎባታል። ሆኖም አሁን አዲስ መኪና መግዛት ፈለገ። ይህን ካደረገ ግን ለቤተሰቡ የሚያስፈልገው ጥሩ ልብሶችና ለልጆቹ የትምህርት ቤት ወጪአቸውን መሸፈን አይችልም። ዮሐንስ የሚያስፈልገው ምንድን ነው?

ሐ. ሶስና በምትሰራበት ቢሮ ውስጥ ብዙ ፀሀፊዎች አሉ። ከእነሱ ውስጥ አንዷ ብርቱካን ናት። ብርቱካንና ሶስና ክርስቲያን እንደሆነች ስለምታውቅ እሷን ለማናደድ ያለ ማቋረጥ አንዳንድ ነገሮችን ታደርጋለች። ሶስና የሚያስፈልጋት ምንድን ነው?

መ. እስጢፋኖስ ብዙውን ጊዜ ደስተኛ ነው። ነገር ግን መኪናውን ስሚነዳበት ጊዜ ሰው ስመንገድ ከመጣበት ወይም ከፊት ለፊቱ የሚነዳው ሰው ቀስ ካለ ይናደዳል። የሚያስፈልገው ምንድን ነው?

ሠ. ያዕቆብ ቤተክርስቲያን ውስጥ ለብዙ አመታት መጣ ቅረት ይላል። በሰዎች ላይ ድካም ባየ ጊዜ፣ ቤተክርስቲያን ውስጥ ችግር ሲፈጠር ወይም በሆነ ነገር ሲቀየም ለጥቂት ጊዜያት ቤተክርስቲያን መሄድ ያቆማል። የሚያስፈልገው ምንድን ነው?

ረ. የቤተልሔም እማት ሁልጊዜ አቃቂር ታወጣላታለች፣ ብዙ ጊዜም በቤተሰቧ ፊት ትስድባታለች፣ በቅርቡ እንዳውም ልጇ ለሆነው ለቤተልሔም ባለቤት እንደ ቤተሰቡ አባል እንደማትቆጥራት ነግራዋለች። ይህም የቤተልሔምን ስሜት በጣም ጎድቷታል። እርሷ የሚያስፈልጋት ምንድን ነው?

ሰ. ሳሙኤል የሚኖረው ክርስቲያን ያልሆነ ገዥ ባለበት አገር ውስጥ ነው። ክርስቲያኖች በጉባኤ እንዳያመልኩና እስዳይመሰክሩ ተከልክለዋል። ሳሙኤል በግሉ መጽሐፍ ቅዱሱን ያነባል፣ ለቤተሰቡም ይፀልያል። ነገር ግን ይህንን ስደት ለመቃወም ከብዶታል። ሳሙኤል የሚያስፈልገው ምንድን ነው?

አገልግሎት እና ትእግስት

ዓላማ 5 ሰተሰጡት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ ትእግስትንና የሚያስገኘውን ምላሽ ለመግለጽ።

የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ትእግስት በወንጌል አገልጋይ ሕይወት እና አገልግሎት በጣም ትልቅ ሥፍራ አለው። ትእግስት በፀሎት፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ በስልጠና፣ በእድገትና በዝግጅት ጊዜ ሁሉ ያስፈልጋል። በመሪነትና ሌሎችን በማገልገል ጊዜ ትእግስት ያስፈልጋል። ይህንን ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በአገልግሎቱ ስለ ትእግስት አስፈላጊነት የመከረው። "በእግዚአብሔር ፊት በህያዋንና በሙታን ሊፈርድ ባለው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት፣ በመገለጡና በመንግስቱም እመክርሃለሁ፤ ቃሉን ስበክ፣ በጊዜውም አሰጊዜውም ፅና ፈፅመህ እየታገስህና እያስተማርህ፣ ገስፅ፣ ገስፅ፣ ምከር። አንተ ግን ነገርን ሁሉ በልክ አደርግ፣ መከራን ተቅበል የወንጌልን ስባኪነት ስራ አድርግ፣ አገልግሎትህን ፈፅም" (2ጢሞ 4፡1-2፣ 5)።

በሌላ አባባል የአገልጋይ ስራ ስብከት፣ ማስተማር፣ መገስጽ፣ ማበረታትና ሌሎችም ተግባራት ሁሉ በታላቅ ትእግስት የሚከናወኑ ናቸው።

(8). ከዚህ በታች የወንጌል አገልጋይንም ሆነ በመንፈስ የተሞላ ክርስቲያንን የሚመለከቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ። ለእያንዳንዱ ምንባብ ውስጥ ትእግስትን የሚገልጸውን ቃል ለይ።

ሀ. በመልካም መሬት ላይም የወደቁ እነርሱ በመልካም እና በሰነ ልብ ቃሉን ስምተው የሚጠብቁ በመፅናትም ፍሬ የሚያፈሩ ናቸው (ሉቃ 8፡15)።

ለ. በመታገሳችሁ ነፍሳችሁን ታገኛላችሁ (ሉቃ 21፡19)።

ሐ. የእግዚአብሔርን ፈቃድ አድርጋችሁ የተስጣችሁን የተስፋ ቃል እንድታገኙ መፅናት ያስፈልጋችኋልና (ዕብ 10፡36)።

መ. ወንድሞች ሆይ፣ የመከራና የትእግስት ምሳሌ የሆኑትን በጌታም ስም የተናገሩትን ነቢያትን ተመልከቱ። እነሆ፣ በትእግስት የፀኑትን ብፁአን እንላቸዋለን፣ ኢዮብ እንደታገስ ስምታችኋል፣ ጌታም እንደፈፀመለት አይታችኋል፣ ጌታ እጅግ የሚምር የሚራራም ነውና (ያዕ 5፡10-11)።

(9). ቀደም ባሉት ምንባቦች ውስጥ የተጠቀሱትን ትእግስት የሚያስገኛ ቸውን ነገሮች ግለጽ።

ትእግስት ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፍ ወይም በዐሉት የሚጨመር፣ ዘይት በመቀባት፣ እጅ በመጫን ወይም እንደዚህ የመሳሰሉትን ነገሮች በማድረግ የሚገኝ አይደለም። በፈቀድንበት መጠን መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ክርስቶስን እንድንመስል የሚያፈራው ፍሬ ነው። በህይወትህ የሚያልፈው ማንኛውም ፈተናና መከራ፣ ማንኛውም መዘግየት መንፈስ ቅዱስ በአንተ ውስጥ የትእግስትን ፍሬ እንዲያፈራ የተሰጠ እድል ሊሆን ይችላል።

ትእግስት በምሳሌ

ዓላማ 6 በሕይወትህ ልትጠቀምባቸው የምትችላቸውን ከአሉታዊም ሆነ አዎንታዊ የትእግሥት ምሳሌዎች መመርያዎችን ለማውጣት።

አሉታዊ ምሳሌዎች

እንዳንድ ጊዜ ክርስቶስን የመምሰል አመለካከት በሚጓደልበት ጊዜ የሚከሰተውን ነገር በማስተዋል ጠቃሚነቱን እንድናይ ያደርገናል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኛቸው አሉታዊ ምሳሌዎች የትእግስት ማጣት የፈጠራቸው ችግሮች እንደሆኑ እንመለታለን።

አብርሃም - እግዚአብሔር ዘሩ ታላቅ ሀገረ እንደሚሆን ለአብርሀም ቃል ገብቷል (ዘፍ 15፥1-5)። ትእግስት ከማጣቱ የተነሳ አብርሀም የእግዚአብሔር የተሰፋ ቃል እስኪፈፀም አልጠበቀም። ነገር ግን ሰራሱ መንገድ ችግሩን ሰመፍታት ወሰነ። በውጤቱም ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ እስማኤል ተወለደ። እስማኤል ለአብርሃም፣ ለሣራ እና ለይስሀቅ የችግር ምክንያት ሆነ። በአሁኑ ጊዜ እንኳን በእስማኤልና በይስሀቅ ዘሮች መካከል ግጭት አለ።

ያዕቆብ - ይህ ወጣት ሰው እግዚአብሔር መሪ እንደሚሆን የተናገረውን ቃል እስኪፈፀም ሰትእግስት አልጠበቀም (ዘፍ 25፥23)። ዘፍ 27 በረከትን ሰማግኘት አባቱን እንዴት እንዳታለለ ይነግረናል። እግዚአብሔር መሪ እስኪያደርገው ድረስ ባለመታገሱ ሰዩትን መከራንና ሌሎችንም ችግሮች ተቀበለ። የችግሩን ምንነት ሰፈርኦን በተናገረው በእንደ ዐረፍተ ነገር ተጠቃልሰው እናገኛሰን። "የሕይወት ዘመኖቼ ጥቂትም ክፉም ሆኑብኝ" (ዘፍ 47:9)።

ሳኦል - ሳኦል የመጀመርያው የእስራኤል ንጉስ እንዲሆን በመንፈስ ቅዱስ የተቀባ ትሁት በው ነበር። ነገር ግን ሳሙኤል መጥቶ ማድረግ ያለበትን እስኪነግረው ድረስ ሰባት ቀናት ሰመጠበቅ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አልታዘዘም። ባለመታገሱ የካህናትን ተግባር የሚቃጠለውን መስዋእት አቀረበ። ከዚህም የተነሳ መንግስቱን እጣ (1ሳሙ 10፥8-10 እና 12፥11-14 ተመልከት)።

ዮናስ - እግዚአብሔር ለነነዌ ከተማ ከነበረው ርህራሄና ትእግስት የተነሳ ለማመን እስኪያስቸግር ድረስ ዮናስ በጌታ ላይ ተቆጥቶ ትእግስት አጣ። ዮናስም እግዚአብሔርን እንዲህ አለው። "አንተ ቸርና ይቅር ባይ፣ ታጋሽም፣ ምህረትህም የበዛ፣ ከክፉው ነገርም የተነሳ የምትፀፀት አምላክ እንደሆንህ አውቄ ነበርና።" (ዮና 4:2) በግልፅ እንደምናነበው ዮናስ ለከተማዋ የነበረው አመለካከት እግዚአብሔር እንደነበረው ርህራሄና ይቅርታ አይደለም።

በሚከተሉት መልመጃዎች ውስጥ ሰተለያየ ምሳሌዎች የተጠቀሱትን መመሪያዎችና በሕይወታችን እንዴት ልንለማመዳቸው እንደምንችል የሚያሳዩ ምሳሌችን ምረጥ።

(10). የአብርሀምና የያቆብ ምሳሌ የሚገልፀው።

ሀ. ጌታ በሰጠን የተሰፋ ቃል እርምጃ እንድንወስድ ነው።
ሰ- ጌታ አንድ ነገር እንደሚያደርግልን ቃል ከገባ እርሱ እስኪፈፅመው ድረስ መታመን ይሻላል።

(11). የሳኦል ምሳሌ የሚገልፀው

ሀ. መጠበቅ እግዚአብሔር ለእኛ ካሰው የስልጠና ሂደት አንዱ ነው።
ሰ. እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ በስዎች ሰኩል ሊናገረን ይወዳል።

(12). የዮናስ ምሳሌ የሚያሳስበን

ሀ. እግዚአብሔር በራሳቸው መንገድ ለመሄድ የሚመርጡ ሰዎችን አይታገስም።
ሰ. እግዚአብሔር በሰዎች ተስፋ እንድንቆርጥ ሳይሆን ከስዎች ጋር ባሰን ግንኙነት የእርሱን የትእግስት ምሳሌ እንድንከተል ይፈልጋል፡

አዎንታዊ ምሳሌዎች

ዳዊት ዘማሪው እግዚአብሔርን መጠበቅ ጠቃሚ እንደሆነ ተምሯል። በመዝ 37፥7 እንደፃፈው ለእግዚአብሔር ተገዛ ተስፋም አድርገው ይላል። ከመዝ 37፥7 ቀጥሎም ይህንኑ ምስክርነት ሲስጥ እንዲህ ብሏል። "ቆይቼ እግዚአብሔርን ደጅ ጠናሁት፣ እርሱም ዘንበል አሰልኝ ጩኸቴንም ሰማኝ" (መዝ 40፥1)።

የብሉይ ኪዳን ነብያት - ያቆብ 5፥10 እንደሚሰው "ወንድሞች ሆይ፣ የመከራና የትእግስት ምሳሌ የሆኑትን በጌታ ስም የተናገሩትን ነብያትን ተመልከቱ።" ኤልያስን፣ ኤልሳእን፣ ሐዘንተኛውን ነብይ ኤርሚያስንና ሌሎች ብዙ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ለእግዚአብሔር ስም ለእመኛው ሀገረ የተናገሩትን ነብያት አስብ። እነዚያ የእግዚአብሔር ቅዱሳን ከመንፈስ የተሰጠ ትእግስት ነበራቸው።

ኢዮብ - በምሳሌነት ሰያዕ 5፥11 ውስጥ የተጠቀሰውን ትልቅ ትእግስት ያሰውን ኢዮብን ሳንጠቅስ እናልፍም ። ኢዮብ በብዙ መንገድ በእነሱ፣

በስሜቱ፣ ንብረቱንና ቤተሰቡን በማጣት ቢፈተንም ትእግስቱ ግን እነዚህን ታላላቅ ፈተናዎች በፅናት እንዲወጣና ለጌታም እንዲህ እንዲል እስችሉታል። "እነሆ ቢገድለኝም እንኳ እርሱን በትእግስት እጠብቃለሁ" (ኢዮ 13፥15)።

ጳውሎስ - በ2ቆሮ 6፥4 እና 6 ትእግስተኛ ሰው እንደሆነ ይናገራል። በዚያው ምእራፍ ውስጥ ከቁጥር 4 እስከ 10 ጳውሎስ በሕይወቱ የነበረውን ኃይለኛ ማእበልና ጨለማ ይገልፃል። በሕይወትህ የመንፈስ ፍሬ እውን ካልሆነ እንደዚህ ባለ ሁኔታ ውስጥ መታገስ ቀላል እይደለም። በኋላም በ2 ጢሞቲዎስ እስር ቤት በነበረ ጊዜ በፃፈው መልእክት ትእግስቱን፣ እምነቱን፣ ፍቅሩንና ፅናቱን ይጠቅሳል (ምዕ. 3 ቁ. 10)። ጳውሎስ ትእግስትን ከጌታው የተማረ እውነተኛ ደቀ መዝሙር ነው። በለዚህም ነው ጳውሎስ እንደዚህ ብሎ መፃፍ የቻለው፣ ይህም ልንቀበለው የሚገባን የታመነ አባባል ነው።

> "ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው ከኃጢአተኞችም ዋና እኔ ነኝ፣ በሰዘህ ግን፣ የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት በእርሱ ያምኑ ዘንድ ላላቸው በዎች ምሳሌ እንድሆን ኢየሱስ ክርስቶስ ዋና በምሆን በእኔ ላይ ትእግስቱን ሁሉ ያሳይ ዘንድ ምህረትን አገኘሁ" (1ጢሞ 1፥15-16)።

የዕብራውያን ፀሐፊ እንዲህ በማለት እንድናበብ ያደርገናል።

> "እንግዲህ እነዚህን የሚያህሉ ምበክሮች እንደ ደመና በዙርያችን ካሉልን፣ እኛ ደግሞ ሸክምን ሁሉ ቶሉ የሚከበንን ሃጥያት አስወግደን፣ በትእግስት እንሩጥ። እርሱ ነውርን ንቆ በፈቱም ባላሰው ደስታ በመስቀል ታግሶ በእግዚአብሔር ዙፋን ተቀምጦአልና" (ዕብ 12፥1-2)።

የክርስቶስ ዳግመኛ ምፅአት - ኢየሱስ ወደ ሰማይ ባረገበት ጊዜ የመመለሱን ተስፋ ሰጥቶናል። ምእተ አመታት ቢያልፉም ቤተክርስቲያን እሁንም ይህን ተስፋ ቃል በትጋትና በሀያውነት ትጠብቃለች። ያዕቆብ በትእግስት የመጠበቅን አስፈላጊነት ያሳበበናል። "እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፣ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ታገሱ። እናንተ ደግሞ፣ ልባችሁንም አፅኑ የጌታ መምጣት ቀርቦአልና" (ያዕ 5፥7-8)። እስከሁን እንዳየነው ጌታ ቃሉን ይጠብቃል የዘገየው ግን ሰዎች ንስሀ እንዲገቡ እና ከሀጥያታቸው እንዲድኑ እድል ስመስጠት ነው። (2ጴጥ 3፥9፣ 15 ተመልከት)።

(13). ከእሉታዊ የትእግስት ምሳሌዎች በለምንማረው መመሪያዎች እውነተኛ ከሆነው ዐረፍተ ነገር ፊት ያለውን ፊደል አክብብ።

ሀ. እግዚአብሔር የልጁን ዳግም ምፅአት እንዲዘገይ ያደረገው ለሰዎች ተጨማሪ የንስሐ ጊዜ ለመስጠት ነው።

ለ. ከኃጢአተኞች ሁሉ የከፋ ኃጢአተኛ የነበረው ጳውሎስ የትእግስት ምባሌ ከሆነ ትእግስት በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በመንፈስ በተሞላ በማንኛውም ክርስቲያን ውስጥ ሊያድግ ይችላል።

ሐ. ጌታን በተስፋ የሚጠብቁ ተስፋ ይቆርጣሉ።

መ. እግዚአብሔር ራሱን ለእኛ ካሳየን በኋላ ብቻ ነው ትእግስት በውስ ጣችን ሊያድግ የሚችለው ።

ሠ. ትእግስትና ፅናት ሰትዝህ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር እስፈላጊ ናቸው።

በራእይ 2 እና 3 የተጠቀሱት የኢየሱስ የማጠቃለያ ንግግሮች ስስባቱ እብያተ ክርስቲያናት እነዚህ ናቸው። "ድል ስነሳው . . . እስጠዋለሁ።" ድል ስነሳው ሐዋርያው ጳውሎስ እንደሚያመለክተው የትእግስት ዘላለማዊ ሽልማት ታላቅ ነው።

> "የማይታየውን እንጂ የሚታየውን ባንመለከት ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልናልና የሚታየው የጊዜው ነውና፣ የማይታየው ግን የዘላለም ነው" (2ቆሮ 4፥17-18)።

የመከራ ፈተና

ምርጫ። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ የሆነውን መልስ (መልሶች) ምረጥ።

1. ትእግስት ለሚለው ቃል ትክክለኛው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ፍቺ የትኛው ነው?

ሀ. ብዙ መቻል
ለ. ራስን የሚገዛ
ሐ. በቀላሉ የማይቆጣ
መ. ተስፋ የሚቆርጥ
ሠ. ዕናት

2. ዕናት የሚናገረው ስለ

ሀ. መከራ ነው
ለ. ተስፋ ነው
ሐ. መከራን መቻል ነው
መ. መቀበልን ነው

3. ከእነዚህ ውስጥ የዕናት ውጤት የትኛው ነው?

ሀ. ባህርይ ለ. ሰላም ሐ. ይቅርታ መ. ጥበብ

4. ያጠናነው የእግዚአብሔር ቃል እንደሚነግረን የእግዚአብሔር ታላቅ ትእግስት ለኃጢአተኞች ከምን የተነሳ ነው?

ሀ. እኛም እንዲሁ አይነት ባህርይ እንዲኖረን ለማስተማር ነው።
ለ. ሰዎች ንስሀ እንዲገቡ እድል ለመስጠት ነው።
ሐ. ትእዛዛቱን ለመጠበቅ አስቸጋሪ እንደሆነ ስለሚያውቅ ነው።
መ. እርሱ ከእኛ የሚጠብቀው እጅግ ከባድ ስለሆነ ነው።

5. ከእነዚህ ቃላት ውስጥ እግዚአብሔር ራሱን ለመግለፅ የተጠቀመ ባቸው የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ርህሩህ
ለ. ቸር
ሐ. ለቁጣ የዘገየ
መ. ታጋሽ እና አፍቃሪ
ሠ. ይቅር ባይ
ረ. ከላይ የተጠቀሱትን ቃላቶች ሁሉ ራሱን ለመግለፅ ተጠቅሞባቸዋል።

6. እንደ ማቴ 18፡21-35 አበባል የጌታን ምህረት ለመቀበል ቅድሚያ ማሟላት ያለብን ሁኔታ ምንድን ነው?

ሀ. ለኃጢአታችን ማዘን
ለ. ፈልጎ መጠየቅን
ሐ. ሌሎችን ይቅር ማለት
መ. ትእግስት

እውነት-ሐሰት። መልሱ ትክክለኛ ከሆነ "እ" ብለህ ፃፍ። ሐሰት ከሆነ ደግሞ "ሐ" ብለህ ፃፍ።

7. አገልጋይ በትእግስት ሊያርም፣ ሊገስጽ ሊያበረታታ ይችላል።
8. ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ለትእግስተኛ ዋጋ እንዳለው ይገልፃሉ።
9. ትእግስት በፈለግነው ጊዜ እግዚአብሔር የሚጨምርልን ባህርይ ነው።
10. ዮናስ የእግዚአብሔርን እቅድ ለማስፈፀም ታላቅ ትእግስት ያሳየ ምሳሌ ነው።
11. ኢዮብ መከራ የተቀበለ ጥሩ የትእግስት ምሳሌ ነው።
12. የጌታ ዳግም ምፅአት መዘግየት ለሰዎች የወንጌልን መልእክት እንዲቀበሉ እድል ለመስጠት ነው።
13. ትእግስትን መማር የሚቻለው በታላቅ መከራ ብቻ ነው።
14. እብሃኛውን የትእግስት ትምህርት የምናገኘው ምናልባት ከክርስ ቲያኖች ህብረት ውጭ ነው።
15. የጌታን ምሳሌ መከተል መስቀል መያዝን ያጠይቃል።

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስ

8. ሀ. ዕናት
ለ. በዕናት መቆም
ሐ. መዕናት
መ. ትእግስት እና ዕናት

1. ያነተ መልስ ከእነዚህ ጋር ሊመሳሰል ይገባል።

ሀ. ፈተና ወይም መከራ ባለ ጊዜ ተስፋ እለመቁረጥ መከራን መታገስ
ለ. እይቆጣም ወይም በደል ሲደርስበት አይዘቀልም።

9. ሽልማቶቹ የሚከተሉት ናቸው። ጥረ ማፍራት፣ ራሳችንን ማዳን፣ እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ ማግኘት እና መባረክ ናቸው።

2. ኢያስብን ለመከተል ወይም ደቀመዝሙር ለመሆን መስቀልን ለመሸከም (መከራን ለመቀበል) ፈቃደኝነት ይጠይቃል።

10. ለ

3. ሀ. በመከራችን ልንደሰት እንችላለን፣ ምክንያቱም ትእግስትን ስለሚያስተምረን፣ መልካም ባህርይ እንዲኖረን ስለሚያደርግ እና ተስፋ ስለማያስቆርጥ ነው።
ለ. በእንተ ውስጥ ትእግስትን ስለሚያሳድግ ፈተናህን በደስታ መቀበል መሰኖ የበሰለ እንድትሆን ያደርግሃል።
ሐ. የኢዮብ ምሳሌ እንደሚያስረዳን መከራን ከታገስን በረከትን እንቀበላለን።
መ. መከራን ብትታገስ በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስን ታገኛለህ።

11. ሀ

4. ሀ. እውነት
ለ. እውነት
ሐ. ሐሰት
መ. እውነት
ሠ. እውነት
ረ. ሐሰት
ሰ. እውነት
ሸ. ሐሰት

12. ለ

5. እግዚአብሔር ማንም ሰው ከነ ኃጢአቱ እንዳይሞት፣ እያንዳንዱ ይቅር እንዲባልና ከእርሱ ጋርም እንዲታረቅ ይፈልጋል።

13. ሀ. እውነት
ለ. እውነት
ሐ. ሐሰት
መ. ሐሰት
ሠ. እውነት

6. ይህ መልመጃ በሕይወት ውስጥ ትእግሰት በሚያስፈልግህ አቅጣጫ የመንፈስ ቅዱስን እርዳታ እንድትመሰክት ይረዳሃል።

7. እንደሚከተለው ተቀምጠዋል።

ሀ. ቻይነት
ለ. ራስን መግዛት
ሐ. እርጋታና ቻይነት
መ. ለቁጣ መዘግየት
ሠ. መታገስ፣ ዕናት
ረ. የይቅርታ መንፈስ
ሰ. መታገስ ፣ ዕናት

6 ቸርነትና በጎነት
መንታዎቹ ፍሬ

ትምህርት

ቸርነትና በጎነት በጣም የተባለሉ ከመሆናቸው የተነሳ እንዳንደ ለመለየት እንኳ አስቸጋሪ ነው። ቸር ሰው ጥሩ ሰው ነው፣ ጥሩ ሰው ሁሉንም ይረዳዋል ደግ ነው። እነዚህ ሁለት ባህርያት ከፍቅር የሚመነጩ ናቸው። አንድ ሰው እንደተናገረው ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን ያጠናነው፣ ትእግስትን የመከራው ፍቅር፣ ቸርነትን ርህሩህ ፍቅር እንዲሁም በጎነትን አገልጋዩ ፍቅር ብሎታል።

እነዚህ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በውስጣችን የሚያድጉት ባህርያት ከሌሎች ጋር ባለን ግንኙነት የሚጠቅሙን ናቸው። አንድ ሰው እሷ ጥሩ ሰው ናት ሲል፣ ደግና በጎ ናት ማለት ነው።

ብዙውን ጊዜ ደግነት ሰው ለሰው ያለው የፍቅር መግለጫ እንደሆነ ስናስብ በጎነት ደግሞ የንፅህና ምልክት ሆኖ እናገኘዋለን። በዚህ ትምህርት ውስጥ የእነዚህ የሁለቱ ቃላት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አጠቃቀም በአሁኑ ጊዜ ባጠቃላይ ከምንጠቀምባቸው ለየት እንደሚልና ቸርነትና በጎነት ብዙ የፍቅር መግለጫዎችን እንደማያጠቃልሉ ትመለከታለህ።

ወላጆች ሁልጊዜ ልጆቻቸውን መልካም እንዲሆኑ ሲነግሯቸው መጥፎ እንዲሆኑ ግን መንገር አያስፈልጋቸውም። መጥፎ መሆን ራሱ የሚመጣ ነገር በመሆኑ ነው። በውስጣችን የክርስቶስ መንፈስ ከሌለ ተፈጥሮአችን ክፉና መጥፎ ወደ መሆን ያደላ ነው። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ቸርነትንና በጎነትን ስለሚያፈራ ዓለምን በክርስቶስ ፍቅር እንድናገለግል የረዳናል። ሰዓለም የሚያስፈልገው ኢየሱስ ነው። ይህም ማለት ብዙ ፍቅር፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ የዋሃትና ሰጋስነት ነው።

የነፍሰ ትምህርቱ አከፋፈል

- የቸርነትና የበጎነት ምንነት
- ቸርነትና በጎነት ሲገለፅ
- ቸርነትና በጎነት በምሳሌ

የነፍሰ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህንን ትምህርት ስታጠናቅቅ የሚከተሉትን ማድረግ መቻል ይኖርብሃል።

- የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሆኑትን የቸርነት (ክሪስቶቴስ) እና የበጎነት (ኢንቶስኒ) ምንነት መግለጽ።
- የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሆኑትን የቸርነትና የበጎነትን ምንነት መግለፅ።
- ከአገልግሎት፣ ከሰጋስነት፣ ከምህረትና ከፀጋ ጋር የተያያዙትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎች መግለጽ።

- በሕይወትህ ውስጥ ቸርነትና በጎነት ሊገለፅባቸው የሚያስፈልጉትን ቦታዎች ለይ።

የክፍለ ትምህርት መመሪያዎች

1. ትምህርቱን እንዳሰፉት ትምህርቶች አድርገህ አጥና። በትምህርቱ ውስጥ የተጠቀሱትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ማንበብህ ጠቃሚ ነው። የማጥኛ ጥያቄዎችን መልስ። ወደሚቀጥለው ክፍል ከመሄድህ በፊት እያንዳንዱን የትምህርቱን ዓላማ ማሟላትህን እርግጠኛ ሁን።
2. የመከራ ፈተናውን ስርተህ መልሶችህን አመሳክር።

የትምህርቱ ዝርዝር

የቸርነት እና የበጎነት ምንነት

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጉም (ፍቺ)

ዓላማ 1 የቸርነትና የበጎነትን ባህሪያት ከእያንዳንዱ ትርጉምቻቸው ጋር ለማዛመድ።

የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትእግስት፣ ቸርነትና በጎነት. . ነው (ገላ 5፡22)።

ቸርነት

ቸርነት በገላትያ 5፡22 የመጣው ክሪስቶቴስ ከሚለው የግሪክ ቃል ነው። ይህም ሚስት የንፅህና ምልክት ብቻ ሳይሆን የለጋስነት ባህሪንና አመሰጋገቡት ነው። ልስላሴን፣ ርህሩህነትንና መልካምነትን ያጠቃልላል።

በማቴ 11፡30 ክሪስቶቴስ የተባለው ቃል የኢየሱስን ቀንበር ለመግለፅ ተጠቅሷል። በዚህ ሥፍራ ኢየሱስ "ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነው" ብሎ ተናግሯል። ኢየሱስ ቀንበር ብሎ የሚናገረው በመታዘዝ፣ በመገዛት፣ ዘርጎራጌ፣ በማልገልና በመተባበር ስለሚያደርግ የተገራ ሕይወት ነው። ይህም ዐጋ የሞላው፣ መልካምነትና ቸር የሆነ ግንኙነት ነው። ምክንያቱም የተመሰረተው በፍቅር ላይ እንጂ በሀይል ወይም በባርነት ላይ ባለመሆኑ ነው። ስለምንወደው የምናገለግለው ጌታ አለን። ከእርሱ ፍቅር የተነሳም እርስ በርሳችን እንዳችን ሌላችንን እናገለግላለን። ከፍቅር የተነሳ ማገልገል ታላቅ እድል ሲሆን ያለፍቅር ማገልገል ግን የማይቻል ነው። ይህንን ሀሳብ የበለጠ በትምህርቱ ውስጥ እናነሳዋለን።

ክሪስቶቴስ የሚለው ቃል በሉቃ 5፡39 ላይ እንደገና አሮጌውን ወይን፣ ጣፋጩንና የደረሰውን ለመግለፅ ተጠቅሷል። በዛ ውስጥ መራርነት የለም። ይህም ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌ 4፡31-32 እና 5፡1-2 ያሰውን ሀሳብ የተሻለ እንድንገነዘብ ይረዳናል።

"መራርነትና ንዴት ቁጣም፣ ጩኸትም፣ መሳደብም ሁሉ ከክፋት ሁሉ ጋር ከእናንተ ዘንድ ይወገድ። እርስ በርሳችሁም ቸሮችና ርህሩሆች ሁኑ፣ እግዚአብሔርም ደግሞ በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ።"

"እንግዲህ እንደተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን የምትከተሉ ሁኑ፣ ክርስቶስም ደግሞ እንደወደዳችሁ ለእግዚአብሔርም የመዓዛ ሽታ የሚሆንን መስዋእት አድርጎ በስ እናንተ ራሱን አሳልፎ እንደሰጠ በፍቅር ተመላለሱ።"

የፍቅርን ኑሮ መዓዛ እንዳለው መስዋእት እንዴት መኖር እንዳለብን የሚያሳየን ምሳሌ ክርስቶስ ነው። የብሉይ ኪዳን የኃጢአት መሥዋዕት መልካም መዓዛ እንዳለው በፍፁም አልተገለፀም። ኢየሱስ የኃጢአት መስዋዕታችን ግን ራሱን በርህራሄ፣ በመልካምነትና በደግነት በሰጠን ይህ መልካም መዓዛ ተብሎዋል። ኢየሱስ እንዳችን በሌላችን ሊኖረን ስለሚገባ ቸርነትና ርህራሄ ትልቅ ምሳሌ አሳይቶናል። በለዚህም ነው ኢየሱስ ለሐዋርያው ጳውሎስ መልካም መዓዛ ያለው በፍቅር የተሰጠ መስዋእት የሆነው ክሪስቶቴስ የሚለው ቃል እንደ 1ጴጥ 2፡3 አባባል ቸር - ወይም ቸርነት ተብሎ ተተርጉሞዋል። "ጌታ ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ. . ." ተመሳሳይ የሆነ የብሉይ ኪዳን ክፍል በመዝ 34፡8 "እግዚአብሔር ቸር እንደሆነ ቅመሱም እዩም" ይላል። ስለ ቸርነት ይናገራል። እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በግል የጌታን ቸርነት በሕይወት ስበመስማመድ የሚናገሩ ክፍሎች ናቸው።

(1). የመንፈስ ፍሬ የሆነውን ቸርነት ጥሩ አድርገው የሚገልጹት ሁለት ምርጫዎች የትኞቹ ናቸው?

ሀ. የጣፋጭነት፣ የርኅራሄና የልስላሴ ባህሪ ነው።
ለ. የባርነት ቀንበር ነው።
ሐ. የወጥ በጎነትና ንፅህና ምልክት ነው።
መ. ስሌሎች የሚገበሰ ውጭያዊ ፍቅር ነው።

በጎነት

በጎነት እንደ መንፈስ ፍሬ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አራት ጊዜ ብቻ ነው የተጠቀሰው። አጋቶስኒ ከሚለው የግሪክ ቃል የተተረጎመ ነው። ክሪስቶቴስ ከሚለው ቃል ጋር ሊነፃፀር በጎነት የቸርነት መገለጫ ወይም ድርጊት ወይም መልካም የሆነውን ማድረግ ነው። አጋቶስኒ በሚከተሉት የጳውሎስ ጹሑፎች ውስጥ ተጠቅሷል።

1. ሮሜ 15፡14 እኔም ራሴ ደግሞ፣ ወንድሞቼ ሆይ፣ በበጎነት (አጋቶስኒ) ራሳችሁ እንደተሞላችሁ . . .
2. ገላ 5፡22 የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትእግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት (አጋቶስኒ). . . ነው።
3. ኤፌ 5፡9 የብርሀኑ ፍሬ በበጎነትና (አጋቶስኒ) በፅድቅ በእውነት ሁሉ ነውና።

4. 2ተሰ 1፡11 የበጎነትም (እጋቶሱኒ) ፈቃድ ሁሉ፣ የእምነትንም ስራ በሃይል ይፈፅም ዘንድ ስለ እናንተ ሁልጊዜ እንፀልያለን።

በመጀመርያው ጥቅስ ሮሜ 15፡14 ጳውሎስ የሮሜ ክርስቲያኖች እርስ በርስ አንዱ ሌላውን ስማገልገል ዝግጁ መሆናቸውን ተረድቶታል። በቁ.15 የራሱን ጥሪ ማስትም የክርስቶስ አገልጋይ መሆኑን በማስታወስ እንዲያገለግሉ ይመክራቸዋል። በቁ. 16 ጳውሎስ ራሱን የዳኑ አህዛብን በመንፈስ ቅዱስ እንደተቀደሰ መስዋእት ለእግዚአብሔር አድርጎ እንደሚያቀርብ ከካህን ጋር ያነጻጽራል። በሁሉም ጥቅሶች ውስጥ የበጎነት መገለጫ ታይቷል። በጎነት ስለአገልግሎት ወይም እርስ በርስ ስለ መተሳሰብ ይናገራል። የልግስና መንፈስ፣ ርኅራኄ፣ ልስላሴ ወይም የበጎነት ተፈጥሮአዊ ውጤት ነው። ይህ ሁሉ ፍቅር በሚለው ቃል ይጠቃለላል። ፍቅር ቸር ነው፣ ይህም የክፋት ተቃራኒ ነው። ፍቅር በጎ ነው ሁልጊዜም ሌሎችን ማገልገል ይፈልጋል።

(2). ሰቀኝ ለኩል የሚገኙትን የመንፈስ ፍሬዎች በስተግራ በኩል ከሚገኙት ፍቺዎች ጋር አዛምድ።

ሀ. አገልግሎት
ለ. አለደሳች/ጣፋጭ
ሐ. ርህራሄ
መ. ንፅህና
ሰ. ማገልገል
ረ. ለጋስነት
ሸ. የክርስቶስ ቀንበር
ቀ. ማድረግ
በ. መሆን

1. ቸርነት
2. በጎነት

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማነፃፀርያዎች

ዓላማ 2 መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን የቸርነትና የበጎነትን ሀሳብ ለመለየት።

በክርስቶስ ውስጥ ፍፁምና ስየት ያለ የቸርነትና የበጎነት ምሳሌ ይታያል። ከቸርነቱም ጋር ፍፁም በጎምግባራዊ ባህርይ ነበረው። ስስዚህም ጠላቶቹን እንዲህ ሲል በመጠየቅ ቆም ብለው እንዲያስቡ አደረጋቸው። "ስለ ኃጢአት የሚወቅሰኝ ማን ነው?" (ዮሐ 8፡46)።

በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለፀው የእግዚአብሔር ቅድስና በጣም አስደናቂና አስገራሚ ነው። ስምሳሌ በቤተ ሳሚስ 70 ሰዎች የእግዚአብሔርን ታቦት ስስተመለከቱ ሞተዋል (1ሳሙ 6፡19)። ይህም ሴሎችን እንዲህ ሲሉ እንዲጠይቁ አድርጓቸዋል። "ብዚህ ቅዱስ እምላክ በእግዚአብሔር ፊት መቆም ማን ይችላል?" (ቁ.20) ስዚህ ጥያቄ መገሙሪኛው ዳዊት በመዝ 15፡1-5 በከፈል መልስ ይሰጣል። ሁለት መስፈርቶች አሉ።

1. በፅድቅ መኖር - "ቅንነት የሚሄድ፣ ፅድቅንም የሚያደርግ፣ በልቡም እውነት የሚናገር፣ በአንደበቱ የማይሸነግል፣ (ቁ. 2 እና 3)።

2. ቸር መሆን-"በባልንጀራው ላይ ክፋትን የማያደርግ፣ ዘመዶችንም የማይስድብ፣ ኃጢአተኛ በፈቱ የተናቀ፣ እግዚአብሔርንም የሚፈሩትን የሚያከብር፣ ስባልንጀራው የሚምል የማይከዳም፣ ገንዘቡንም በአራጣ የማያበድር፣ በንፁህ ላይ መማለጃን የማይቀበል (ቁ. 3-5)።

ስለዚህ ቸርነት ትክክል የሆነውን ነገር የማድረግ ፈቃደኝነት ነው። ክፉውን የማድረግ ተቃራኒ ነው። በምሳ 4:16 እንደተገስፀው "ክፉ ካላደረጉ አይተኙምና ፣ ካላስናከሱም እንቅልፋቸው ይወገዳልና።"

ኢየሱስ ቸርነቱን የገለፀበት አንዱ መንገድ በመንካት ነው። እጆቹን በህፃናት ላይ ይጭን ነበር። ያዘኑትንና የታመሙትን ይነካ ነበር። ፍቅራቸውን ለመግለፅ ስሚፈልጉ እና ፈውስ ክእርሱ የሚጠብቁ ሁሉ ይዳስሱት ነበር። እንዲህ እይነቱ የተቸገሩትን በእኛ ውስጥ ሆኖ መድረስ እንዴት መልካም ነው።

በጎነት ከቸርነት እንድ ደረጃ ይራመዳል። ዊሊያም በርክሌይ እንዲህ ሲሉ ገልጸውታል። (1976 ገፅ 51) "ብየትኛውም ሁኔታ ያማረ በህሪ ነው" ብለዋል። በመቀጠልም "የቸርነትና የበጎነት ልዩነታቸው ምንድን ነው? በጎነት ሊገስፅና ሊገራ ይችላል፣ ቸርነት ግን የዘወትር ተግባሩ መርዳት ነው" (ገፅ 51)። ኢየሱስ ወደ መቅደስ ገብቶ የሚሸጡትንና የሚገዙትን አስወጣቸው። ይህን በማድረጉ በጎነት አሳያቸው (ሉቃ 19፡45-46)። ስታመነዝር የተያዘችውን ሴት ይቅር ሲላት ቸርነት አሳይታል (ዮሐ 8፡10-11)። በፈተናው ጊዜና ፊቱን በጥፊ ስመታው ሎሌ ሁሉ በጎነት አሳይቷል (ዮሐ 18:23)። ቀደም ብሎ በአትክልቱ ስፍራ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ ስይፉን መዝዞ የሊቀካህናቱን ባርያ ጆሮ ሲቆርጥ ኢየሱስ የስወየውን ጆሮ በመዳስስ ሲፈውበው ቸርነት በህይወቱ ተገልጿል (ሉቃ 22:51)። በርክሌይ ሲያጠቃልሉ እንዲህ ይላሉ። ክርስቲያኖች ዳግ እና ጠንካራ የሆነው በጎነት ያስፈልጋቸዋል (ገፅ 51)። ይህም እግዚአብሔር ለኛ ባሰየው ድርጊት ይታያል። በሚገስጸን ጊዜና በሚገራን ጊዜ ቸርነት እኛን ወደ ንስህ ለማድረስና የእርሱን ታላቅ ቸርነት በሕይወታችን ለመግስፅ ነው (ሮሜ 11:32 እና መዝ 25፡8 ተመልከት)።

(3). ይህንን ንፅፅር በምሳሌ ለመግስፅ መዝሙረ ዳዊት 23 እንመልከት። ጌታ በእረኛ ተመስሎ እናያለን። ከታች ከተገስፁት መግስጫዎች ውስጥ የትኛው ስለ ቸርነት የትኛው ደግሞ ስለ በጎነት ይናገራል?

ሀ. የዋህነት ያለበት መንፈስ ወይም ተፈጥሮ
ለ. መምራት
ሐ.ማቅናት (ማረም)
መ. ምህረትን ማሰየት

(4). መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ቸርነትና በጎነት በተመለከተ ከተጠቀሱት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ የትኛቹ ዐረፍተ ነገሮች እውነት ናቸው? በምርጫው ፊት የሚገኙት ፊደላትን አክብብ።

ሀ. ጽድቅ በተቀደሰ ሀልዎተ እግዚአብሔር ለመቆም የሚያስችል ነው። እንደ መዝ 15፥1-5 ፅድቅ ቸርነትን ያካትታል።
ለ. ጌታ እኛን የእርሱን ምህረት ለሌሎች እንድናሳይ ይጠቀምብናል።
ሐ. ቸርነት (ክሪስቶቴስ) በእግለሰብ ከበጎነት (አጋቶሱኒ) ይልቅ ይጠነ ክራል።
መ. መግለፅ እና መግራት ከጌታ በጎነት ጋር ይያያዛል።
ሠ. እግዚአብሔር እኛን በሚያርትበት ጊዜ ዋናው እላማው ቅጣት ነው።

ቸርነት እና በጎነት ሲገለፅ

የእግዚአብሔር በጎነት እና ቸርነት

ዓላማ 3 የእግዚአብሔርን በጎነት እና ቸርነት መለንና ለፍት ለመግለፅ።

ቸርነት - አንዳንድ ሰዎች ሰለ እግዚአብሔር የተዛባ አመለካከት አላቸው። እግዚአብሔርን ምህረት እንደሌለው፣ ጨካኝ ዳኛና ኃጢአተኞችን እየከነነ ወደ ውጭ ጨለማ እንደሚልክ አድርገው ይቆጥሩታል። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ሩህሩህ፣ አፍቃሪ፣ ሰማያዊ አባትና በማንኛውም መልኩ ልጆቹን ለመባረክ የተዘጋጀ ነው። መዝ 103፥13 እንዲህ ይላል። "አባት ለልጆቹ እንደሚራራ እንዲሁ እግዚአብሔር ለሚፈሩት ይራራል።"

(5). መዝ 103፥8-11ን አንብብና በምንባቡ የተጠቀሱትን የእግዚአብሔርን ቸርነት የሚገልፁትን ባህርያት ግለፅ።

ነብዩ ኢሳያስ እግዚአብሔርን እንደ ሩህሩህና ደግ፣ ከበጎች ጋር ያለ እረኛ አድርጎ ያቀርበዋል። "መንጋውን እንደ እረኛ፣ ጠቦቶቹን በክንዱ ሰብስቦ በብብቱ ይሸከማል፣ የሚያጠቡትንም በቀስታ ይመራል" (ኢሳ 40፥11)። ሉቃ 11፥13 እግዚአብሔር ቸርነትን ሊያሳይ ፈቃደኛ እንደሆነ የሚያሳይ ሌላ ምሳሌ ነው። "እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ፣ በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸዋል?"

በማሪው የእግዚአብሔርን ቸርነት በመደጋገም እንዲህ ሲል ይገልፀዋል። "እግዚአብሔር እንደኔት ቸር ነው (መዝ 73፥1፣ 86፥5፣ 106፥1፣ 107፥1፣ እና 136፥1 ተመልከት)። በመዝሙሮች ውስጥ ሁሉ ይህ እስደሳች ዜማ ተገልጿል። በዚህም በማሪው የእግዚአብሔርን ቸርነት ለይቅርታውና ፀሎትን ለመመለስ መሰረት እንደሆነ ይጠቅሳል። የእግዚአብሔር ፍርድ መልካም ነው። በመዝ 119፥39 ዳዊት ስለ ድካሙ ሲናገር እንዲህ ብሎ ያጠቃልላል። "የእግዚአብሔር ፍርድ መልካም ናትና።" ዳዊት በዚህ ስፍራ ንስሀ ለሚገባ ኃጢአተኛ ተሰፋ የሚለጠውን የቸርነቱን ባህርያት ይናገራል።

የእግዚአብሔር ቸርነት ለሰዎች ሁሉ ተዘርግቷል። "ስክፉዎችም ቸር ነውና" (ሉቃ 6፥35)። ነገር ግን የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንሰሐ ይመራናል (ሮሜ 2፥4)። ይህ ስማያዊ ቸርነት ለደህንነታችን የሚሰራና ወደ ኃጢአት ይቅርታ የሚመራ ብቻ ሳይሆን ለቅድሰናችንም የሚሰራ ጭምር ነው። ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቸርነት መከታ በማድረግ በተደጋጋሚ ኃጢአትን ይሰራሉ። ይህም እደገኛና ትልቅ ሰህተት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ሲል ያስጠነቅቀናል። "እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቸርነትና ጭከና ተመልከት፣ ጭከናው በወደቁት ላይ ነው፣ በቸርነቱ ግን ፀንተህ ብትኖር የእግዚአብሔር ቸርነት በአንተ ላይ ነው፣ ያለዚያ አንተ ደግሞ ትቆረጣለህ" (ሮሜ 11፥22)።

በጎነት - እያንዳንዱ ከፀሐይ በታች የሚኖር ሰው ለተትረፈረፈውና ስማያቋርጥ በረከቱ እግዚአብሔር ባለውለታው ነው። መዝ 145፥9 እንዲህ ይላል - "እግዚአብሔር ስሚታገሱት ቸር ነው። ምህረቱም ስሰራው ሁሉ ላይ ነው" "ስክፉዎችና በበጎዎች ላይ ፀሀይን ያወጣልና፣ ስማድቃንና በታጥያተኞች ላይ ዝናቡን ያዘንባልና" (ማቴ 5፥45)። እመፀኛ ሰው እንደዚህ ያለ በረከት አይገባውም ነገር ግን የእግዚአብሔር በጎነት በነፃ ለሁሉም ደርሷል። በዮሐ 1፥16 እንዲህ ተፅፎዋል - "እኛ ሁላችን ከሙላቱ ተቀብለን በፀጋ ላይ ፀጋ ተለጥቶናልና።" እያንዳንዱ ሰው እንደዚህ ላለ በረከቱ ስለጤና፣ ስለዝናብ፣ ስለሰብል፣ ስለቤተሰብ፣ ስየእለቱ ስለሚሰጠን ነገሮች ሰለጥበቃውና፣ ሌላ ከእርሱ ሰለተቀበልናቸው በረከቶች ያለ ማቋረጥ ማመሰገን ይኖርበታል። ሐዋርያው ያዕቆብ እንደዓፈው "በጎ ስጦታ ሁሉ ፍፁምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፣ መለወጥም በእርሱ የተደረገ ጥላ ስእርሱ ከንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ"።

(6). ሀ. የእግዚአብሔር ቸርነትና በጎነት ለሰዎች ሁሉ - በክፉዎችም ሆነ በበጎዎች ላይ ስምን እንደተሰጠ ግለፅ?

ለ. የእግዚአብሔር ቸርነትና በጎነት በእመፀኛ ሰዎች ላይ ያለውን ውስንነት ግለፅ?

የቸርነት እና በጎነት መርሆዎች

ዓላማ 4 ከመገረሰ ፍሬዎች ከቸርነትና ከበጎነት ጋር የተዛመዱትን እውነተኛ መመሪያዎች ለይቶ ለማወቅ።

ሌሎችን ማገልገል

ቸርነትና በጎነት ሊነጣጠሉ እይችሉም። እዚህ ላይ ሁለት መለኮታዊ መመሪያዎች አሉ።

1. የግል ድኅነትና 2 ሌሎችን ማገልገል። በጎነት ከመጀመርያው ጀምሮ እግዚአብሔር ስሰው ያለው እቅድ ነበር። የሰው መንፈሳዊ ሁኔታ ማህበራዊ ግንኙነቶቹ ላይ ተፅእኖ አለው። ይህንንም ምሳሌ በሁለት ታላቅ ትእዛዞች ውስጥ እናየዋለን (ማር 12:29-31 ተመልከት)።

ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ግንኙነት	ከሰዎች ጋር ያለ ግንኙነት
1. እግዚአብሔር እምላክህን ውደድ	2.ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ

ይህ መመሪያ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በበለጠ በሁለት ጥንድ ጥያቄዎች ተገለጿል።

ከእግዚአብሔር ጋረ ያለ ግንኙነት	ከሰዎች ጋር ያለ ግንኙነት
ዘፍ 3፥9 ወዴት ነህ?	ዘፍ 4፥9 ወንድምህ ወዴት ነው?
ሉቃ 10፥25 የዘላለም ሕይወት እን ድወርስ ምን ላድርግ?	ሉቃ 10፥29 ባልንጀራዮስ ማን ነው?

ቦተጠቀሰው የዘፍጥረት ምሳሌ ሳይ እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን እርሱን ሳይታዘዙ ኃጢአት ባደረጉ ጊዜ ወዲያው የጠየቃቸው የመጀመርያው ጥያቄ ነው። የእርሱ ጥያቄም የእነርሱ የመንፈሳዊ ደህንንት ሁኔታ ግድ እንዳለው የሚገልፅ ነው። ሁለተኛ ጥያቄውን ቃየል ወንድሙን ከገደለው በኋላ ወድያው የጠየቀው ጥያቄ ነው። የእግዚአብሔር ጥያቄ እርሱ በወንድሙ ላይ ስለሰራው ክፋት ግድ እንደሚለው የሚያሳይ ነው።

በሉቃስ ላይ በተጠቀሰው ምሳሌ እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች የህግ አዋቂው ኢየሱስን የጠየቃቸው ናቸው የመጀመርያው ከመንፈሳዊ ሁኔታዎች ጋር ሁለተኛው ደግሞ ከማህበራዊ ሁኔታ ጋር የተያያዘ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት በመጀመርያ ሊታይ ይገባው ነበር። አምላክህን በፍፁምልብህ፣ በፍፁም ነፍስህም፣ በፍፁም ኀይልህም በፍፁም አሳብህም፣ ውደድ። ከዚያም ከሌሎች ጋር ያለው ግንኙነት ይቀጥላል። ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ።

ከዚህ የምንማረው የመንፈስ ፍሬዎች የሆኑትን የቸርነትና የበጎነት ጠቃሚነትን ነው። የመንፈስ ፍሬ በውስጣችን ባፈራ ጊዜ ሌሎቹን እግዚአብሔር እንደሚያያቸው በመመልከት ፍቅሩ በእኛ ተገልጾ እንዲደርሳቸው አገልግሎታችን የሚያመራው ሌሎችን ጌታን እንደግል አዳኛቸው እንዲያውቁ ወደ ማድረግና የሚያስፈልጋቸውን አገልግሎት ወደ መስጠት ነው። ይህም ህብረትን፣ መበተንግዶን፣ በችግራቸው መርዳትን፣ ማበረታታትንና ከሁሉም በላይ ደግሞ ፍቅር ማሳየትን ያካትታል።

(7). መለኮታዊ በሆኑት የደኅንነትና ሌሎችን የማገልገል ሁለት መርሆዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ግለፅ።

የዳንነው ጥሩዎችና ቅዱሳን ስለሆንን ሳይሆን ኢየሱስ ታዳጊያችን ሆኖ በምትካችን ስለሞተልን ነው። ክርስቲያኖች እንደመሆናችን መጠን የክርስቶስን ፍቅር ለመንፈስ አማካኝነት ለዓለም እናንፀባርቃለን። ይህንን የምናደርገው ደህንነት ለማግኘት ሳይሆን በለዳንን ነው። የዳንነው ከምናደርገው ነገር የተነሳ ሳይሆን በእምነትና በፀጋው ኢየሱስ ከሰራልን የማንጸት ተግባር የተነሳ ነው።

ለጋስነት

ሌሎችን የሚያገለግል ጥሩ የሆነ ሰው ምድራዊ ንብረት እንኳ ባይኖረው ሀብታም ነው። በራእ 2፥9 የተጠቀሱት የሰምርኔስ ቤተክርስቲያን ክርስቲያኖችም ሁኔታ ይህ ነበር። "መከራህንና ድህነትህን አውቃለሁ፣ ነገር ግን ባለ ጠጋ ነህ።" የመቄዶንያም ቤተክርስቲያን ከእነሱ ትመደባለች። በ2ቆሮ 8፥2-3 ጸውሎስ እመሰግኖዋቸዋል። "በብዙ መከራ ተፈትነው ባሉ የደስታቸው ብዛትና የድህንታቸው ጥልቅነት የልግስንታቸው ባለጠግነት አብዝቶታል፤ እንደ አቅማቸው መጠጥ ከአቅማቸውም የሚያልፍ እንኳ ወደው እንደ ሰጡ እመሰክርላቸዋለሁና።"

ከላይ የተጠቀሰው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንደሚያመለክተው ልዩ የሆነ የክርስቲያን ባህሪ በንነት ወይም አጋቶሱኒ ለጋስነት ነው። አስራትና መባ መስጠት ያለን ሁሉ ነገር ከእግዚአብሔር እንደመጣ የምናሳውቅበት መንገድ ነው። አስራኤሳውያን ለመቅደሱ ማሠሪያ ስጦታቸውን ነፃመጡ በኋላ ዳዊት ሰለ ስጦታዎቹ ጌታን አመሰገነ። እንዲህም አለ "ሁሉ ከእንተ ዘንደ ነውና፣ ከእጅህም የተቀበልነውን ሰጥተንሀልና ደህን ያህል ችለን ልናቀርብልህ እኔ ማን ነኝ? ሕዝቤስ ማን ነውን?" (2ዜና 29፥14)። ዳዊት የሚናገረው ዋስትናቸው እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ነው። ሰዎች ግን ብዙ ጊዜ ባጠራቀሙት ሀብት ዋስትና ለማግኘት ይሞክራሉ። መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያ እንደሚለው እውነተኛ ዋስትና የሚገኘው በልግስና በመስጠት ወይም በእጅ መፈታት ነው። እግዚአብሔር የሚባርከው ለጋሶችን ነው። ይህም መሠመርያ በዘዳግም 15፥10-11 ተጠቅሷል።

> አምላክህ እግዚአብሔር ስለዚህ በስራህ ሁሉ ይባርክሃልና ፈፅመህ ስጠው፣ ሰስጠኸው ጊዜ በልብህ አትፀፀት። ድሆች ከምድሪቱ ላይ አያልቁምና ስለዚህ እኔ ዘእገርህ ውስጥ ላሰው ድሀ ለተቸገረው ወንድምህ እጅህን ትከፍታለህ ብዬ አገዝሃለሁ።

ሰው የሚጠፋውን የዚህ ዓለምን ነገር አጥብቆ አለመያዝን ጠቃሚነት መረዳት የሚጀምረው ሊሰጥ ነው። ኢየሱስ "ብልና ዝገት በሚያጠፉት ሌቦችም ቆፍረው በሚሰርቁት ዘንድ ለእናንተ በምድር ላይ መገብገብ አትሰብስቡ ሌቦች ቆፍረው በማይሰርቁት ዘንድ ለእናንተ በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ፤ መዝገብህ ባለበት ልብህ ደግሞ በዚያ ይሆናልና" በማለት ተናግሮናልና (ማቴ 6፥19-21)።

በብዙ የዓለም ክፍሎች የጌታ ስራ ከስግብግብ ክርስቲያኖች የተነሳ ይበደላል። ምንም አይሰጡም ምንም ደግሞ አይቀበሉም ። ቸርነት በእግኝ ሕይወት ውስጥ የመንፈስ ፍሬ ሆኖ ሲናር እንደሚቁዶንያ ቤተ ክርስቲያን በልግስናው ይታወቃል።

(8). ለወንድሞቹ እጅን የሚዘረጋና ለእግዚአብሔር ሥራ እንዲሠራ በልግስና የሚሰጥ ሰው ሽልማቱ ምንድን ነው?

በጎነት፣ ዕድቅ እና እውነት

በበጎነት፣ በዕድቅና በእውነት መካከል ዝምድና ያለ ሲሆን፣ ይህም ጠቃሚ የሆነ መመርያ ያስተምረናል። ኤፌ 5:9 እንደሚለው "የብርሃኑ ፍሬ በበጎነትና በዕድቅ በእውነት ሁሉ ነውና" በጎነት ከምሀረት ጋር ይዛመዳል፤ ዕድቅ ከፍትህ ጋር ይዛመዳል፤ እውነት ደግሞ ከእውቀት ጋር ይዛመዳል። ይህንን በሚከተለው ስንጠረዥ ሲገለፅ የእግዚአብሔር በጎነት ለእኛ ምን ማለት እንደሆነ ታስተውሳለህ።

በጎነት	ዕድቅ	እውነት
ምህረት	ፍትህ	እውቀት
ለሰው የሚጠቅመውን ሁሉ ስጠው ሀግን ያልፋል	ለሰው የሚገባውን ስጠው ከህጉ ጋር ተጣበቅ	ሀግ እውነት አለው ፀጋ ግን የለውም
ከፀጋ ጋር የተዋሀደ ነው። ምህረት፣ የሚገባንን አላገኘንም። ፀጋ፣ የማይገባንን አግኝተናል።		በኢየሱስ እውነት እና ፀጋ አለን

"ህግ በሙሴ ተሰጥቶ ነበርና ፀጋና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ" (ዮሐ 1፥17)። ሀግ እውነት አለው እንጂ ፀጋ የለውም። በኢየሱስ ግን እውነትና ፀጋ አሰን፣ ከብር ለእግዚአብሔር ይሁን! በጌታ ኢየሱስ በተገለጠው በእግዚአብሔር ፀጋ እማካኝነት የሚገባንን ሳይሆን ያገኘነው የእርሱ ፍቅርና ፀጋው በነፃ የሰጠንን ነው።

የበጎነት ብልጫ ወርቃማው ሀግ በሚባለው ተጠቃልሉ ይገኛል፡ "ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እድርጉላቸው፤ ህግም ነቢያትም ይህ ነውና" (ማቴ 7፥12)። በሌላ አባባል ሰዎችን የምንይገበት መንገድ እግዚአብሔር እኛን በምህረቱና በፀጋ እንደያዘን ዓይነት ነው።

(9). በስተቀኝ ያለውን ሰስተግራ ካለው ከሚዛመደው ቃል ወይም ገስፃ ጋር አዛምድ። የመረጥካቸውን ቃላት ቁጥር በክፍት ቦታው ሳይ ፃፍ።

____ሀ. የሚገኘው በህግና በኢየሱስ ነው።	1) በጎነት
____ለ. ምህረት እና ፀጋን ይይዛል።	2) ዕድቅ
____ሐ. ህግን ያጠቃልል።	3) እውነት
____መ. ከእውቀት ጋር ይዛመዳል።	
____ሠ. የሚገባውን ይሰጣል።	
____ረ. የሚገባውን አይሰጥም።	

(10). አዚህ ሳይ የተጠቀሰት አንዳንድ አረፍተ ነገሮች እውነት ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ሀሰት ናቸው። እውነተኛ ከሆኑት አረፍተ ነገሮች ፊት ያለውን ፊደል አክብብ።

ሀ. እግዚአብሔርን ስመምሰልና በበጎነት መካከል ያለው ግንኙነት የእግዚአብሔርን የደኅንነት ስጦታ ስንቀበል እኛም ለሌሎች በተስጠን መጠን ፍቅር ማሳየት ነው።
ለ. ለጋስነት ማለት የዚህ ዓለም ጥሪታችንን አጥብቀን ስንይዝ ዋስትና እናገኛለን ማለት ነው።
ሐ. የለው ማህበራዊ ግንኙነት መሆን እንደሚገባው ከሆነ ለመዳን የሚያስፈልገውን አድርጓል ማለት ነው።
መ. ለኃጥአታችን ይቅርታ እንድናገኝ የእግዚአብሔር ዕድቅ ከምህረቱ ጋር መዋሃድ አለበት።
ሠ. እውነተኛ የልማስና ምልክት ለራሱ ያልተሟላ ፍላጎት አያለውም እንኳን በደስታ ሊሰጥ ነው።
ረ. አስደናቂው እግዚአብሔር ለኛ ያለው ታሳቅ በጎነት እርሱ መህረኑት፣ ባለፀጋነቱ፣ የሚገባንን ከመክፈል ይልቅ የማይገሳንን ምህረት መስጠቱ ነው።

ቸርነትና በጎነት በምሳሌ

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎች

ዓላማ 5 በተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ ቸርነትና በጎነት በምን አይነት መንገድ እንደተቀመጡ ለመግለፅ።

መጽሐፍ ቅዱስ ለወገኖቻቸው ቸርነትና በጎነት ባደረጉ የእግዚአብሔር ሰዎች ምሳሌ የተሞላ ነው። ከእነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ ጥቂቶቹን ወስደን የመንፈስ ፍሬ በሕይወታችን የሚታይበትን መንገድ እንመለከታለን።

ኢዮብ - ትእግስተኛ ሰው ብቻ ሳይሆን የቸርነትና የበጎነት ምሳሌም ነው። ራሱን እንደሚከተለው ገልያታል።

> ለእውር እይን፣ ለእንካሳ እግር ነበርሁ። ለደሀው አባት ነበርሁ፤ የህጢአተኛውን መንጋጋ ሰብርሁ፣ የነጠቀውንም ከጥርሱ ውስጥ አስጣልሁ። መዓተኛው ግን በሚዳ እያድርም ነበር፣ ደጁንም ለመንገደኛ እከፍት ነበር፤ (ኢዮ 29፥15-17፣ 31፥32)።

ዳዊት - የዳዊት ቸርነት ለጠላቶቹ ቤት በሳኦል እንኳ መድረሱ ልብ የሚነካ ነው። ዳዊት ይህንንም አድልዎ የሌለበት ቸርነት - የእግዚአብሔር ቸርነት (2ሳሙ 9፥1-3) ብሎታል። ይህ የቸርነት ከፍተኛው ደረጃ ነው። ያለእድልዎ መደረግ ስላለበት ቸርነት ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ እንዲህ ሊል ያስተምረዋል። "የጌታም ባርያ ለሰው ሁሉ ገር ለማስተማርም የሚበቃ በትእግስትም የሚዐና ሊሆን እንጂ ሊጣላ አይገባውም" (2ጢሞ 2፥24)። እንደ መንፈስ ፍሬ የማያዳላ ቸርነት በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ሊገበፅ ይችላል።

የዳዊት ውሳኔ በ2 ሳሙኤል 24 ውስጥ በእግዚአብሔር እጅ መውደቅ ነበር። "ምህረቱ ብዙ ነውና በእግዚአብሔር እጅ እንውደቅ በሰው እጅ ግን አልውደቅ" (ቁ. 14)። ዳዊት የእግዚአብሔርን ቸርነት በሕይወቱ

ብዙ ጊዜ ተለማምዷል። ስለዚህ ከሰው ይልቅ በእግዚአብሔር የምህረት እጅ መውደቅን መረጠ።

ጳውሎስ - ከመለመጡ በፊት የሚታወቀው በክርስቲያኖች ሳይ ባለው ጭከናው እንደነበር ራሱ ይመሰክራል። ነገር ግን በክር ስቶስ እንዳለ አዲስ ፍጥረት ይህንን ምስክርነት ይሰጣል (1ተሰ 2፥7)።

ሊያሰብ - ከመሞቱ በፊት ባደረገው በመጨረሻው ድርጊት ቸርነትን አሳይቷል። በመበቀል ሳይ በተሰቀለ ጊዜ ለእንዱ እናቱን አደራ ብሎታል (ዮሐ 19፥28-27)። ለተበቀሉትም ይቅርታ ለምኖላቸዋል (ሉቃ 23፥34)።

እስጢፋኖስ - ጌታውን በመከተል ቸርነትን ያሳየ ሌላው ግሩም ምሳሌ ነው። የአባዳጆችን ሞት ከመመኘት ይልቅ በድንጋይ ሊወግሩት ስለእነርሱ ፀለየ (የሐዋ 7፥59-60)።

(11). ከታች የተጠቀሱትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በማንበብ በእያንዳንዱ ምንባብ ስለተገለፀው ሰው ቸርነትና በጎነት ምን እንደሚሉ ግለፅ።

ሀ. በወንድሞቹ ለባርነት የተሸጠው የያቆብ ልጅ ዮሴፍ (ዘፍ 45፥21-23)።
ለ. ረዓብ (ያዕ 2፥25፣ ኢያ 2 ንም ተመልከት)።
ሐ. ሱነማዊቷ ሴት (2ነገ 4፥8-10)
መ. ዶርቃ (የሐዋ 9፥36)
ሠ. የጥንቶቹ በኢየሩሳሌም የነበሩ ክርስቲያኖች (የሐዋ 2፥44-45፣ 4፥32-35)

ከግል ሕይወት ጋር ማዛመድ - በፍቅር ማገልገል

ዓላማ 6 ስፍቅር በማገልገል ላይ ተመርኩዞ በግል ሕይወታችን ውስጥ ስሥራ በመተርጎም።

የቸርነትና የበጎነት መንፈሳዊ መልኩ ክርስቲያናዊ አገልግሎትን የሚመለከት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ እርስ በእርስ የማገልገልን ጠቃሚነት በእጽንእት ሲገልጽ እንዲህ ይሰል፦

> ወንድሞች ሆይ እናንተ ለእርነተ ተጠርታችሃልና፣ ብቻ እርነታችሁ ለስጋ ምክንያትን አይስጥ፣ ነገር ግን በፍቅር እርስ በርሳችሁ እንደ ባርያዎች ሁኑ። ህግ ሁሉ በአንድ ቃል ይፈፀማልና፣ እርሱም ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ የሚል ነው። ነገር ግን እርስ በርሳችሁ ብትነካከሱና ብትበላሉ እንዳትጠፉ ተጠነቀቁ" (ገላ 5፥13-15)።

ማገልገል በዚህ ክፍል ውስጥ የሚመለከተው ባርያ የሚለጠውን አገልግሎት ነው። ይህ ወደ ብሉይ ኪዳን ይወስደናል። ጌታ አበርቱን ትእዛዝት ከሰጠ በኋላ ስለባእድ አምልኮና መበዊያ ተናግሯል። ከዚያም ስስ ዕብራውያን እገልጋዮች ህግ ተናግሯል (ዘፀ 21፥1-6)። ከዕብራውያን መካከል እስራኤላዊው ሴባ ወይም እዳውን መክፈል ያልቻስ ባስእዳ ካልሆነ በቀር ባርያ የለም። በዚህ ሁኔታ ግን ቢበዛ ስስደስት ዓመታት ያህል ሊሸጥ ይችላል። በነዚያ ጊዜያቶች እዳውን እስከ ሰባት እመት እስኪከፍል ድረስ እንደተቀጠረ ሰራተኛ ይቆጠራል። ከዚያ በኋላ በቀጥታ በነፃነት ይለቀቃል። ባርያው ጌታውን ወዶ ከእርሱ ጋር ሊኖር ቢፈልግ ወደ ዳኛ ይወሰድና ጆሮው ይበሳል። ከዚያ ቀን በኋላ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ በምርጫው ለጌታው ይሆናል። እንዲህ እደነኑ ስው የፍቅር ባርያ ይባላል።

በመዝ 40፥6-8 ስለሚመጣው መሲህ ቢናገር ዘማሪው ራሱን እንደ ፍቅር ባርያ ይሰጣል። "መስዋእትንና ቁርባንን እልወደድህም ስጋን አዘጋጀህልኝ . . . በዚያን ጊዜ አልሁ እነሆ መጣሁ፣ . . እምሳኬ ሆይ ፈቃድህን ለማድረግ ወደድሁ።" ኢየሱስ ራሱ የመጣው እንደ የፍቅር ባርያ ነው። በእርግጥ በኢሳ 42፥1 እና 52፥13 ጌታ ባርያ ተብሱ ተጠርቷል። ይህንን በማቴ 20፥28 እረጋግጦታል። ". . . የስው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ስብዙዎች ቤዛ ሊስጥ እንጂ እንዲያገለግለት እልመጣም።"

ሐዋርያው ጳውሎስ የገሳትያን ስዎች በፍቅር እርስ በርሳቸው እንዲያገለግሱ ነግሯቸዋል። ከዚያም አንዱ የሌላውን ሸክም እንዲሸከም ዕርላቸዋል (ገላ 6፥2)። በዚህ ቦታ ሸክም የሚለው ቃል የመጣው ባርስ ከሚለው ሲሆን ይህም ማለት ከብደት ማለት ነው። በገላ 6፥5 እያንዳንዱ የገዛ ራሱን ሸክም ሊሸከም ነውና፣ ቢል ስስድርሻ መናገሩ ነው። ስለዚህም የድርሻችንን ሸክም በመሸከም ከሌሱች ጋር ልንካፈል ይገባናል።

በፍቅር ማገልገል የበጎነት መገለጫ ሲሆን፣ መጀመር ያለበትም ከቤተሰባችን ውስጥ ነው። የመንፈስ ፍሬዎችን ስመለማመድ ቤታችን የተመረጠ ቦታ ነው። በቤታቸው ደግነትና ቸርነት ከማሳየት ይልቅ አንዳንድ ክርስቲያናች ስውጭ ሰዎች ቸርነትን ማሳየት ይቀላቸዋል። በፍቅር ማገልገል ስቤተሰብህ የምትገልጠው መንፈሳዊ ፍሬያማነት ነው።

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በፍቅር የማገልገልን ጠቃሚነት እንዲህ ሲል እጠቃልሱታል። "ባንገዘልም በጊዜው እናጭዳስንና መልካም በራን ለመስራት አንታክት። እንግዲያስ ጊዜ ካገኘን ዘንድ ለስው ሁሉ ይልቁንም ለሀይማኖት ቤተሰዎች መልካም እናድርግ" (ገላ 6፥9-10)።

"ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ይሸፍናልና ከሁሉ በፊት እርስ በርሳችሁ እጥብቃችሁ ተዋደዱ። ያለማንጉራጉር እርስ በርሳችሁ እንግድነት ተቀባበሱ፣ ልዩ ልዩ የእግዚአብሔርን ፀጋ ደጋግ መጋቢዎች እንደ መሆናችሁ፣ እያንዳንዳችሁ የፀጋን ስጦታ እንደተቀበላችሁ መጠን በዚያው ፀጋ እርስ በርሳችሁ እገልግሉ" (1ጴጥ 4፥8-10)።

(12). ከክርስቶስ ጋር ያስንን ግንኙነት መሰረት በማድረግ የክርስቲያን አገልግሎት መመሪያዎችን በራስህ አባባል ግለፅ።

(13). ከዘማሪው ዳዊት ጋር "አምላኬ ሆይ ፈቃድህን ለማድረግ ወደድሁ" ልትል ትችላለህን? እነዚህን ጥያቄዎች ጠይቅና በማስ ታወሻ ደብተርህ ላይ መልስህን ፃፍ። ሰፀሎት ልትመረምራቸው የሚገቡ ጠቃሚ ጥያቄዎች ናቸው።

ሀ. ሌሎቹን ለለማገልገል ያለኝ አመለካከት ምን ይመስላል? በትህትና ገዛ ብዬ ለማገልገል ፈቃደኛ ነኝን? ለለራሁት ነገር አውቅና ማግኘት ለኔ ትልቅ ነገር ነውን?
ለ. ሌሎች በማደርገው ቸርነትና በጎነት ክርስቲያን መሆኔን ያያሉን?
ሐ. እውነተኛ የልግስናና የፍቅር መንፈስ አለኝን?
መ. ከላይ ለስጠሁት መልስ መሰረት የቸርነትና የበጎነትን ፍሬ በሙላት ለማፍራት የመንፈስ ቅዱስን እርዳታ በሕይወቴ በሚከተሉት አትጣጫዎች አፈልጋለሁ (በማስታወሻ ደብተርህ ላይ መልስህን ፃፍ)።

የመከራ ፈተና

አጭር መልስ። እያንዳንዱን ጥያቄ ባጭሩ መልስ።

1. ሶስቱን የቸርነት (ከሬስቶተስ) ፍቺዎች ፃፍ።

2. የበጎነትን (አጋቶሱኒ) ፍቺ ጻፍ።

3. በብሉይ ኪዳን የፍቅር ባርያ ምሳሌ እና የመንፈስ ፍሬ በሆኑት ቸርነት እና በጎነት መካከል ያለውን ግንኙነት ግለፅ።

ምርጫ- ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ ምረጥ።

4. የትኛው ቃል የበለጠ ክበጎነት (አጋቶሱኒ) ጋር ይዛመዳል?

ሀ. ቀንበር ሐ. አገልግሎት
ለ. ሸክም መ. ንፅህና

5. ከእነዚህ ውስጥ የትኛው ለመንፈሳዊ ቸርነት መሰረት ነው?

ሀ. የሞራላዊ ባህርያት መገፃት
ለ. ለጋስነት
ሐ. ለመገለፅ እና ለማረም ፈቃደኝነት
መ. መዳበስ

6. ከሚከተሉት ውስጥ በጎነት (አጋቶሱኒን) በተመለከተ የትኛው ዐረፍተ ነገር ትክክል ነው?

ሀ. በውስጥ ማንነት የተወሰነ ነው።
ለ. በአንድ ጊዜ በጎና ጠንካራ መሆን ይቻላል።
ሐ. አይገበፅም፣ አያርምም።
መ. አገልግሎት የማይሰጥ አይነት ነው።

7. እግዚአብሔር ቸርና በጎ ስለሆነ ፅድቁ ከ ጋር ሚዛናዊ ነው።

ሀ. ጋይለኝቱ
ለ. ከትእዛዛቱ
ሐ. ከምህረቱና ዐጋው

8. የእግዚአብሔርን የመምሰልና የበጎነት ሁለት መለኮታዊ መርሆዎች የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ደኅንነትና አገልግሎት ሐ. ምህረትና ዐጋ
ለ. አገልግሎትና ፍቅር መ. ፅድቅና ዐጋ

9. ለጋስነት የመንፈሳዊ በጎነት ክፍል ሆኖ ሲታይ ምን ማለት ይሆናል?

ሀ. የሚፈለግብኝን ሁሉ እሰጣለሁ።
ለ. ለመስጠት ፍላጎት በተስማኝ ጊዜ እሰጣለሁ።
ሐ. በስወታዱ እስከመስዋእትነት ድረስ እጂ ከፍት ነው።
መ. በደስታ እንድ እስረኛውን ስጌታ እሰጣለሁ።

10. ሀግ እውነት እሰው ነገር ግን _____ የለውም።

ሀ. ፍትህ ለ. ፅድቅ ሐ. በጎነት መ. ፀጋ

11. ዳዊት ለሳኤል ቤት ያሳየው ቸርነት ለእኛ የሚያስተምረን ጠቃሚ ነገር

ሀ. ትእግስት ሐ. ፍትህ
ለ. ያለማዳላት መ. ደህንነት

12. የእግዚአብሔር በጎነትና ቸርነት ለለምች ሁሉ ነው፣ ምክንያቱም _____ ወደ ምን ሊመራን ስለፈለገ ነው?

ሀ. እመጸ ሐ. ንስሀ
ለ. በረከት መ. ፍርድ

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስ

7. በቅድሚያ እግዚአብሔርን መውደድ፣ ቀጥሎም ሌሎችን መውደድ። እግዚአብሔር በጎነቱን ለእኛ ሊያሳየን በዚያው ዓይነት እኛም ለሌሎች ማሳየት ይኖርብናል። ጌታን ደስ ማሰኘት ከፈለግን ሁለቱም እስፈላጊዎች ናቸው።

1. ሀ እና ለ

8. እጹን በዘረጋበት ነገርና በሚስራው ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ይባርከዋል።

2 ሀ. 2 ሐ. 1 ሠ. 2 ለ. 1 ቀ. 1
ለ. 1 መ. 1 ረ. 2 ሸ. 2

9. ሀ. 3 ሐ. 2 ሠ. 2
ለ. 1 መ. 3 ረ. 1

3. ሀ. ቸርነት ሐ. በጎነት
ለ. በጎነት መ. ቸርነት

10. ሀ. እውነት ሐ. ሐሰት ሠ. እውነት
ለ. ሐሰት መ. እውነት ረ. እውነት

4. ሀ. እውነት ሐ. ሐሰት ሠ. ሐሰት
ለ. እውነት መ. እውነት

11. ሀ. ለወንድሞቹ የሚያስፈልጋቸውን ነገር ከስጣቸው በኋላ ለአባቱ የተመረጠውን የግበዕ በረከት ላከለት።
ለ. ረዓብ የእስራኤልን ሰላዮች ካስጠለለች በኋላ በሌላ አቅጣጫ ላከቻቸው።
ሐ. ለቅዳሱ የእግዚአብሔር ለው ኤልሳዕ ምግብ እና መጠለያ በመስጠት አስተናገዶቸው።
መ. ዶርታ ዘወትር ድሆችን እየረዳች መልካም ታደርግ ነበር።
ሠ. ያላቸውን ሁሉ ሸጠው እያንዳንዱ እንደሚያስፈልገው ይሰጡ ለስነበረ በመካከላቸው ችግረኛ አልነበረም።

5. እርስ ሩሀሩህ፣ ባለፀጋ፣ ስቁጣ የዘገየ፣ ፍቅር የተሞላና ልንከሰስ በሚገባ ጊዜ እንኳን የማይከሰን፣ እንደ ኃጢአታችንና እንደሚገባን ያልከፈለን ነው።

12. የእንተ መልስ። የኔ መልስ የሚከተለው ነው። ምክንያቱም ራሴን ለክርስቶስ ስመሰጠት ስለመረጥኩኝ የእርሱ እገልጋይ ነኝ፣ እናም ሌሎቹን በስሙና በእርሱ ፍቅር እገለግላለሁ።

6. ሀ. እግዚአብሔር ሁሳችንንም ስስሚወደን እያንዳንዱን ሰው ወደ ንስሐ ይመራል። ከራሱ ማንነት የተነሳ በጎነቱ ለሁሉም ሰው ተዘርግቷል።

ለ. ንስሀ ያልገቡትና የእግዚአብሔርን ይቅርታ ያልተቀበሉት ከእግዚአብሔር ተለይተው እግዚአብሔር እንደ እመዋቸው ብዛት ይፈርደባቸዋል።

13. የእንተ መልስ። እስታውስ ቸርነትና በጎነት ልምምድን ይጠይቃል። ቸር ለመሆንና በጎ ለመስራት መነሳሳት እንድ ነገር ነው። ነገር ግን ውሳኔህን በተግባር ለመተርጎምም መንፈስ ቅዱስ ፍሬውን በውስጥህ እንዲያሳድግ መፍቀድ እስፈላጊ ነው።

7 እምነት
የማመን ፍሬ

ትምህርት

እምነት ወይም ታማኝነት በእምነት ሙሱ የመሆን ባህሪይ ነው። እምነት የመጽሐፍ ቅዳስ ትልቁ ርዕስ ነው። መጀመርያ በፍጥረት 4 ላይ ቃየል እና አቤል መስዋእታቸውን ለእግዚአብሔር ሲያቀርቡ ተጠቅሷል። እግዚአብሔር የአቤልን መስዋእት ሲቀበል የቃየልን ግን አልተቀበለውም። ምክንያቱ በዚያ ክፍል ላይ አልተጠቀሰም፣ ነገር ግን ከዕብራውያን 11 እንደምንማረው ልዩነት ያመጣው የእምነት ጉዳይ መሆኑን ነው።

እግዚአብሔርን ከእምነት ነጥለን ማየት እንችልም። ስምሳሌ እግዚአብሔር የደህንነታችን ራስ ፣ ዐጋው ምንጫችን እና እምነታችን የመቀበያ ባንኳ ነው። ከክርስቶስ ጋር ያለን ግንኙነት የተመሰረተው በእምነት ላይ ነው። "እድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎ እንደተፃፈ የእግዚአብሔር ዕድቅ ከእምነት ወደ እምነት በእርሱ ይገለጣልና" (ሮሜ 1፥17)። "በእምነት እንጂ በማየት እንመላለስምና" (2ቆሮ 5፥7)። እምነት በልጁ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ላለን ግንኙነት መሰረት ነው። "ያለ እምነትም እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ፣ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና" (ዕብ 11፥6)።

በዚህ ትምህርት ውስጥ የተለያዩ የእምነት ገፅታዎችን ትማራለህ። ከእነዚህም ውስጥ አንዱ ታማኝነት የተባለው የመንፈስ ፍሬ ነው። እምነትህ የሚረጋገጠው በታማኝነትህ ነው። የታማኝነት መሠረቱ በእግዚአብሔር ላይ ያለህ እምነት ነው፣ ይህም በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ስታልፍ፣ በሕይወት የሚያኖርህ ነው። ይህም የሚገለፀው በታማኝነትህና በማይለዋወጥ የክርስትና ሕይወት ነው። የእምነት ፍሬ በህይወትህ ይታያልን? ይህ ትምህርት ለእግዚአብሔር መንግስት ያለህን ታማኝነት እንድትመረምር ይረዳሃል፣ እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ በሕይወትህ ይህንን ፍሬ የበለጠ እንዲያፈራ እንድትፈቅድለት ያበረታታሃል።

የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- የታማኝነት ምንነት
- ታማኝነት ሲገለፅ
- ታማኝነት በምሳሌ

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህንን ትምህርት ስታጠናቀቅ የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ መቻል ይኖርብሃል።

- እምነትና ታማኝነት የሚሉት ቃሎች በመጽሐፍ ቅዳስ በተጠቀመው መሠረት የቃሎችን ምንነት መግለፅ።
- በበድስቱ የእምነት ገፅታዎች መሀከል ያለውን ልዩነት መግለፅ።
- ስለ እግዚአብሔር ታማኝነት ምሳሌዎች መበጠትና ከዚያ ልንማር የምንችለውን መግለጽ።
- በታማኝነት፣ ፍቅር፣ መከራ፣ ቃል መግባት፣ ታዛዥነት፣ አለመስዋወጥና ባሳደራኑት መካከል ያለውን ግንኙነት መግለፅ።
- የመንፈስ ፍሬ የሆነውን የታማኝነትን ዋጋ ማወቅና ይህ ፍሬ በህይወትህ እንዲያድግ መፈለግ።

የክፍለ ትምህርቱ መመርያዎች

1. ያለፉትን ትምህርቶች በታጠና በነበረበት መልክ ይህንንም ትምህርት አጥና። የማታውቃቸውን ቁልፍ ቃላት ፍቺዎች መማርህንና ሁሉንም የመጽሐፍ ቅዳስ ክፍሎች ማንበብህን አረጋግጥ። ሁሉንም የማጥኛ ጥያቄዎች መልስ ከሰጠህ በኋላ መልስህን አመሳክር።
2. የሙከራ ፈተናውን በመሥራት መልስህን በመጽሐፉ መጨረሻ ከተሰጠው ጋር አመሳክር።

የትምህርቱ ዝርዝር

የታማኝነት ምንነት

ስድስት የእምነት ዓይነቶች

ዓላማ 1 ስድስቱን የእምነት መግለጫዎች ከፍቺዎቻቸው ጋር ማዛመድ።

የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣ . . . ነው (ገላ 5፥22)።

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዳስ ተርጓሚዎች ከታማኝነት ይልቅ እምነት በማለት በገላ 5፥22 የተዘረዘረውን ተርጉመውታል። ነገር ግን ታማኝነት የሚለው ትርጓሜ የበለጠ ትክክለኛ ነው። ስፋ ባለ መልኩ እምነት በእግዚአብሔርና በወንጌል ላይ ያለን የማይናወጥ አበተሳሰብ በለሆነ ከፍሬ ይልቅ ግንድ ነው። የመንፈስ ፍሬ የተበጠው አንድ ባህሪይ ሲሆን ታማኝነት እምነት ያለው ሰው አንዱ ባህሪይ ነው።

የታማኝነትን ጠቅሜታ ከማጥናታችን በፊት እምነት የሚለውን ቃል ትርጉም መረዳት ያስፈልገናል። ይህንን ለማደረግ በድበት የእምነት ገፅታዎችን እንመለከታለን። እምነት ራሱን በብዙ መንገዶች የገልፃል።

❶. *ተፈጥሮአዊ እምነት* ማንኛውም ሰው የተወለደው ከተፈጥሮአዊው እምነት ጋር ሲሆን ይህም ከበው የማበብ ችሎታ ጋር የተያየዘ ነው። ይህም በአውሮፕላን ለትሄደ የሚኖርህ እምነት ነው። አውሮፕላኑ

በደህና ሁኔታ ላይ እንዳለና ለመብረር የሚያስችለው ብቃት እንዳለው ማመን ይኖርብሃል። አብራሪውም አውሮፕላኑን ለማብረርና የተፈለገው ቦታ ለማሳረፍ አስፈላጊ ስልጠናና ችሎታ እንዳለው ማመን ደግሞ ይኖርብሃል። በየእለቱ ተፈጥሮአዊ እምነታችንን በብዙ መንገዶች እንለማመዳለን። በሌሎች የተዘጋጀውን ምግብ በምንበላበት ጊዜ ፣ ብዙ መኪና በሚበዛበት መንገድ ስናቋርጥ ፣ መብራት ስናበራ፣ እና ከሌላ ሰዎች ጋር ባሰን ግንኙነት ሁሉ በዚህ አይነቱ እምነት ላይ እንደገፋለን። በዚህ መልክ ሰው ጥሩ አስተሳሰብ ወይም ከእግዚአብሔር ጋር ግላዊ ግንኙነት ሳይኖረው ህልውናውን ሲያምን ይችላል።

❷. *የሚያድን እምነት* - ይህ ዓይነቱ እምነት ወደ ልብ የሚገባው በመንፈስ ቅዱስ ቅባት በሆነ የእግዚአብሔር ቃል ነው። "፬ጋው በእምነት አድኖአችኋልና፣ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ እንጂ ከእናንተ አይደለም፣ ማንም እንዳይመካ ከስራ አይደለም" (ኤፌ 2:8-9)። ይህን ዓ ይነቱን እምነት ነው ወንጌልን በሰማን ጊዜ እግዚአብሔር በልባችን ውስጥ የሚያስነሳው። የእኛ ድርሻ ማመን፣ ኃጢአታችንን መናዘዝና የእግዚአብሔርን የድኅነት ስጦታ መቀበል ነው። የወህኒ ጠባቂውም ጳውሎስን እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? ብሎ ጠየቀው። የጳውሎስም ምላሽ "በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን እንተና ቤተሰቦችህም ትድናላችሁ" (የሐዋ 16፥30-31) የሚል ነበር።

❸. *ሀያው እምነት* - ክርስቶስን ከተቀበልን በኋላ ጠንካራና፣ በጌታ ላይ በማይናወጥ እምነት መኖር እንችላለን። ይህ እምነት ምንም ይሁን ምን እግዚአብሔርን ማመን እንድንተጥል ይረዳናል። ምክንቱም በእርሱ ዋስትና ስላስን ነው። ሀያው እምነት በፈተናችን እንድናሸንፍ ይረዳናል። ይህን እምነት ጳውሎስ እንዲህ በማስት ይገልጸዋል (2ቆሮ 4፥13)። "እመንሁ ስለዚህም ተናገርሁ ተብሎ እንደተጻፈ ያው እንዱ የእምነት መንፈስ ስላስን፣ እኛ ደግሞ እናምናስን ስለዚህም እንናገራለን። በዚሁ የእምነት መንፈስ እኛም እናምናለን ስለዚህም እንናገራለን።"

❹. *የእምነት ስጦታ* - ይህ እምነት መንፈስ እንደፈቀደ የሚስጠው አምላካዊ የመንፈስ ቅዱስ በጦታ ነው። ለእንዱም በዚያው መንፈስ እምነትን . . . ያደርጋል" (1ቆሮ 12:9) ይህ እምነት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተአምራትን በማድረግ፣ በፈውስና በሌላ የመንፈስ ስጦታዎች ይገስፃል። ይህ በስው ውስጥ የሚሰራ የእግዚአብሔር እምነት ነው።

❺. *የእምነት ፍሬ (ታማኝነት)* - ከእምነት በጦታ የተለየ እምነት እንደ መንፈስ ፍሬ በውስጣችን ያድጋል (2ቆሮ 10፥15 እና 2ተሰ 1፥3 ተመልከት)። ኢየሱስ ይህንን እምነት በማር 11፥22 ሲጠቅሰው "በእግዚአብሔር እመኑ" ብሎአል። ይህን አባባል በቁሙ ስንወስደው በእግዚአብሔር ውስጥ ያለው እምነት ይኑራችሁ እንደ ማለት ነው። ይህ እምነት በታማኝነት ባህሪ ወይም አመለካከት ይገለፃል።

❻. *እምነት እንደ አሰተሳሰብ* - የታመነው ነገር ወይም የእምነቱ ይዘት እምነት ይባላል። በሐዋ 6፥7 እንደተገለጸው "በኢየሩሳሌም የደቀ መዛሙርት ቁጥር እጅግ እየበዛ ሄደ፣ ከካህናትም ብዙ ሰዎች ለሃይማኖት የታዘዙ ሆኑ" ይላል። በሌላ አባባል እነዚህ ካህናት

የወንጌልን አበተምህሮ ተቀበሉ፣ በክርስቶስ እውነት ኃይል ተረቱ፣ ይህ አስተምህሮና እውነት እምነታቸው ሆነ ማለት ነው።

(1). በስተቀኝ ያለውን የእምነት መግለጫ በስተግራ ካለው ከእያንዳንዱ ፍቺው ጋር አዛምድ።

ሀ. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ስቤተክርስቲያን	1. ተፈጥሮአዊ እምነት
ለ. ወንበር ላይ ለመቀመጥ የሚያስፈልግ	2. የሚያድን እምነት
ሐ. የእምነቴ ይዘት	3. ሀያው እምነት
መ. በመንፈስ ቅዱስ የሚያድግ እምነትና ታማኝነትን የሚያፈራ	4. የእምነት ስጦታ
ሠ. በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ያለማቋረጥ በእግዚአብሔር ላይ ያለ እምነት	5. የእምነት ፍሬ
ረ. ወደ ንስሀ የሚመራና ክርስቶስን ለመቀበል የሚያበቃ እምነት	6. እምነት እንደ አስተሳሰብ

የታማኝነት ፍቺ

ዓላማ 2 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰውን እምነትና ታማኝነት የሚሉትን ቃላት ጠቀሜታ የሚያንፀባርቁ ዐረፍተ ነገሮችን ለመለየት።

በብሉይ ኪዳን እንደተጠቀስው ታማኝ የሚስውን ቃል ማጥናት የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖረን ያደርጋል። መነሻ የሆነው ቃል "እማን" የሚል ሲሆን፣ እንደ ዘዳ 12፥7 አባባል ይህም ማለት "መገንባት፣ መደገፍ፣ ማፅናት፣ ስቋሚነት መመስረት፣ መታመን፣ እውነተኛ መሆንና ለለእንድ ነገር እርግጠኛ መሆን ነው።

(2). ዘጉ 12፥7ን አንብብ። ሙሴን እንደ ታማኝ የሚገልጸው ከእነዚህ ፍቺዎች ውስጥ የትኛው ነው?

"እማን" ከሚለው ቃል "ኢሙን" (እምነት) የሚለው ቃል የመጣ ሲሆን፣ በዘዳ 32፥20 ውስጥም የተጠቀስው በእሱታዊ መልክ ሰሳልታመኑት እስራኤላውያን በመናገር ነው። "አሜናህ" (መታመን) በዘጸአት 18፥21 የሚናገረው ታማኝ ስዎችን ስለመሾም ነው። የእኛ አሜን የሚስው ቃል የመጣው አማን ከሚለውና በዘዳ 5፥22 (ይሁን) ከተጠቀሰው ነው። ስስዚህ ከእነዚህ ምሳሌዎች እንደምናየው ዋናው ሀሳብ በብሉይ ኪዳን *ከመታማመን፣ ከጥንካሬና ከእርግጠኝነት* ጋር የተያያዘ እንደሆነ ልንረዳ እንችላለን ነው።

በአዲስ ኪዳን "ፒስቲስ" የሚለው ቃል እምነት ተብሎ ተተርጉሟል። ማእከላዊ ሀሳቡም በመስማት ላይ ተመስርቶ መቀበል ወይም በሙሉ ልብ ማመን ማለት ነው። ሮሜ 10፥17 "እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም ከእግዚአብሔር ቃል ነው።" በማቴ 23፥23 ፒስቲስ ከመተማመን ወይም ታማኝነት ጋር የተያያዘ ነው።

ኢየሱስ እርሱ እውነት እንደሆነና *መታመን* እንደሚገባው በድርብ አሜን አሜን በማለት 25 ጊዜ በዮሐንስ ወንጌል ተጠቅሷል። እንዳንድ ትርጉሞች "እውነት እውነት" ሲሉት፣ ሌሎች ደግሞ "እውነት እላችኋለሁ" በማለት ይገልጹታል። የመጀመርያው ይሻው *መግለጫ* በዮሐ 1፥51 ውስጥ ተጠቅሷል።

እምነት የሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን በጥቂቱ ተገልጿል። ቢሆንም በብሉይ ኪዳን ቅዱሳን ሕይወት ውስጥ እንደነበረ ማየት ይቻላል። ዕብ 11፥2 "አባቶችም የተመሠከረላቸው በዚሁ ነው" በማለት ይህን እምነታቸውን ይገልጻል። ምዕራፉ በሙሉ የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን የነበራቸውን እምነት ሁሉ ያስታውስናል። እኛ ዛሬ በእምነት እንደዳንን እነርሱም እንዲሁ በእምነት ነው የዳኑት። እነርሱ በሚመጣው የእግዚአብሔር በግ በማመን ሲድኑ፣ እኛም በታረደው በግ በማመን ድነናል። እነርሱ በመምጣቱ ጥላ ኖሩ። እኛ ግን በእኩሉ እንኖራለን (ቆላ 2፥17ን ተመልከት)። ልዩነት በጥላ ውስጥ ስንሆን ሁልጊዜ እኩሉ በዚያ ቢሆንም እንኳን አይታይም።

ለምሳሌ የአስቴር *መጽሐፍ* የእግዚአብሔርን የማዳን እጅ የሚያሳይ እስደናቂ *መጽሐፍ* ቢሆንም የእግዚአብሔር ስም እንድም ጊዜ አልተጠቀሰም። እርሱ ባይታይም እንኳ የእርሱ ጥላ አዚያ አለ። ይህ የሚያፅናና እውነት ነው። በሁኔታዎች ውስጥ ባናየውም እርሱ ሲያድነን አለ። በመዝ 121፥5 የተሰፋ ቃል እንዲህ የሚል ነው። "እግዚአብሔር ይጠብቅሃል፣ እግዚአብሔር በቀኝ እጅህ በኩል ይጋርድሃል።" እምነት በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሁለት ጊዜ ብቻ ተጠቅሷል (ዘዳ 32፥20 እና ዕን 2፥4)። ነገር ግን ጥላው በሁሉም የብሉይ ኪዳን *መፃህፍት* ከመታየቱም በላይ በዕብ 11 ላይ ተረጋግጧል። ይህም ምእራፍ ደግሞ ታማኝነት እምነትን በትክክል የሚያሳይ የመንፈስ ፍሬ እንደሆነ ይጠቁማል።

ቀደም ብለን እንዳልነው ፒስቲስ የሚለው ቃል እምነት እና ታማኝነት በመባል በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ውስጥ ተተርጉሞዋል። ምክንያቱም ከክርስቶስ ጋር ባለን ግንኙነት ሁለት *መታሰብ* ያለባቸው ገፅታዎች አሉ። እምነት ከጌታችን ከኢየሱስ ጋር ያለ የመንፈሳችን የቅርብ ግንኙነት ነው። በመጀመርያ፣ እንዲያድነን *ሙሉ* ለሙሉ በእርሱ ላይ ያለን *መታመን* ነው (ዮሐ 1፥12 እና ዕብ 7፥25ን ተመልከት)። ሁለተኛ፣ በክርስቶስ *ማመን* ሰው ለእኛ ራሱን *ሙሉ* ለሙሉ እንዲሰጥ የሚያደርግ ነው። የመጀመርያው የእምነት ገፅታ ከኢየሱስ ጋር እንደ አዳኛችን ሲያስተሳስረን የሁለተኛው ደግሞ በሙሉ ታዛዥነት ያስተሳስረናል። "በእርሱ እናራለሁ የሚል እርሱ እንደተመላለሰ ራሱ ደግሞ ሊመላለስ ይገባዋል" (1ዮሐ 2፥6)። ስለዚህ ፒስቲስ የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለበትን ሁለት *መንገዶች* የሚያመለክቱት *ማመንን* እና ታማኝነትን ነው።

በግሪኩ ዓለም ፒስቲስ የሚለው ቃል አብዛኛውን ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውለው የአንድን ሰው አስተማማኝነት ወይም ታማኝነት ለመግለጽ ነው። ይህ አስተማማኝነት ለአንድ የእውነት *መስፈርት* ታማኝ *መሆንን* ከሌሎች ጋር ባለ ግንኙነት አስተማማኝ *መሆንን* የሚያሳይ ነው። እንዲህ ዓይነቱ አስተማማኝ ሰው ሁልጊዜ ትክክለኛውን ነገር

ያደርጋል፣ ደግሞም የገባውን ቃል ይጠብቃል። ስለዚህ ታማኝነት እንደ *መንፈስ* ፍሬነቱ ነቀፋ የሌለበትን፣ ቃልን *መጠበቅን*፣ እውነተኛነትን የሚታመን *መሆንንና* ትክክለኛነትን፣ ሁሉ የያዘ ባህሪ ነው።

(3). በተሰጡት ምሳሌዎች *መሰረት* የሚከተሉትን ቃላት ትርጉም ፃፍ።

ሀ. ፒስቲስ
ለ. አሜናህ
ሐ. ኢሙን
መ. አሜን

(4). ከእነዚህ *ዐረፍተ* ነገሮች ውስጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተሰጡትን እምነት እና *ታማኝነት* የሚሉትን ቃላት ጥቅም ከሚገልጹ *ዐረፍተ* ነገሮች ፊት ያለውን ፈደል አክብብ።

ሀ. እማን፣ አሜናህና አሜን የሚሉት ቃላት በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለ *መታመን*፣ ጥንካሬና እርግጠኝነት ይናገራሉ።
ለ. እምነት የሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከጥላ ጋር ስናዛምደው በተደጋጋሚ ተጠቅሷል ማለት ይቻላል።
ሐ. ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል ላይ ብዙ ጊዜ አሜን አሜን ሲል እውነተኛነቱ ላይ ማተኮሩ ነው።
መ. ፒስቲስ የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተጠቀሰው የሚያድነውን እምነት ለማመልከት ብቻ ነው።
ሠ. የመንፈስ ፍሬ የሆነው ታማኝነት ለእውነተኛ *መስፈርቶች* ታዛዝነትንና ከሌሎች ጋር ባለ ግንኙነት እውነተኝነትን ያካትታል።

ታመማኝነት ሲግሰቀ

የእግዚአብሔር ታማኝነት

ዓላማ 3 የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን በመተንተን የእግዚአብሔርን ታማኝነት የሚገልጹ ዐረፍተ ነገሮች ለመፃፍ።

ታማኝነት የቅዱስ ስላሴ ባህሪይ ነው። እግዚአብሔር እብ ታማኝ ነው። "እንተም እምላክሀ እግዚአብሔር እርሱ እምላክ እንደሆነ፣ ለሚወዱትም ትእዛዙንም ለሚጠብቁ ቃል ኪዳኑን ምህረቱን እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ የሚጠብቅ የታመነ እምላክ እንደሆነ እወቅ" (ዘዳ 7፥9፣ 1ቆሮ 10፥13ንም ተመልከት)። የተባረከው ጌታችን ኢየሱስ የታመነና እውነተኛ ተብሏል (ራዕ 19፥11)። እርሱ የእምነታችን ራስና ፈፃሚ ነው (ዕብራውያን 12፥2)። ታማኝነት የመንፈስ ቅዱስ ባህሪይ ነው። የመንፈስ ፍሬ እምነት (ታማኝነት) ነው (ገላ 5፥22)።

ብዙ ጊዜ *መጽሐፍ* ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ታማኝነት የመስክራል። ጥቂቶችን እንመልከት።

❹. *ታማኝነት ተላብሷል* - "የወገቡ መታጠቂያ ፅድቅ፣ የጎኑም መቀነት ታማኝነት ይሆናል" (ኢሳ 11፥5)። *ታማኝነት* የእግዚአብሔር የእርሱነቱ ወይም የማንነቱ አንዱ ክፍል እንደሆነ ያስታውሰናል።

❺. *ቃሉን ለመጠበቅ የታመነ ነው* - "የተስፋን ቃል የሰጠው የታመነ ነውና እንዳይነቃነቅ የተስፋችንን ምስክርነት እንጠብቅ" ዕብራውያን 10፥23 የእግዚአብሔር ቃል በተስፋ የተሞላ ነው። እነዚህም ተስፋዎች የእኛ ናቸው። ጴጥሮስ እንዳለው በእርሱ ክብርና በጎነት "የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን ሰጠን" (2ጴጥ 1፥4)። ጌታ አንድ የተስፋ ቃል ከገባልህ ቃሉን በእምነትና በፀሎት ብትጠይቅ እርሱ የታመነ ነው።

❻. *እግዚአብሔር ይቅር ለማለት የታመነ ነው* - ይህ የታመነ ቃል በ1ዮሐ 1፥9 አለ። "ኃጢአታችንን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከአመፃም ሁሉ ሊያነፃን የታመነና ፃድቅ ነው።" ይቅርታው በሚለማን ሰሜት ላይ የተመሰረተ ሳይሆን፣ እርሱ ቃል የገባልንን በማድረግ በእምነታችን ላይ የተመሰረተ ነው።

❼. *እግዚአብሔር እኛን በመጥራቱ የታመነ ነው* - እኛን መጀመርያ ሲጠራን ለደህንነት ሲሆን ቀጥሎም ጴጥሮስን በገሊላ ባህር እንደጠራው እንድናገለግለው ነው። እርሱን ትተው ወደኋላ የተመለሱ ወደ እርሱ እንዲመለሱ ይጠራል። (ኤር 3፥12፣ 22 ተመልከት)። የጠራን እቅዱንና ፈቃዱን ለሳሙኤል እንደነገረ ሁሉ ለእኛም ሊገልፅልን ነው (1ሳሙ 3፥10-11)። እርሱ የጠራን እንድንቀደስና ቅዱሳን እንድንሆን ነው (1ቆሮ 1፥2)። አንድ ቀን እንደተሰፋ ቃሉ ጌታን በአየር ላይ ለመቀበል በደመና እንነጠቃለን (1ተስ 4፥13-17) በ1ተስ 5:24 እንዲህ የሚል የተሰፋ ቃል አለን። "የሚጠራችሁ የታመነ ነው እርሱም ደግሞ ያደርገዋል።" ለእርሱ የተለየ ስራ እንድትሰራ ጠርቶሃልን? ቃል የገባውን እንደሚያደርግ በታ ማኝነቱ ልትደገፍ ትችላለህ። ከነብዩ ጋር አንዲህ ልንል እንችላለን። "ያልጠፋነው ከእግዚአብሔር ምህረት የተነሳ ነው ርኅራሄው እያል ቅምና ማለዳ ማለዳ አዲስ ነው ታማኝነትህ ብዙ ነው" (ሰቆ 3፥22-23)።

(5). የትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ነው ታማኝነት ጠቃሚ የሆነ የእግዚአብሔር ባህርይ እንደሆነ የሚገልፅልን??

(6). በገላ 6፥7-8 የተጠቀሱት እግዚአብሔር ቃሉን እንደሚጠብቅ የሚገልፁት ሁለት ገፅታዎች ምን ምንድን ናቸው?

(7). የእግዚአብሔርን ይቅርታና ምህረት ለመቀበል የሚያስፈልጉት ሁለት መስፈርቶች የትኞቹ ናቸው?

(8). እግዚአብሔር የጠራንን ማድረግ እንድንችል እንደሚረዳን ምን ዓይነት ዋስትና አለን?

(9). በዚህ ትምህርት ውስጥ የተጠቀሰውን የእግዚአብሔርን የታማኝነት ገፅታዎች እንዲያጠቃልል ይህንን ዐረፍተ ነገር እማለ። እግዚአብሔር ለ የታመነ ነው።

የታማኝነት መመርያዎች

ዓላማ 4 ታማኝነትን የሚገልጹ ቃላትን ከታማኝነት መርሆዎች ጋር ለማዛመድ።

ሮሜ 5፥1-2 "እንግዲህ በእምነት ከፀደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ፣ በእርሱ ደግሞ ወደ ቆምንበት ወደዚህ ፀጋ በእምነት መግባት እግኝተናል" በማለት ይነግረናል። ስለዚህ እምነት የታማኝነትና መልካም ነገሮች የሆኑት የሌሉቹ የመንፈስ ፍሬዎች መሰረት ሆኖ የሚሰራ ነው። በክርስቶስ ያለ አዲሱ ሕይወት ከአሮጌው ከ:ጢአት ኑሮ ጋር ሲነፃፀር ታማኝነት፣ ትህትና ነው። በዚህ ጊዜ ልንመለከታቸው የሚገቡ ጠቃሚ የታማኝነት መመርያዎች አሉ። እነዚህ መመርያዎች ክርስቲያናዊ ኑሮን የሚቀርፁና በግንኙነቱም ውስጥ ሁሉ በታ ያላቸው ናቸው።

❶. *ታማኝነት እና ፍቅር* - ገላ 5፥6 እንደሚለው "በክርስቶስ ኢየሱስ ሆኖ በፍቅር የሚሰራ እምነት እንጂ መገረዝ ወይም አለመገረዝ እይጠቅምምና።" እምነትን እንደ መሰረት ሆኖ እንዲገለጽና እንዲሰራ ፍቅር ያስፈልገዋል። ልክ ባል እና ሚስት እርስ በርስ ያላቸውን ፍቅር አንዱ ለሌለው ባሰው ታማኝነት እንደሚያረጋግጡ፣ እኛም ለጌታ ያለንን ፍቅር ለቃሉ እና ለፈቃዱ ታማኞች በመሆን እናረጋግጣለን።

❷. *ታማኝነት እና መከራ* - ታማኝነት ስለክርስቶስ መከራ መቀበልን ያጠቃልላል። በዚህ መልኩ ታማኝነት ባለፈው ትምህርታችን ካየነው ከፅናት ጋር የተሳሰረ ነው። የዕብራውያን መልእክት የተፃፈው እስፈሪ ስደት በነበረበት ሁኔታ ነው። በእንደዚህ እይነት ሁኔታ እምነት ይፈተናል። በእብራውያን 6፥12 ታማኝነትና ፅናትን በመከራ ውስጥ እናያለን። "በእምነትና በትእግስትም የተስፋውን ቃል የሚወርስትን እንድትመስሉ እንጂ ዳተኞች እንድትሆኑ አንፈልግም" የመንፈስ ፍሬ የሆነው ታማኝነት በማንኛውም ሁኔታ ይፀናል።

❸. *ታማኝነት እና ቃልን መጠበቅ* - ታማኝነት እንደ መንፈስ ፍሬ ከስነምግባር ጋር የተያያዘ ነው። ይህ የተባረከ የመንፈስ ፍሬ ክርስቲያን በቃል እና በተግባር ሃላፊነት እንዲሰማው ያደርጋል። የሰው ቃል ትልቅ ዋጋ የነበረው የአጅ ሰላምታም ልክ እንደተፃፈ ወረቀት ማስረጃ የሚቆጠርበት ጊዜ ነበር። ይህ አሁን ባለንበት ዘመን እውነት አይመስልም። ከእግዚአብሔር ጋር የሚራመድ ሰው የተለየ ነው፣ ምክንያቱም የታዛዥነት፣ የታማኝነትና የትህትና ፍሬ በውስጡ ነው ። መንፈስ ቅዱስ ሁልጊዜ ክርስቲያን በቃሉ መኖር እንዲችል ኃይል ይሰጠዋል። መክብብ 5:5 "ተሰለህ የማትፈፅም ብትሆን ባትሳል ይሻላል" ይላል። ማንም ሰው ቃለ መሀላ እንዲፈጽም ወይም ቃል እንዲገባ አይገደድም። ነገር ግን ቃል ከገባህና መጠበቅ ካቃተህ የመንፈስን ፍሬ ማሳየት አልቻልክም ማለት ነው። የእግዚአብሔር ሰው በመዝ 15፥4 "እግዚአብሔርንም የሚፈሩትን የሚያከብር፣ ሰባልንጀራው የሚምል፣ የማይከዳም" ይላል። እንዲህ ዓይነቱ ክርስቲያን ብዙ ተናግረው ከማይፈፅሙትና ማንም ከማያምናቸው ከሀያ ሰዎች ይበልጣል። እነዚያ ግን የመንፈስ ፍሬ የላቸውም።

❹. *ታማኝነትና ታዛዥነት* - የመንፈስ ፍሬ የሆነው ታማኝነት ለእግዚአብሔር፣ ለባልደረቦቻችን፣ ለጓደኞቻችን፣ ለጎረቤቶቻችን ለሰራተኞቻችንና አሰሪዎቻችን ታዛዦችና ታማኞች እንድንሆን ያደርገናል። ታማኝ ሰው ገዢ ማለት በሚቀልበት ጊዜ እንኳን ትክክለኛ የሆነውን ነገር ይደግፋል። ይህ መርህ በማቴ 25፡14-30 ተገልያሞል። ጌታቸው በሌለበት ጊዜ እንኳን ታማኝ የሆኑና እንደታዘዙት የሚሰሩ ባሮች ይመሰገናሉ፣ ይሸለማሉም። ያልታመኑት ግን ይቀጣሉ።

❺. *ታማኝነትና አለመለዋወጥ* - ብዙ ሰዎች አንድ ፕሮጀክት ጀምረው መጨረስ ባለመቻላቸው ያፍራሉ፣ ጀምረህ ያልጨረስካቸው አንት ነገሮች አሉ? ክርስቲያናዊ ተግባር እንደ ቤተሰብ አምልኮ፣ የግል አምልኮ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ አስራትን መክፈል ጀምረህ ያልቀጠልክባቸው አሉን? ብዙ ውሳኔዎች ወስነህ በታማኝነት ለመፈፀም ያቃተህ፣ ይህ ካለመለዋወጥ ጉድለት ነው። ታማኝ ክርስቲያን የማይለዋወጥና ፅኑ ነው። ቤተክርስቲያን በመሄድ፣ ቃሉን በመጠበቅና መስራት ያለበትን በመሰራት ታማኝ ነው። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን እንዲህ ሲል መክሮታል። "በጊዜውም አለጊዜውም ፅና" (2ጢሞ 4፡2)። ይህ የሚያመለክተው በጌታ የተሰጠንን ተግባር በፅናት ስለመቀጠል ነው።

❻. *ታማኝነትና ባላደራነት* - ባላደራ ሰው የሌላን ሰው ጉዳይ ወይም ንብረት የሚያስተዳድር ነው። እኛ እንደፈቃዱ ሰራውን እንድንሰራ አደራ የተቀበልን የጌታ ባሮች ነን። ይህ ለጌታ ያለን አገልግሎት ነው፣ የመንፈስ ፍሬ የሆነው ታማኝነት ሰወንጌል አገልግሎት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ይህም ጳውሎስ ለወጣቱ ጢሞቲዎስ በዛፈው ቃል ውስጥ ይታያል። "መልካሙን አደራ በእኛ በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ ጠብቅ" (2ጢሞ 1፡14)። ለጌታ አገልጋይ የተሰጠው ይህ መልካም አደራ ምንድን ነው? በመጀመርያ ደረጃ የእግዚአብሔር ሀብት የሆነውን የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ለሌሎች ማካፈል የእኛ ድርሻ ነው። ኢየሱስ እንዲህ ሲል ጠየቀ። "እንኪያስ ምግባቸውን በጊዜው ይሰጣቸው ጠንድ ጌታው በቤተሰዎቹ ላይ የሚሾመው ታማኝና ልበም መጋቢ ማን ነው?" (ሉቃ 12፡42)። ጥሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ለመሰጠት በታማኝነት ጥረት ማድረግ ይኖርብናል። ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ሲል ፅፏል። "ከተዓፈው አትለፍ" (1ቆሮ 4፡6)። ጳውሎስ የእርሱ ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንደሆነ እርግጠኛ ስለሆነ እንዲህ ብሏል። ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ (2ጢሞ 2፡2)። እንደገናም በ1ቆሮ 4፡2 ጳውሎስ ሲፅፍ "እንደነዚህም ሲሆን በመጋቢዎች ዘንድ የታመነ ሆኖ መገኘት ይፈለጋል" ብሏል።

የተጠራነው በዚህ ዓለም ለእያንዳንዱ ንስሀ ሳልገባ ሀጢአተኛ ከሚመጣው መቅሰፍት እንድናስጠነቅቅና ጠበቂዎች እንድንሆን ነው። ሕዝ 3፡18 እንዲህ ሲል ያስጠነቅቀናል። "እኔ ኃጢአተኛውን፣ በእርግጥ ትሞታለህ ባልሁት ጊዜ፣ አንተም ባታስጠነቅቀው ነፍሱም እንድትድን ከክፉ መንገዱ ይመለስ ዘንድ ለኃጢአተኛው አስጠንቅቀህ ባትነግረው፣ ያ ኃጢአተኛ በሀጢአቱ ይሞታል፣ ደሙን ግን ከእጅህ እፈልጋለሁ።"

የምንኖርበት ዘመን ለዎች ራሳቸውን የሚወዳቡት፣ የግል ጥቅም የሚያለድዳቡትና ደስታቸውን የሚፈልጉበት ጊዜ ነው። ክርስቲያን መጋቢ ግን የጌታውን ስራ በትድሚያ በታማኝነት የሚሰራና ለእግዚአብሔር መንግስት ነፍሳትን የሚማርክ ነው።

ታማኝነት በባላደራነት ውስጥ ጊዜያችንና አውቅታችን፣ ሁሉ የእሱ መሆኑን ማስታወስና የእርሱ ስራ አስኪያጆች መሆናችንን በማለብ ያለንን ለእርሱ መስጠትን ያካትታል። በጌታችን ንብረት ላይ ታማኝ መሆን አለብን። "በሌላው ሰው ሀብት ካልታመናችሁ፣ የራሳችሁ የሆነውን ማን የሰጣችኋል?" (ሉቃ. 16፡12) ተብሎ እንደተፃፈ ነው።

ማቴ 25 ባላደራነትን የሚመለከቱ ሁለት የኢየሱስን ምሳሌዎች ይዟል። ጌታ ሲመጣ በሀዝቡ ላይ ሊያገኛቸው የሚፈልጋቸው ሁለት ነገሮች ላይ ትኩረት አድርጓል። እነሱም ከእርሱ ጋር ፍፁም የሆነ ግንኙነትና ለእርሱ ታማኝ መሆን ናቸው።

(10). ማቴ 25፡14-26 አንብብ። ከምንባቡ ውስጥ የምንማረው መንፈሳዊ ትምህርት የትኛው ነው?

ሀ. ከእግዚአብሔር ያገኘነውን ነገር ለሌሎች ሰናካፍል ከሚጠፋብን ይልቅ አጥብቀን ብንይዘው ይሻላል።
ለ. የእግዚአብሔር መንግስት ለእግዚአብሔር ለመስራት ብዙ መክሊት ላላቸው ተዘጋጅታለች።
ሐ. ይብዛም ይነስም ጌታ የሰጠንን ነገር እንዴት እንደምንጠቀምበት ከጌታ ዘንድ ሃላፊነት አለብን።

(11). በስተቀኝ የሚገኘውን ቃል በስተግራ ከሚገኘው ሊዛመድ ከሚች ሰው መመርያ ጋር አዛምድ።

ሀ. የእርሱ አስተዳዳሪዎች ከሆንን ጊዜአችንን፣ ችሎታችንንና ንብረታችንን ለእርሱ መሰጠት አለብን።	1. ፍቅር
ለ. ቃላችንን መጠበቅ እና ታማኝ መሆን እንችላለን።	2. መከራ
ሐ. ቅዱሳን ትእግስትና ፅናት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል።	3. ቃልን መጠበቅ
መ. የጌታ ሀብት የሆነውን የክርስቶስን ወንጌል ማካፈልን ያካትታል።	4. ታማኝነት
ሠ. ታማኝነትን መግለጽና መለማመድ ይጠይቃል	5. አለመለዋወጥ
ረ. ለጌታ አንድ ስራ ከጀመርኩ እስከ መጨረሻው እዘልቃለሁ።	6. ባላደራነት
ሸ. መልካም ልምዶችን - እንደ ቤተሰብ አምልኮ አይነቱን ሳላቋርጥ እቀጥላለሁ።	
ቀ. ጌታን እንደ ምሳሌዬ በመውሰድ፣ ሌሎችን ትክክለኛ በሆነ ነገር እረዳለሁ።	

ታማኝነት በምሳሌ

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎች

ዓላማ 5 ከመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ስለ ታማኝነት የምንማረውን ስመማስድ።

ዮሴፍ- ጥሩም የሆነ መሪና ታማኝ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነው። በጌታው ላይ እምነት ከማጉደል ይልቅ ወደ እስር ቤት መሄድን መረጠ። ስለ ታሳቁ ታማኝነቱ የተጻፈውን ከዘፍ 37 እስከ 48 እንመለከተዋለን።

ኢያሱ- የታመነና አደራ የሚጣልበት ሰው ስለሆነ እስራኤላውያንን ወደተገባላቸው የተስፋ አገር ለመምራት ተመርጧል። የእርሱን ታማኝነት የሚገልጸው አንዱ ምሳሌ ቃሉን ጠብቆ የገባለን ለዎችን አለመግደሉ በኢያሱ 9 ተፅፎዋል።

ሙሴ- በፈርዖን ፊት ተአምራትን ሠራ፣ ነገር ግን ትንሽ በሚመስል ነገር ስላልታዘዘ እግዚአብሔር ሊገድለው ፈለገ። ይህም ትንሽ ነገር ልጁን ሳያስገርዝ መቅረቱ ነበር (ዘፀ 4፥24)። በዚህም ታማኝነት ሙሉ ለሙሉ መታዘዝን እንደሚያካትት ተማረ። ከዚያ በኋላ ሙሴ ታዛዥ ነበር፣ ምክንያቱም በዕብ 3፥5 በቤቱ ሁሉ እንደሉሌ የታመነ ነበር ተብሎ ተፅፎዋል። የሙሴ ታዛዥነት ሶስት ነገሮችን ይመለከታል 1) የፈርዖን የልጅ ልጅ እንዳይባል በእምነት እንቢ አለ (ዕብ 11፥24) በሌላ አባባል ከንጉሳውያን ቤተሰብ ደስታ ይልቅ የእግዚአብሔርን መንገድ መረጠ። 2) ከእግዚአብሔር ህዝብ ጋር መከራን መቀበል መረጠ። በመታዘዝ ያለን ታማኝነት የሚፈተነው በሰው አመለካከት ጎጂ የሆነ ውሳኔ መወሰን ሲኖርብን ነው። 3) የንጉሱን ቁጣ ሳይፈራ ግብፅን ተው። መታዘዝ እንዳንዴ አንዳንድ ነገሮችን ወደኋላ እንድንጥል ይጠይቀናል። ሙሴ እነዚህን ነገሮች ሁሉ እደረገ ምክንያቱም ታማኝ የጌታ አገልጋይ ሰለነበረ ነው።

ዳዊት- ታሳቅ የእምነት ሰው ነበር። ዳዊት እግዚአብሔርን እንደቃሉ መውሰዱና ቃሉን በታማኝነት እንደሚፈፅም ማመኑን በናዝብ ያነቃቃናል። ዳዊት በእስራኤል ሁሉ ላይ ንጉስ ይሆን ዘንድ በተቀባ ጊዜ እግዚአብሔር የዳዊት ቤትና መንግስት ለዘለዓለም እንደሚፀና ቃል ገባለት። ወዲያው ዳዊት በእግዚአብሔርም ፊት ገብቶ ተቀመጠ (2ሳሙ 16፥18)። በርግጥም ይህ ለዳዊት ታሳቅ የመንፈሳዊ መነቃቃት ጊዜ ነበር። ወዲያውኑ ያንን የተቀደሰ ቦታ ትቶ ቢሄድ በፍልስጤማውያን ላይ ታሳቅ ድል አገኘ።

እግዚአብሔር ለዳዊት የገባለት ቃል እውን ሆነ፣ ዙፋኑ ለዘላለም ለዳዊት ቤት ሆነ። መልእኩ ገብርኤል የኢየሱስን መወለድ ሲናገር እንዲህ አለ። "እርሱ ታሳቅ ይሆናል የልዑል ልጅም ይባላል፣ ጌታ አምላክም የአባቱን ዙፋን የሰጠዋል። በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘላለም ይነግሳል፣ ለመንግስቱም መጨረሻ የለውም" (ሉቃ 1፥32-33)። በኢየሱስ መወለድ እግዚአብሔር ለዳዊት የገባለት የታመነ ቃል ተፈጸሚ ሆነ።

ያዳዊት ኃያላን - ዳዊት በሠርነት ጊዜ ሰሳሰ በሚያህሉ ታማኝና ኃያላን ሰዎች ይረዱት ነበር (2ሳሙ 23፥8-9 ተመልከት)። ዳዊት በእስራኤል ላይ በተሾመ ጊዜ ሰዎቹን አልረሳቸውም። በተመሳሳይም ታሳቁ የዳዊት ልጅ ኢየሱስ ለእርሱ ምስክር ሆነው በታማኝነት መልካም የእምነት ተጋድሎ ያደረጉትን የእርሱ የሆኑትን አይረሳቸውም።

ዳንኤል - ሕይወቱ እደጋ ላይ በነበረ ጊዜ ሁሉ እንኳን ለጌታ ታማኝ ነበር። በታማኝነት እስት እስት ከጌታ ጋር ያለውን የዐሱት ጊዜ በመቀጠል ዘሚያደርገው ነገር ሁሉ ጌታን ይታዘዝ ነበር። ጠሳቶቹም በእርሱ ላይ እንከን ቢፈልጉም እንኳን ሊያስከስከው የሚችል ምንም አሳገኙበትም። ወደ ምርኮኛ ሆኖ ወደሌላ አገር ቢሄድም ለእግዚአብሔርና ለሀገሩ ታማኝ ነበረ። እግዚአብሔርም እርሱን በማዳንና በማክበር ታማኝነቱን አክብሮዋል፤ ይህም ታሪክ በዳንኤል ተጽፎዋል።

የንጉስ ኢዮአስ ንብረት ያገሮች - ታማኞች ሰለነበሩ ለሚያወጡት ነገር አይጠየቁም ነበር (2ነገ 12፥15)። በሌላ በኩል የንጉስ ኢዮአስ በረኞች ስበራተኞች በሚከፍሉት ነገር ታማኞች ሰለነበሩ አይጠየቁም ነበር (2ነገ 22፥7)። እዚህ በሁሉም ደረጃ ያሉ ሠራተኞች የህዝቡን ንንዘብ በጥንቃቄ በማስተዳደር የሚጠቀሱ ሁለት ግሩም ምሳሌዎች ናቸው።

የጰጲስ ኪዳን ሐዋርያት- መንፈስ ቅዱስ ከመሞሳቱ በፊት ጴጥሮስ በአንዲት ገረድ ፊት ጌታውን ካደ (ሉቃ 22፥54-60)፤ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ በተሞላ ጊዜ በሄደበት ቦታ ሁሉ በግልፅነት በኢየሩሳሌም አለቆች ፊት እንኳን በድፍረት እምነቱን መሰከረ (የሐዋ 4፥18-20)።

የሐዋርያት ሰራ ወይም መልእክቶችን በምናነብበት ጊዜ ወንጌልን ያበ ፍርሃት በሰደት ውስጥ የሰበኩ የታማኝነት ምሳሌ የሚሆኑንን ብዙ ሐዋርያትን እናያለን። የአብራውያን ዐህፊ ሰለ እምነታቸው ጠንካራ ምሥክርነት በዕብ 11 ላይ ፅፎዋል። ከአይሁድ ወገን የሆኑትን ከርስቲያኖች በጥንት ዘመን የነበሩትን ቅዱሳን ታሳቅ የሆነ ታማኝነት ያስታውሳቸዋል። ብዙዎቹ በታሳቅ ሰደት ውስጥ በማሰፍ ሰለ እምነታቸው መስዋዕት መሆናቸውን ቢገልጹ እንደሚከተለው ያጠቃለለዋል።

"እንግዲህ እነዚህን የሚያህሉ ምስክሮች እንደ ደመና በዙርያችን ካሉልን፣ እኛ ደግሞ ሸከምን ሁሉ ቶሎም የሚከበንን ኃጢአት አሰወግደን የእምነታችንንም ራስና ፈፃሚ ኢየሱስን ተመልከተን በፊታችን ያለውን ሩጫ በትእግስት እንሩጥ" (ዕብ 12፥1)።

12. ከተጠቀሱት ታማኝ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅዱሳን ሰዎች የምንማረውን አንድ ትምህርት ጥቀስ።

ሀ. ዮሴፍ
ለ. ኢያሱ
ሐ. ሙሴ
መ. ዳዊት

ሠ. የዳዊት ኃያላን
ረ. ዳንኤል
ሸ. ንጉስ ኢዮአስና ሠራተኞቹ
ቀ. የአዲስ ኪዳን ሐዋርያት



በግል ሕይወት መተርጎም

ዓላማ 6 ታማኝነታችንን ለእግዚአብሔርና ለሌሎች የምናሳይበትን መንገዶችና የታማኝነት ሽልማቶችን ለመግለፅ።

ታማኝነት የተባረከ የመንፈስ ፍሬ እንደመሆኑ መጠን ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ጋር፣ ከሌሎች ጋርና ከራሱ ጋር ላለው ግንኙነት በጣም ጠቃሚ ነው። እምነት የማመናችንና ከክርስቶስ ጋር ላለን ግንኙነት መሠረት እንደሆነ ሁሉ ታማኝነትም የአስተማማኝነታችንና ክርስቲያንን እንዲታመኑበት ሊያደርገው የሚችል መልካም ነገር ነው።

እግዚአብሔር ክእርሱ ጋር የሚራመዱና እርሱን የሚያገለግሉ ታማኝ ሰዎችን ይፈልጋል። "ክእኔ ጋር ይኖሩ ዘንድ ዓይኖቼ ሰምድር ምእመናን ላይ ናቸው፣ በቀና መንገድ የሚሄድ እርሱ ያገለግለኛል" (መዝ 101፥6)።

ለእግዚአብሔር ያለ ታማኝነት፦ በዘዳ 32 ሙሴ ከመሞቱ ሰፊት ባለው በመጨረሻው ቃሉቹ አሰራኤልን ከጌታ ጋር ባላቸው ግንኙነት ወደ ቁልቁል ስለሄዱና እግዚአብሔርን ሰላልታዘዙበት ብዙ እርምጃዎች አስጠንቅቆአቸዋል። የመጨረሻው ታማኝ ስላለመሆን ነበር (ቁ. 20)። ክጊዜ በኋላ ለነብዩ ኤርሚያስ የተነገረው ቃል ይህ ነበር፦

"በኢየሩሳሌም መንገድ እየተመላለሳችሁ ሩጡ፣ ተመልከቱም፣ እወቁም፣ በአደባባይዋም ፈልጉ ፍርድን የሚያደርገውን እውነትንም የሚሻውን ሰው ታገኙ እንደሆነ ይቅር እላታለሁ። . . .የእስራኤል ቤትና የይሁዳ ቤት በእኔ ላይ እጅግ ወንጅለዋል ይላል እግዚአብሔር"(ኤር 5፥1፣ 11)።

ካለመታመን ኃጢአት የተነሳ እስራኤላውያን በስተመጨረሻ ወደ ምርኮ ተወስደው ነበር። ምሳሌ 28፥20 "የታመነ ሰው እጅግ ይባረካል" በማለት ያረጋግጥልናል። በእጠቃላይ በእግዚአብሔር ላይ ያለን እምነት እክብሮትን፣ መታዘዘን፣ ራስን መስጠትን ያካተተ ቢሆን፣ የመጀመርያው ያለመታመንን የምንከላከልበት መከላከያም እርሱ ነው። ከሌሎች ጋር ባለን ግንኙነት ታማኝነትን ከማሳየታችን በፊት መጀመሪያ ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆን አለብን።

ታማኝነታችንን ከማሳየታችን በፊት ራሳችንን እንዲህ ብለን እንጥይቅ ይሆናል። ለጌታ ያለኝ ታማኝነት እርሱ ለእኔ ታማኝ የሆነውን ያህል ነውን? በታማኝነት ታጥቄያለሁን? ለእግዚአብሔር የገባሁትን ቃል እጠብቃለሁን? ፍቅሬን ለጌታ በመግለፅና ቃሌን በመጠበቅ ታማኝ ነኝን? ሰለወንጌል በፈቃደኝነትና በትእግስት መከራን እቀበላለሁን? ታዛዥና የሚታመንብኝ ባላደራ ነኝን ? እርሱ በሰጠኝ ንብረት ላይ ታማኝ ነኝን? እነዚህ ታማኝነትን ሊያነቃቁ የሚችሉ ጠቃሚ ጥያቄዎች ናቸው።

ለሌሎች ያለን ታማኝነት፦ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የሚገኘው የታማኝነት ፍሬ ባክባቢያችን ካሉት ሰዎች ጋር ሁሉ ያለንን ግንኙነት ይነካል። ሙሉ ለሙሉ ስንግግራችን፣ በድርጊታችን እምነትን በሚያሳይ ሁኔታ ታማኝ ሆነን ልንታይ ይገባል። ታማኝ ክርስቲያን ቃሉን ይጠብቃል፣ ያልተዛነፈ የክርስቲያናዊ ኑሮ ይኖራል፣ ጌታንም ደስ የሚያሰኝ ባህርይ ያሳድጋል። በቤቱ ቤተሰቦችን በመውደዱና ለእነርሱ መልካም በማድረግ ታማኝነቱን ያስረግጣል። ልጆቹንም ወጥ በሆነ መንገድ ያሰለጥናል። መልካምና የተከበረ ጎረቤት፣ አስሪና ሰራተኛ ይሆናል። በቤተክርስቲያን አምልኮ በመገኘትና መጋቢውንም በመደገፍ ታማኝ ይሆናል። የኢየሱሰንም ምሰሌ በመከተል ሌሎችን በሚያሰፈልጋቸው ነገር ያገለግላል። በሚያደርገው ነገር ሁሉ ታማኝ ከመሆኑ የተነሳ የክርስቶስ እነባል ትጠነክራለች፣ ትበረታታለችም።

ለራስ ያለ ታማኝነት፦ አንዲት ሴት ሚሲዮናዊ ለመሆን ወደ ደቡብ አፍሪካ ሄደች። በሬድዮ በተደረገላት ቃለ ምልልስም እዚያ ምን ለማድረግ እንዳሰበች ስትጠየቅ እንዲህ አለች። "እኔ እሆናለሁ ያልኩትን እሆናለሁ" አለች። ዘሌላ አባባል እርሷ እስመሰላይ የክርስቶስ ባርያ ለመሆን ሳይሆን እውነተኛና ታማኝ ለመሆን ነው። ስንቶቻችን ነን ያልሆነውን የምንሆነው? ሰራሱ ታማኝ የሆነ ሰው በሁለት ነገር የሚወላውል አይደለም። በመዝ 119፥113 ዳዊት "ዓመፀኞችን ጠላሁ፣ ህግህን ግን ወደድሁ" ብሏል።

ዘያዕቆ 1፥8 ላይ "ሁለት ሀሳብ ላለው ዘመንዱም ለሚወላውል ከጌታ ዘንድ አንዳች አያገኝም" ይላል። ጳውሎስ ዲያቆን ታማኝ (በሁለት ቃል የማይናገር) መሆን እንዳለበት ይናገራል (1ጢሞ 3፥8)።

የታማኝነት ሽልማት፦ ለሀገሃ ግንባታ ሰራው አንደ ሀላፊ ለለቀጠረ አንድ መሀንዲስ የተነገረ ታሪክ አለ። ይህ መሀንዲስ ጥራት ባለው አቃ የሚያማምሩ ቤቶችን በመሰራት የታወቀ ለው ነበር። ለብዙ ዓ መታት መሀንዲሱና ሀላፊው በጋራ በመሰራት ብዙ መልካም ቤቶችን ሰርተዋል።

በመጨረሻም መሀንዲሱ ቦተወሰነ ገንዘብ ለቀጠረው ለሀላፊው ሙሱ ሀላፊነት ለጥቶ አንደ ቤት እንዲገነባ ወሰነ። ቤቱም እንደወትሮው ጥራት ባለው አቃ መገንባት ነበረበት። በዚህን ጊዜ ግን ሀላፊው ሰራውን ብቻውን ያለተቆጣጣሪ እንዲሰራ ሆነ። ሃላፊውም እንዲህ ሲል አሰበ ። አነስተኛ ጥራት ያለው አቃ ተጠቅሞ ቤቱን ቢሰራ ቤቱ ያው በመልክ አይለይም፣ ማንም ልዩነቱን አያውቅም። እንዲህ በማድረግ ብዙ ገንዘብ ለግሱ ለመውሰድ ወሰነ።

ቤቱም ተገንብቶ እንዳለቀ፣ ሀላፊው መሀንዲሱን የሰራውን ቤት እንዲያይለት በኩራት ጠራው። በጣም የሚያምር ቤት ነበር፣ ውሰጡ ግን ለማይረባ አቃ መበራቱን የሚያውቀው ሀላፊው ብቻ ነበር። እንግዲህ ምን ያህል እንደሚያሰደነግጥ አሰበው። መሀንዲሱ ቤቱን ለሀላፊው ብዙ አመት ሰላገለገለ እንደ ሰጦታ በጠው። ሃላፊውም በልቡ እንዲህ አለ። ይህ ቤት ለእኔ እንደሆነ ባውቅ ኖሮ ጥራት ባለው አቃ እገነባው ነበር። አሁን ግን ጊዜው አልፎዋል፣ ስለዚህ በዚሁ በገነባሁት ቤት እኖራለሁ።

አስታውስ፣ "የታመነ በው እጅግ ይባረካል" (ምሳ 28፥20)። በሕይወቱ የታማኝነት ፍሬ ያለው ለው ጌታ እንዲህ ሲለው ይሰማል። "መልካም፣ አንተ በጎ ታማኝም ባርያ" (ማቴ 25፥21)። ነገር ግን ያልታመነው ባርያ ወደ ውጭ ይጣላል። "በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጡት በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል" (ማቴ 25፥30)።

ሐዋርያው ጳውሎስ በመንፈስ ስለመኖር የሚናገረውን ሲያጠቃልል የገላትያ ሰዎችን እንዲህ ሲል ይመክራቸዋል። "እትሳቱ፣ እግዚአብሔር አይዘበትበትም። ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና፣ በገዛ ሰጋው የሚዘራ ከሰጋ መበሰበሰን ያጭዳልና፣ በመንፈስ ግን የሚዘራው ከመንፈስ የዘላለምን ሕይወት ያጭዳል" (ገላ 6፥7-8)። የታማኝነት ሽልማት የዘላለም ሕይወትና የጌታ ማበረታቻ ነው።

(13). በማሰታወሻ ደብተርህ ለጌታ፣ ለሌሎች ሰዎችና ለራስህ ታማኝነት የምታላይባቸውን መንገዶች ግለፅ። ይህንን የትምህርት ክፍል ከልሰና የበለጠ ታማኝ ልትሆን የምትችልባቸውን መንገዶች ፃፍ።

(14). ጥቂቶቹ የታማኝነት ሽልማቶች ምን ምን ናቸው?

(15). *ያለመታመን* ምላሹ ምን ምን ናቸው?

የመከራ ፈተና

ምርጫ። ትክክለኛ የሆነውን አንድ መልስ ለአያንዳንዱ ጥያቄ ምረጥ።

1. ታማኝነትንና ፍቅርን በተመለከተ የሚናገረው መርህ

ሀ. ፍቅር ከታማኝነት ይልቅ ጠቃሚ ነው።
ለ. ፍቅር በታማኝነት ይረጋገጣል።
ሐ. ታማኝነት ከፍቅር ይልቅ ጠቃሚ ነው።
መ. አንዱ ካለ ሌላው አይሰራም።

2. ከእነዚህ ውስጥ አንዱ የተፈጥሮአዊ እምነት ምሳሌ ነው።

ሀ. ኢየሱስን እንደ ግል አዳኝ መቀበል።
ለ. ሰው እንዲፈወስ መፀለይ።
ሐ. በእውቶበስ ተሳፍሮ መሔድ።
መ. የተወሰነ ሀይማኖታዊ አስተሳሰብ መያዝ።

3. በመከራ የሚፈተን ታማኝነት

ሀ. ዕናት ነው።
ለ. ፍርሀት ነው።
ሐ. መጽሄም ነው።
መ. የክርስም ስሜት ያለመኖር ነው።

4. ከእነዚህ ውስጥ የትኞቹ መወገድ አለባቸው?

ሀ. ታል መግባት።
ለ. ታል መግባት እና ታልን መጠበቅ።
ሐ. ታል መግባት እና ታልን አለመጠበቅ።

5. ከድነት በኋላ የምንለማመደው በጌታ ላይ ያለን የማይናጋ ዕኑ እምነት ምን ይባላል?

ሀ. የእምነት ስጦታ
ለ. ህያው እምነት
ሐ. የእምነት ፍሬ

6. አለመለየተ ወይም አለመዛነፍ ማለት

ሀ. ታማኝ መሆን
ለ. ለጌታ አበራትን መስጠት
ሐ. እውነተኛ መሆን
መ. የጀመርከውን መቀጠል

7. በአዲስ ኪዳን ውስጥ የትኞቹ ታላቶች ናቸው ሁለቱንም ማለትም የእምነት እና የታማኝነት ትርጉም የሚለጠት?

ሀ. አሜናዊ
ለ. አሜን
ሐ. ኢሙን
መ. ፒስቲስ

8. በላይራኑት ማለት

ሀ. የእምነትን ስውታ መሰማመድ ነው።
ለ. የሌላውን ሰው ንብረት ማስተዳደር ነው።
ሐ. በስደት ያለማጉረምረም መፅናት ነው።
መ. እጅ በመጨባበጥ ውልን ማረጋገጥ ነው።

9. በምን መስረት ነው ተጠያቂዎች የምንሆነው?

ሀ. ጌታ የሰጠንን እንዴት እንደምንጠቀምበት
ለ. ምን ያህል ለጌታ እንደሰጠነው
ሐ. እኛ የሰጠነውን ሌሎች ከሰጡት ጋር በማነፃፀር

10. ያለመታመን ምላሽ ምንድን ነው?

ሀ. ጥቂት በረከቶች
ለ. በማያምኑ መሰደድ
ሐ. ወደ ጨለማ (ሲኦል) መጣል
መ. የበላለም ሕይወት

11. ከእነዚህ ውስጥ የትኛው ነው ያልተባነፈ ታማኝነት ምሳሌ?

ሀ.ሙሴ ለ. ዳንኤል ሐ. ጴጥሮስ

12. ለራስህ ታማኝ መሆን ማለት

ሀ. የራስህን ፍላጎት ከሌሎች ፈላጎት በፊት ማስቀደም ነው።
ለ. ለሌሎች ምሳሌ ለመሆን ታማኝ መሰሉ መታየት ነው።
ሐ. ራስህን ለመከላከል እስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወላዋይ መሆን ነው።
መ. ያልከውን መሆን ነው።

13. ከእነዚህ ውስጥ የክርስቶስ ወንጌል የሆነውን የጌታን ሁበት ለሌሎች ማካፈልን የሚመለከተው የትኛው ነው?

ሀ. ንስሀ
ለ. ትህትና
ሐ. መጋቢነት
መ. የሚያድን እምነት

14. በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በሕይወትህ ውስጥ ከተፈጠረ በኋላ የሚያድገው የትኛው ነው?

ሀ. የሚያድን እምነት
ለ. የእምነት ፍሬ
ሐ. ተፈጥሮአዊ እምነት
መ. የእምነት ስጦታ

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስ

8. በ1ተሰ 5:24 ያለው ተስፋ፣ የሚጠራችሁ የታመነ ነው፣ እርሱም ደግሞ ያደርገዋል።

1. ሀ. 4 ሐ. 6 ሠ. 3
ለ. 1 መ. 5 ረ. 2

9. (እቀማመጡ የትኛውም ሲሆን ይችላል) ቃሉን ለመጠበቅ፣ ይቅር ለማለትና ለመጥራት

2. የአንተ መልስ። ጸንቶ የቆመ፣ እውነተኛ፣ በእግዚአብሔር ስለመታመኑ እርግጠኛ የሆነ ማለት ይቻላል።

10. ሐ

3. ሀ. እምነት፣ ታማኝነት፣ ማመንና መታመን
ለ. ማመን
ሐ. እምነት እና ታማኝነት
መ. እውነተኝነት

11. ሀ. 6 ሐ. 2 ሠ. 1 ሸ. 5
ለ. 3 መ. 6 ረ. 5 ቀ. 4

4. ሀ. እውነት ሐ. እውነት ሠ. እውነት
ለ. ሐሰት መ. ሐሰት

12. የአንተ መልስ። ይህ መልስ የምሰጥበት መንገድ ነው።

ሀ. ታማኝ ክርስቲያን በማንኛውም ሁኔታ ይታመናል።
ለ. ታማኝ ክርስቲያን ሁልጊዜ ቃሉን ይጠብቃል።
ሐ. ታማኝ ክርስቲያን ለእግዚአብሔር ታዛዥ ነው።
መ. ታማኝ ክርስቲያን ቃል የገባውን ይፈፅማል።
ሠ. ታማኝ ክርስቲያን ሁልጊዜ ለጌታው ታዛዥ ነው።
ረ. ስዎች የፈለጉትን ቢያደርጉትም ታማኝ ክርስቲያን ላመነበት ነገር በፅናት ይቆማል።
ሸ. ታማኝ አገልጋይ የሌላውንም ሆነ የህዝቡን ገንዘብ በታማኝነት ይይዛል።
ቀ. ታማኝ አገልጋይ ስደት ቢያስከትልም እምነቱን በግልፅ ይመሰክራል።

5. ኢሳ 11:5

13. የአንተ መልስ። ይህ ጠቃሚ የሆነ ራስን መመዘኛ ስለሆነ በጥንቃቄ ለመመርመር ጊዜ ውሰድ።

6. ራሱን ለማስደሰት ብቻ የሚኖር ሰው ይጠፋል። እግዚአብሔርን ለማስደሰት የሚኖር ሰው ግን የዘላለም ሕይወት ያገኛል።

14. ከእነዚህ ውስጥ የትኛውም ሊሆን ይችላል። ከጌታ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት፣ የዘላለም ሕይወት፣ በታማኝነት መታወቅ፣ እውነተኝነትና ብዙ ሰረከት።

7. *መመለከርና እምነት*

15. እግዚአብሔር የማይታሉትን ለምች ወደ ጨለማ (ሲኦል) ይጥላቸ ዋል፣ ሌሉችም ለምች እያምኑትም፣ በራሱም ተስፋ ይቆርጣል።

8 ገርነት
የመገዛት ፍሬ

ትምህርት

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ለእርግብ መመሰሉ፣ ኢየሱስም በበግ መመሰሉ እና ለተከታዮቹም የበጎች ስያሜ መሰጠቱ የሚያስደንቅ ግጥምጥሞሽ ነው። እነዚህ ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ የመገዛት ፍሬ የሆነው የገርነት (የየዋሃት) ምልክቶች ናቸው።

ኢየሱስ በዮርዳኖስ ወንዝ በተጠመቀ ጊዜ በእርሱ ላይ መንፈስ ቅዱስ የወረዳው በእርግብ አምሳል ነበር። መልእክተኛውም መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስን ያስታወቀው ኃያልና እሽናፊ ብሎ ሳይሆን የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ብሎ ነበር (ዮሐ 1፥35)። ራሱን የሚሰዣቱ ባህርይ በኢሳያስ መጽሐፍ ውስጥ እንዲህ በማለት ተጠቃልሎ ይገኛል። "ተጨነቀ ተስቃየም አፉንም አልከፈተም፣ ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት፣ በሸላቶቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ፣ እንዲሁ አፉን አልከፈተም" (ኢሳ 53፥7)። "ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም መከራንም ሲቀበል አልዛተም፣ ነገር ግን በፅድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ" (1ጴጥ 2፥23)።

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን በበግ ስም ጠርቷቸዋል። "መልካም እረኛ እኔ ነኝ፣ የራሴን በጎች አውቃለሁ የራሴም በጎች ያውቁኛል ነፍሴንም ስለ በጎቼ እሰጣለሁ" (ዮሐ 10፥14-15)። በጎች ሰላማዊና ታዛዥ እንስሳት ናቸው። በመንፈስ የተሞላ እና የገርነት (የየዋሃት) የመንፈስ ፍሬ የሚታይበት ክርስቲያንም ለጌታው የሚገዛና የሚጠቅም ነው።

ይህ ትምህርት የገርነት (የየዋሃት) የመንፈስ ፍሬ ጠቃሚነትን እንድትረዳ ይረዳሃል። እንደ ታማኝ በግ ጌታህ ወደሚመራህ ቦታ እንድትከተለው እመኝልሃለሁ።

የክፍለ ትምህርቱ እከፋፈል

- የገርነት ምንነት
- ገርነት ሲገለፅ
- ገርነት በምሳሌ

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህንን ትምህርት ስታጠናቅቅ የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ መቻል ይኖርብሃል።

- የመንፈስ ፍሬ የሆነውን የገርነትን (የየዋሃት) ዋና ሀሳብ (ፕራሉቴስ) መግለፅ።
- ለእያንዳንዱ የገርነት (የየዋሃት) ገፅታዎች ምሳሌ መሰጠት።
- በየእለቱ አገለግሎትና ምስክርነት ውስጥ የገርነት (የየዋሃት) መመሪያዎችን መጠቀም።

1. ያለፉትን ትምህርቶች ስታጠና ስነስረስት መልክ ይህንንም ትምህርት አጥና። የጥናት ማጠናክሪያ ጥያቄዎች ሁሉ መልስ፣ የትምህርቱን ዓላማዎች መፈጸምህን እርግጠኛ ሁን።
2. የተጠቀሱትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አንብብ፣ የማታውቃቸውን ቁልፍ ቃላቶች ፍቺ ፈልግ።
3. የሙክራው ፈተናን ሥራና መልሶችህን አመሳክር።

የግርጌች ምጣኔች

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ፍቺ

ዓላማ 1 የፕራኦተስን ወይም ገርነትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አጠቃቀም ጠቅለል አድርጎ ስማስቀመጥ።

የመንፈስ ፍሬ ግን፣ ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትእግስት፣ ቸርነት፣ ስነነት፣ ታማኝነት፣ ገርነት . . . ነው (ገላ 5፥22-23)።

በገላ 5፥23 የተጠቀሰው ገርነት ፕራኦተስ ከሚለው ከግሪክ ቃል የመጣ ነው። ከውጪያዊ ድርጊት ይልቅ ውስጣዊ ባህሪ ስመሆኑ ከሁሉም ባህርያት የበለጠ ገርነትን መግለፅ ያስቸግራል። ሶስቱ የገርነት ዋና ሀሳቦች የሚከተሉት ናቸው።

❶. *ለእግዚአብሔር ፈቃድ መገዛት* - ኢየሱስ በማቴ 11፥29 የተናገረው ይህንኑ ነው። "ቀንበሬን በላያችሁ ተሸክሙ ከእኔም ተማሩ፣ እኔ የዋህ በልቤም ትሁት ነኝና፣ ስንፍሳችሁም እረፍት ታገኛላችሁ" ኢየሱስ በዚህ ስፍራ ላይ ገርነት (የዋህነት) እና ትህትና እንዳለው ገልጿል። እነዚህ ሁለቱም ራሱን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ያስገዛ ሰው ባህርያት ናቸው።

❷. *የመማር መንፈስ* - ይህ ስመማር ፈቃደኛ መሆን ወይም ለመማር ያስመታበይን ያባያል። ያዕ 1፥21 ይህንን እንዲህ ይስዋል። "ንፍሳችሁን ማዳን የሚችለውን በውስጣችሁም የተከከለውን ቃል በየዋህነት ተቀበሉ"

❸. *ለሳቢነት* (Considerate) - ፕራኦተስ የሚለው የግሪክ ቃል አብዛኛውን ጊዜ ለሌላው ማስብን፣ ልከኝነትን፣ እርጋታን፣ መንከባከብን ወይም ከፍቅር የተነሳ መሸካከምን ስማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል።

ገርነት የጨካኝነት ተቃራኒ ነው። ይህም ደካማ ሳይሆኑ ወይም የዝቅተኝነት ስሜት ሳይሰማ ልከኛና ስላማዊ መሆን ማለት ነው። ገርነት ከፈሪነት ጋር የሚያያዝ ነገር አይደለም፣ ይልቁንም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከብርታት፣ ከጥንካሬና ከመፍትሔ ጋር ይያያዛል። ሙሴ

ሰጣም የዋህ ሰው ነው፣ በችግር ጊዜ ግን ለመንቀሳቀስና ውሳኔዎችን ተግባራዊ ስማድረግ ዝግጁ ነው።

ፕራኦተስ በልብና በአእምሮ የመንፈሳዊነት ባህሪን መሳበስንና የኃይልን ፍሬ የሚገልጽ መሆኑን መረዳት ጠቃሚ ነው። በገላ 6፥1 ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ይላል። "ወንድሞች ሆይ፣ ሰው በማናቸውም በደልስ እንኳን ቢገኝ፣ መንፈሳዊያን የሆናችሁ እናንተ እንደዚህ ያለውን ሰው በገርነት መንፈስ አቅኑት፣ እንተ ደግሞ እንዳትፈተን ራስህን ጠብቅ" በመጽሐፍ ትዳብ አባባል መንፈሳዊ መሆን ማለት ከሰው መንፈስ ይልቅ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር መሆን ማለት ነው። ስነጢሞ 6 በቁ. 11 ጳውሎስ የተናገረው ይህንኑ ነው፣ የእግዚአብሔር ሰው ከሁሉ ነገር የስለጠ ገር መሆን እስበት። ስሚቀጥለው ቁጥር ጳውሎስ ጢሞቴዎስን መልካሙን የእምነት ገድል ተጋደል ብሎታል (ቁ.12)።

ገርነትና ዕናት ጎን ለጎን ይሄዳሉ። ፈረንሳዮች እንዲህ የሚል አባባል አላቸው። "ሰው ከከፋይ ጨርቅ የተበራ ጓንት (የእጅ ሹራብ) የለበሱ የብረት እጆች ሊኖረው ይገባል።" ጳውሎስ ራሱ የራሰዋን ልጆች እንድምትንከባከብ ሞግዚት የዋህ ነበር (1ተስ 2፥7)። ነገር ግን የቆሮንቶስ ሰዎች እንዶ ክርስቶስ ሐዋርያ መንፈሳዊ ስልጣኑን ጥያቄ ውስጥ ባስገቡ ጊዜ እንዲህ ሲል ጠይቋቸው። "ምን ትወዳላችን? በስትር ወይስ በፍቅርና በየዋሃት መንፈስ ልምጣባችሁን?" (1ቆሮ 4፥21)። የመንፈስ ፍሬ እንዳፈራ ሰው ሁስቱንም ገርነትንና ዕናትን አብሮ ይዛል።

(1). የመንፈስ ፍሬ ስለሆነው ገርነት የሚገልፁት ትክክለኛ የሆኑት ዐ ረፍተ ነገሮች የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ፕራኦተስ የሚለው ቃል አብዛኛውን ጊዜ የሚገልፀው የእንደን ሰው ውጭያዊ ባህሪይ ነው።
ለ. ገርነት በገላ 5፥23 ባለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከት መታዘዝን፣ ስመማር ፈቃደኛ መሆንንና ለሌሎች እሳቢነትን ያካትታል።
ሐ. ገርነት ማለት ደካማነት ወይም የዝቅተኝነት መንፈስ ነው።
መ. ገርነትንና ዕናትን በእንድነት መያዝ ይቻላል።
ሠ. በገላ 6፥1 እንደተጠቀሰው ስበደል የተገኘውን ሰው ስመመስስ የገርነት መንፈስ ያስፈልጋል።
ረ. ትህትና እንዱ የገርነት ገፅታ ነው።
ስ. መንፈሳዊ ሰው በደሰኛውን ሰው በገርነት መንፈስ ካቀናው ራሱ ከመፈተን ነፃ ይሆናል።

ምድራዊ ፍቺ

ዓላማ 2 የፕራኦተስን ምድራዊ ፍቺዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ ፍቺዎች ጋር በማነፃፀር ተመሳሳይነታቸውን ለመፈስግ።

ዜኖፖን (434-355 ዓ.ዓ) የታሪክ ሰው ፀሀፊ እና ወታደር ነበር። ፕራኦተስን ሰረጅም ጊዜ ሰውጊያ ላይ በሚኖሩ ወታደሮች መካከል

የሚታየውን የሰውን የወንድማማች መግባባትን ለመግበጽ ተጠቅሞበታል።

ፕሳቶ (427-355 ዓ.ዓ) በጣም አዋቂ የሆነ የግሪክ ፈላሰፋ ነበር። ፕራሉተስን የተጠቀመው ትህትናና ብርታትን ለመግለጽ ሲሆን እነዚህ ሁለቱ ነገሮች የበው ዘርን ሁሉ በእንድነት የያዙ ናቸው። ደግሞም ቃሉን ፈረበን ለጌታው ጥቅምና ፍሳጎት መግራት እንደማለት ነው ሲል ተጠቅሞበታል። በተገራ ቁጥር በጣም ጠንካራና ጠቃሚ ይሆናል። የሰውነታችን ጡንቻዎች ለራ በተለማመዱ ቁጥር ጠንካራ ይሆናሉ። ምናልባትም ኢየሱስ ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ ሲል በውስጡ የነበረው ይኸው ሃሳብ ይሆናል (ማቴ 11፥29)።

ሶቅራጥስ (470-399 ዓ.ዓ) ሌላው ብሩህ የግሪክ ፈላሰፋ ነበር። ፕራሉተስ ተሚለውን ቃል ጨዋትን ወይም ገርነትን ከበድብ ጋር ለማነፃፀር ተጠቅሞበታል። እንደገናም ከተገሩ በኋላ በርዓትን ሰሚይዙ እንስሳት ተጠቅሞበታል።

አሪስቶትል (384-322 ዓ.ዓ) ሌላው ታላቁ የግሪክ ፈላሰፋ ነበር። በእርሱ አገላለጽ ፕራሉተስ በኃይለኛ ቁጣና ለቁጣ መነሳት ነገር ግን የነኃለሰ የቁጣን ሰሜት ባለማሳየት መካከል ያለ ሚዛንን ያመለክታል። በሌላ አገላለጽ ፕራሉተስ በአርስቶትል አባባል ሁልጊዜ ተገቢ በሆነ ጊዜ የሚቆጣና ተገቢ ባልሆነ ጊዜ ግን የማይቆጣ ሰው አድርጎ ይመለከተዋል። ይህም የቁጣን ሰሜት መቆጣጠር ነው።

እነዚህ ምድራዊ ፍቺዎች ሐዋርያው ጳውሎስ የተጠቀመበትን ፕራሉተስ የሚለውን ቃልና ገርነት የምንለውን የመንፈስ ፍሬን የተሻለ እንድንረዳ ይረዳናል።

(2). ከሚከተሉት ምድራዊ ፍቺዎች ውስጥ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ፍቺ ጋር ሊነፃፀር የሚችለውን ፈልግና ፃፋቸው።

ሀ. ኃይሉን ሰጌታው ጥቅምና ፍሳጎት የሚያውል የተገራ ፈረስ።
ለ. ትህትናና አሳቢነት።
ሐ. በወታደሮች መካከል ያለ ወንድማዊ መግባባት።
መ. በብዙ ቁጣና በጥቂት ቁጣ መካከል ያለ ሚዛን።

ገርነት ሲገለፅ

የእግዚአብሔር ገርነት

ዓላማ 3 ከኢየሱስ ገርነት የተማርከውን ምሳሌያዊ ትምህርት ለመግለጽ።

ገርነት አስፈላጊ የሆነ የክርስቶስ ተከታይ የክርስቲያን ምልክትና ባህሪ ነው፣ ምክንያቱም እያንዳንዱ ክርስቲያን የተወለደው ከመንፈስ በመሆኑና የመንፈስ ማደርያ በመሆኑ ነው። የእኛ ጌታ የዋህ አምላክ ነው። ለምንድን ነው ታድያ መገሙሪኛው እግዚአብሔርን በየዕበቱ

የሚቆጣ ጻድቅ አምላክ አድርጎ የሚያቀርበው በምንድን ነው? የእግዚአብሔር ቁጣ ሁልጊዜ በኃጢአትና በክፋት ሳይ በሰሆነ ለእኛ ያለው ፍቅርና ርህራሄ እደበወጥም። ይህ መለኮታዊ ገርነት ነው። የበው ቁጣ ብዙ ጊዜ ኃጢአት አበው፣ በበዘሀም ነው በኤፌሶን 4፥26 ላይ ያበው ቃል የሚያስጠነቅቀን። "በቁጣችሁ ሳይ ዐሐይ እይግባ" እንዲሁም "ክፉውን ነገር ተጻየፉት" ይላል (ሮሜ 12፥9)። እግዚአብሔር ፍፁም ለሆነ ገርነትና ፅናት ምሳሌያችን ነው።

ኢየሱስ ትሁትና የዋህ ነበር (ማቴ 11፥29)፣ ይህ ማለት ግን ክፉውን ነገር እይቃወምም ማለት አይደለም። ባበፈው ትምህርታችን ኢየሱስ በመቅደስ በሬዎችን፣ በጎችንና ርግቦችን የሚሸጡትንና ገንዘብ ለዋጮችንም የገመድ ጅራፍ አበጅቶ ሁሉን ከመቅደስ እንዳበወጣቸው ተመልክተናል (ዮሐ 2፥15-18)። መቅደሱን የሚያረክሱትን በኃይል አበወጣ። በሌላ ጊዜ በገዘሙት የተያዘችውን ሌት ይቅር አሰ (ዮሐ 8፥10-11)። የመንፈስ ፍሬ የሆነውን ገርነት ከጥንካሬ ጋር መያያዙን ምሳሌ ሆኖ አሳየ። ገርነት ከደካማነት ጋር እይያያዝም።

ኢየሱስ በቤተ ክርስቲያን ዘመን ገርነት ዋነኛ የደቀ መዝሙር ምልክት እንደሆነ አስተምሮአል። የሳምራውያን ሰዎች ኢየሱስን ባልተቀበሉት ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ እንዳንዶቹ ከሰማይ እሳት እንጥራና ያጥፋቸውን ብለው ጠይቀውት ነበር። ኢየሱስ ግን እንዲህ ሲል ገለፀባቸው። "ምን አይነት መንፈስ እንደሆነባችሁ እታውቁም የለው ልጅ የሰውን ነፍስ ሊያድን እንጂ ሊያጠፋ አልመጣም" አሰ (ሉቃ 9፥55-56)። በሌላ አባባል ደቀ መዛሙርቱን የነገራቸው የወንጌል መልእክት የመንፈስ ቅዱስ የሆነ አገልግሎት መሆኑንና በገርነትም የሚደረግ አገልግሎት መሆኑን ነው (2ቆሮ 3፥8 ተመልከት)።

የኢየሱስ ገርነት በዮሐ 13፥5 ላይ በሚያስደንቅ ሁኔታ ተገለጿል። ኢየሱስ የደቀ መዛሙርቱን እግር በማጠብና ራሱን ገብ በማድረግ የአገልጋይነትን መንፈስ ይዘው እንዲያገለግሉ ምሳሌ አሳያቸው።

ኢየሱስ በእርሱ ላይ በመንፈስ ቅዱስ ያበው ገርነት በሚገባ የታየው ወደ መበቀል ሊሄድ ባለበት በመጨረሻዎቹ ሰዓታት ነበር። መከራና ሞት ቢጠብቀውም እንኳን ዐሉቱ ራሱን ሙሉ በሙሉ ሰእጣቱ ፈቃድ መስጠት ነበር (ማቴ 26፥39)። በተያዘበት ጊዜ ከአሰራ ሁለት የሚበልጡ የመላእክት ጭፍሮች ሊጠራ ይችል ነበር፣ ነገር ግን በፈቃደኝነት ራሱን ለወታደሮቹ ሰጠ (ቁ.50-54)። በሊቀ ካህናቱና በሸማግሌዎች በተከሰሰ ጊዜም ለእንዳም ክበ መልስ አልመለሰም (ማቴ 27፥14)። ሀላለማዊ የሆነው የእግዚአብሔር በግ በፍቅርና በየዋሃት መንፈስ የበውን ልጆች ኃጢአት ሁሉ ለማንፃት ራሱን በፈቃዱ በጠ። በየዋህነት መበቀል ላይ ሆኖ የበቀሉትን እንኳን ይቅር አላቸው።

(3). በመለኮታዊ ገርነት (የዋህነት) ውስጥ የቁጣን ስፍራ ግለፅ።

(4). የኢየሱስን ታዛዥነት ምሳሌ በጥ።
5). የኢየሱስን ትህትና ምሳሌ በጥ።

(6). ከኢየሱስ ገርነት ልንማራቸው የምንችሳቸውን ሶስት ምሳሌዎች ጥቀስ?

መጽሐፍ ቅዱሳዊ የገርነት ምሳሌዎች

ዓላማ 4 ገርነትን የሚመለከተውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን እውነት የሚያጠቃልሉትን አረፍተ ነገሮች ሙሉ ለማድረግ።

ብዙ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ገርነት ከሌላ ባህርያት ጋር ይያዛል ወይም የመጥፎ ተግባሮች ተቃራኒ ነው። እነዚህ ማነጻጸሪያዎች በሕይወታችን በሰሚገለፀው የገርነት ፍሬ ጠቃሚ መመርያ ይሰጡናል። እነዚህንና ለእኛ የሚሰጡንን መልእክቶች እንመለከታለን።

ገርነትና ኃጢአት ሲነፃፀር - "እግዚአብሔር የዋሃንን ያነሳል፣ ኃጢአተኞችን ግን እስከ ምድር ድረስ ያዋርዳል" (መዝ 147፥6)። በዚህ ምንባብ ውስጥ ያለው ገርነት ወይም ገር የሚለው የእብራይስጥ ቋንቋ ቢተረጎም ትሁት የሚል ትርጉም ይሰጣል። እዚህ መዝሙረኛው የዋህን ሰው ከክፉ ሰው ጋር ያነጻጽረዋል። የዋህ ወይም ትሁት መንፈስ ኃጢአት ላይ ተፅእኖ አለው። የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሆነው የዋህነት በሕይወታችን ውስጥ ኃጢአትን ይከላከላል።

ገርነትና የዋህነት - በ2ቆሮ 10፥1 ሐዋርያው ጳውሎስ የቆሮንቶስ ሰዎችን እንዲህ ሲል ይመክራቸዋል። "በክርስቶስ የዋህነትና ገርነት እለምናችኋለሁ በዚህ ክፍል የዋህነት መጓዳትን ያለምሬትና በትእግስት መቀበልን ያመለክታል። ገርነት ማለት በጠባይ ምቹ ወይም ለሰላሳ መሆን ሊሆን ይህም የክፋት፣ የግትርነት፣ የኃይለኝነትና የጨካኝነት ተቃራኒ ነው። ጳውሎስ በዓለም እንዳለው ዓይነት ኑሮ የሚኖሩትን በኃይለኝነት አልመጣባቸውም፣ ነገር ግን ወንጌልንና አገልግሎቱን ከምንም በላይ ለመከላከልና ለመጠበቅ ዝግጁ ነበር። አቀራረቡም ክፉ የሚሰሩትን በታዛዥነትና በትህትና መንፈስ መልካም እንዲሰሩ እድል ለመስጠት በወንድማዊ ፍቅር ነበር።

ገርነትና ትህትና - ገርነት ከትህትና ውጪ የሆነ ነገር አይደለም። ኤፌሶን 4፥2 እንዲህ ይላል። "በትህትና ሁሉና በየዋህነት በትእግስትም እርስ በርሳችሁ በፍቅር ታገሱ።" ትሁት መሆን ማልት የትዕቢተኝነት ወይም የትምክህተኝነት ተቃራኒ ነው። ይህም የመገዛትና ለሌሎች የማስብ መንፈስ ነው።

ገርነትና ጥበብ - "ከእናንተ ጥበበኛና አስተዋይ ማን ነው? በመልካም እንዋዋሩ ስራውን በጥበበ ያሳይ" (ያዕ 3፥13)። ፕራእተስ የሚለው ቃል በገላ 5፥23 ውስጥ ገርነት ተብሎ የተተረጎመው በዚህ ክፍል ውስጥ ጥበብ ተብሎ ተተርጉሞዋል። ጥበበኛ ለው ትሁትና ገር ነው። እንደገናም ይህ የገርነት ፍሬ ማረጋገጫ የሆኑት መገዛትንና ለመማር መውደድን ያሳያል።

ገርነትና ዝግታ (ዐጥታ) - በ1ጴጥ 3፥1-6 ሐዋርያው ሚስቶችን ለባሎቻቸው እንዲገዙ ይመክራቸዋል። የማያምኑ ባሎች ቢኖሩ

በሚሰቶቻቸው ውስጥ የሚታየውን ንጽህናና አክብሮት በመመልከት ወደ ጌታ ሊመጡ እንደሚችሉ ያሳስባቸዋል። ጴጥሮስ በዚህም ላይ ጨምሮ የሚሰቶች እውነተኛ ውበት በውጪ ወይም ከላይ ተሽሞንሙኖ መታየት ሳይሆን "በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ የከበረ፣ ገርና ጭምት መንፈስ ያለበት፣ ምንጊዜም የማይጠፋ የውስጥ ለውነት ውበት ይሁን" ይላቸዋል። ፕራእተስ የሚለው ቃል የማረጋጋት ወይም ጸጥ የማድረግንም ሃሳብ የሚጨምር ነው። ይህ ክፍል የተፃፈው ለሚስቶች ቢሆንም መመርያው ግን ለሁሉም ይሰራል። የዋህና ረጋ ያለ መንፈስ ከክርክርና ከውጭያዊ ሀይማኖት ይልቅ የማያምኑትን ወደ ክርስቶስ ይስባል።

ገርነት ድኅነት "እግዚአብሔር በዘገዘው ተደስቶአልና፣ የዋህንንም በማዳኑ ክፍ ከፍ ያደርጋልና" (መዝ 149፥4) በዚህ የብሉይ ኪዳን ክፍል ውስጥ የዋህ የሚለው ቃል በእብራይስጡ ትሁት የሚልም ትርጉም አለው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይህንኑ ነገር እንመለከታለን። "ስለዚህ ርኩሰትን ሁሉ የክፋትንም ትርፍ አስወግዳችሁ፣ ነፍሳችሁን ማዳን የሚችለውን በውስጣችሁም የተተከለውን ቃል በየዋህነት ተቀበሉ" (ያዕ 1፥21)። በዚህ ክፍል ውስጥ የዋህነት የሚለው ቃል የተተረጎመው ፕራኦተስ ከሚለው ቃል ነው። ይህም ማለት ከመንፈስ የሆነ የዋህነት ለእግዚአብሔር ራሳችንን እንድንሰጥ የሚያደርገንና ቃሉ በውስጣችን እንዲያድግ ከዚያም ብዙ ፍሬ እንድናፈራ የሚያደርገን ነው። ማቴ 13 ዘር ዘልቆ ሊገባበት ስላልቻለው ጠንካራና ደረቅ መሬት ይናገራል። በእግዚአብሔር ላይ ካለ አመመኝነት የተነሳ ልብም እንዲሁ የእግዚአብሔርን ቃል የማያስገባ ሊሆን ይችላል። ትሁት ልብ በየዋህነት የለሰለሰና የሚመጣውን የእግዚአብሔር ቃል የሚቀበል ነው።

የዋህነትና ምሪት - "ገሮችን በፍርድ ይመራል፣ ለገሮችም መንገድን ያስተምራቸዋል" (መዝ 25፥9)። ይህ ምሪት በሁለት መንገዶች ነው። ይህም በሰዎች ፊት እና ወደ መንግስተ ስማያት ያለ ምሪት ነው። በዚህ ጥቅስ ውስጥ እግዚአብሔር በሁለት መንገዶች ባርኮቱን እንደሚሰጥ ቃል ገብቶዋል፣ ያም በሰዎች ፊት ትክክል የሆነውንና በእርሱ ፊት ትክክል የሆነውን ማለት ነው።

(7). የሚከተሉት መልመጃዎች ከላይ በተመለከትናቸው ጥቅሶች ውስጥ የሚገኙትን እውነቶች እንድታጠቃልል ይረዱሃል። ያጠናኸውን ወደኋላ ተመልሰህ ባትመለከት በጎደለው ቦታ ሙላ። ከዚያም መልስህን እመሳክርና ለአንተ ግልፅ ያልሆኑትን ትምህርቶች ከልስ።

ሀ. ትዕቢትና የትምክህት ተቃራኒ የሆነ ባህሪና የገርነት ዋነኛ አካል የሆነው ባህሪ ይባላል።

ለ. የምትገዛ ሚስት የ እና መንፈስ ነፃት ያልዳነ ባሏን የማዳን እድል ሊኖራት ይችላል።

ሐ. የዋህነት ለመቀበል እስፈላጊ ነው፣ ምክንያቱም ገናና መሬትን ለዘር እንደሚያዘጋጅ ገርነት እለስልሶ ለመቀበል ያዘጋጃል።

መ. ገርነት ለመከላከል ያገለግላል።

ሠ. ክፉ የሚሰሩትን በማቅናት ገርነትና ሰውን ትእግስተ እንዲኖረውና ጉዳትን ያለምሬት እንዲቀበል ያደርገዋል።

ገርነት በምሳሌ

የገርነት ምሳሌዎች

ዓላማ 5 ገርነት ለክርስቶስ ውጤታማነትን የሚጨምርበርትን ሶስት መንገዶች ለመግለፅ።

በብሉይ ኪዳን ዘመንና በጥንታ ቤተክርስቲያ በነበሩ የእግዚአብሔር ሰዎች ሕይወት ውስጥ ስለታየ የገርነት ፍሬና ጥንስት ብዙ ምሳሌዎችን መጥቀስ እንችላለን። መጽሐፍ ቅዱስን በምታነብበት ጊዜ ራስህን በውስጡ ያሉት ሰዎች ገርነት እላቸውን ብለህ ትጠይቅ ይሆናል። የገርነት መንፈስ በሚያታይበትም ታሪክ ውስጥ ቢሆን ፍረው ቢኖር ናሮ ታሪኩ ምን ዓይነት አምንታዊ ውጤት ሊኖረው እንደሚችል ትመለከታለህ። እዚህ ጥቂት ምሳሌዎችን ብቻ እንመለከታለን።

አብርሃም - በሎጥና በእርሱ መካከል ስለተፈጠረው ግጭት አብርሃም ለሎጥ በተናገረው ውስጥ የየዋህነት ምሳሌ ታይታል።

> "አብርሃም ሎጥን አለው፣ እኛ ወንድማማች ነንና በእኔና በእንተ በእረኞቼና በእረኞችህ መካከል ጠብ እንዳይሆን እለምንሃለሁ። ምድር ሁሉ በፊትህ አይደለችምን? ከእኔ ትሰይ ብንድ እሰምንሃለሁ፣ አንተ ግራውን ብትወስድ እኔ ወደ ቀኝ እሄዳለሁ፤ አንተም ቀኙን ብትወስድ እኔ ወደ ግራ እሄዳለሁ" (ዘፍ 13፥8-9)።

በመጀመሪያ ሲታይ አብርሃም መሬት የሚያጣ ይመስላል። በታሪኩ መጨረሻ ግን ለሎጥ የትድሚያ ምርጫ የሰጠውን አብርሃምን እግዚአብሔር አበልፅጎታል። የአብርሃም ልጅ ይስሐቅ በጉድጓዱ ምክንያት የተነሳውን ፀብ ለማብረድ የእባቱን ምሳሌ ቲከትላሏል (ዘፍ 26፥20-26 ተመልከት) እርሱም በጌታ ተባርኪል (ቁ. 24)።

ሙሴ - ዘኁ 12፥3 እንዲህ ይላል፡ "ሙሴ በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ ትሁት ነበር።" የእርሱን ትህትና በተመለከተ ብዙ ምሳሌዎች አሉ። ዘፀ 15፥24-25 ህዝቡ በእርሱ ላይ እንዲት እንዳጉረመረሙና እሱም ወደ ጌታው እንደተመለከተ ይናገራል። በዘፀ 17፥3-4 ደግሞ ነገር የተደገመ ሲሆን እሱም ወደ ጌታው ተመለከተ። በሚቀጥለው ጊዜ ህዝቡ ሙሴ ላይ ሲጮሁበት እግዚአብሔር ሰለ ሙሴ ሆኖ እርንና ማርያምን ተናገራቸው። እዚህ እንደምንማረው እግዚአብሔር ለየዋሆችና ለትሁታን ይቆማል። በዘኁ 16 በሙሴ መሪነት ላይ አመፃ እንደተነሳ እናያለን። የእርሱም የዋህነት እንደታየና እግዚአብሔርም ስለእሱ እንደቆመለት እንመለከታለን።

ጳውሎስ - ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ሐዋርያው ጳውሎስ ብዙ ጊዜ ስለ የዋህ መንፈስ ጠቃሚነት ጽፏል። ይህ የመንፈስ ፍሬም

ዘወትር ጳውሎስ በስሩ ካሉት ሰዎች ጋር ባለው ግንኙነትና ለጌታው እና ለአዳኙ ፈቃድ ባለው መገዛት ይታያ ነበር። ከመለወጡ በፊት ቁጡና ፀበኛ፣ ክርስቶስን የሚከተሉትን ሰዎች ለማጥፋት የተነሳሳ ሰው ነበር። ነገር ግን ከተለወጠ በኋላ የወንጌልን የፍቅር መልእክትና ርህራሄ በገርነትና በትህትና እያስተማረ ኖረበት።

(8). 2ጢሞ 4፥16 አንብብ። በዚህ ክፍል ውስጥ የትኛው የገርነት ፍሬ ነው ለጳውሎስ ሕይወት ውስጥ የተንፀባረቀው?

(9). እዚህ በተሰጠው ምሳሌ መሰረት የገርነት ፍሬ በሕይወትህ ለማፍራት ለክርስቶስ የበለጠ ውጤታማ የምትሆንበትን ሶስት መንገዶች ግለፅ።

በተግባር መተርጎም

ዓላማ 6 ከተሰጡት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ከመንፈሳዊ ገርነት ጋር የተያያዙ መመርያዎችን ሰተግባር ለመተርጎም።

ገርነት ውጤታማ ለሆነ ለጌታ አገልግሎት አስፈላጊ ነው። እግዚአብሔር በዚህ በጠፈውና በሚሞት ዓለም ውስጥ እንድንወክለው መርጦናል። በእኛ ውስጥ ዓለም የሚያየው ነገር ወደ ክርስቶስ ሊሰበው ይችላል። ሁሉም የገርነት ገጽታዎች መታዘዝ ፣ የመማር መንፈስ፣ አሳዚነትና ቁጣን መቆጣጠር ለጠፉት በመመስከርም ሆነ ደካማውን ወንድም በማቅናት ወይም ደቀ መዝሙር በማድረግ የሚጠቅሙ አስፈላጊ የሆነ የክርስቲያናዊ ምስክርነትና የአገልግሎት ክፍል ናቸው።

ምስክርነትን ማካፈል -በ1ጴጥ 3፥15-16 ክርስቶስን ለሌሎች መመለክርን በተመለከተ ይህ መመርያ ተስጥቶናል።

"ጌታን እርሱም ክርስቶስን በልባችሁ ቀድሱት። በእናንተ ለላለ ተስፋ ምክንያት ለሚጠይቋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ፣ ነገር ግን በየዋህነትና በፍርሃት ይሁን። በክርስቶስ ያለውን መልካሙን ኑሮዋችሁን የሚሳደቡ ሰዎች ክፉን እንደምታደርጉ በሚያመጠበት ነገር እንዲያፍሩ በጎ ህሊና ይኑራችሁ።"

(10). ለዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ የመገዛትን ጠቃሜታ የሚያመለክተው የትኛው ቃል ነው?

(11). በምስክርነት ጊዜ የአሳዚነትን ጠቃሚነት የሚያመለክተው የትኛው ቃል ነው?

አስታውስ! የእግዚአብሔር መንግስት በግድ ወደልብ አይገባም፣ መቀበል ያስፈልጋል። ኢየሱስ መንግስቱን በዓለም ላይ አስገድዶ መመስረት ቢፈልግ ኖሮ ዘጌቴሰማኔ የተናገረውን ሊያደርግ ይችል ነበር። "ወይስ አባቴን እንድለምን እርሱም ከአስራ ሁለት ጭፍሮች የሚበዙ መላእክት እንዲሰድልኝ የማይቻል ይመስልሃልን?" የመንፈስ ፍሬ የሆነው ገርነት ለክርስቶስ ያለንን ምሥክርነት ውጤታማ የሚያደርግ ነው።

የማያስተውል ክርስቲያን የጠፋውን ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግስት እንዲደገፍ ሊያደርገው ይችላል። ከክርስቶስ የተገኘ ገርነት ከማሳየት ይልቅ የራሱን ሀሳብ በማስገደድ ለለሌሎች ላይ ይጭናል። በሌላ መልኩ ፍቅር ያለው፣ አስተዋይ ክርስቲያን በጠባዩ ብቻ እግዚአብሔርን የሚያውቁትን ሰዎች በእርሱ ላይ በሚናገሩት ክፋት ሊያሰፈራቸውና በገርነት ምስክርነቱ ወደ ክርስቶስ ሊሰባቸው ይችላል።

ለኢየሱስ ደቀ መዛሙርትን ማፍራት - ደኅንነት የእግዚአብሔር ብቻ ሰጦታ ሲሆን ደቀ መዝሙር ማድረግ ግን የቤተክርስቲያን ሰራ ነው። በዚህ የማስተማር አገልግሎት ውስጥ የመንፈስ ፍሬ የሆነው ገርነት ዋና ነገር ነው።

"ነገር ግን ጠቢን እንዲያጠላ አውቀህ ከሰነፎችና ከልተማሩ ምርመራ ራቅ፣ የጌታም ባርያ ለሰው ሁሉ ገር ለማስተማርም የሚበቃ ለትእግስትም የሚፀና ሊሆን እንጂ ሊጣላ አይገባውም። ይሻሞም ምናልባት እግዚአብሔር እውነትን ያውቁ ዘንድ ንስሀ ይሰጣቸዋልና" (2ጢሞ 2፥23-25)።

እንዳንድ ጊዜ ደቀ መዝሙር በምናደርግበት ሂደት ውስጥ አንድ ሰው ተነስቶ ሊቃወመን ይችላል። በሞኞች ክርክር ሳንወሰድና ቦታ ሳንሰጥ በምትኩ መንፈስ ቅዱስ የገርነትን ፍሬ በሕይወታችን እንዲያፈራ እየወለደን እውነትን በቸርነት እና በፅናት ማስተማር አለብን። ክርክር የሚያሳምነው ጭንቅላትን ብቻ ነው። የሞህነት ግን ከልብ ይደርሳል። በዓለም ውስጥ ገርነትንና እርማትን አጣምሮ መያዝ ያልተለመደና የማይገኝ ሲሆን በጌታ ቤተክርስቲያን ውስጥ ግን በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት እነዚህን ነገሮች በመላት ማድረግ ይቻላል።

(12). (ትክክለኛውን ምረጥ) ደቀ መዝሙር ከመንፈሳዊ ትምህርት ጥቅም የሚያገኘው ምን ሲያደርግ ነው?

ሀ. በሚማረው ትምህርት ባልተስማማ ጊዜ ወደም ጥያቄ ሲኖረው ከአስተማሪው ጋር ሲከራከር ነው።
ለ. ታዛዥ እና የመማር መንፈስ ሲኖረው ነው።
ሐ. አስተማሪውን ብዙ ጊዜ በገርነት እንዲያስተምር ሲያሳስበው ነው።

(13). ደቀ መዝሙር በምናደርግበት ጊዜ የመመህሩ ዋና ሃላፊነት ምንድን ነው?


ሀ. ጠንካራና እውነተኛ መመርያን ከየዋህነት ጋር አጣምሮ ሲይዝ።
ለ. የሚከፈለውን ዋጋ ከናሉ ቦታውን ሲጠብቅ።
ሐ. የሚናገረው ነገር ትክክለኛ መሆኑን ሲያረጋግጥ።

ደካማውን ወንድም ማቅናት - "ወንድሞች ሆይ ሰው በማናቸውም በደል ስንኳ ቢገኝ መንፈሳውያን የሆናችሁ እናንተ እንደዚህ ያለውን ሰው በየዋሃት መንፈስ አቅኑት" (ገላ 6፥1)። የተሳሳተውን ወንድም ለመርዳትና ለማቅናት የመንፈስ ፍሬ የሆነው ገራአተስ ያስፈልጋል።

ሰው በስህተት ሊወሰድ ሊታሪም ይገባዋል። ነገር ግን እርማቱ በገርነትና መንፈሳዊ በሆነ ሰው መደረግ አለበት።

(14). ሀጢአተኛውን ወንድም ለማቅናት የሚፈልግ መንፈሳዊ ሰው ውስጥ መገኘት ያለበት የትኛው አመለካከት ነው?

ሀ. እርሱ ያንን ኃጢአት የማያደርግ በመሆኑ እርካታ እየተሰማው ወንድሙን በኃይል በመገሰፅ ሀጢአተኝነቱ እንዲገባው ማድረግ።
ለ. ትልቅ ፍቅርና ርህራሄ ሊኖረውና ክኅጢአት የሚጠብቀን መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ማስተዋል ይኖርበታል።



"ከእኔ ጋር ይኖሩ ዘንድ ዓይኖቼ በምድር ምእመናን ላይ ናቸው። በቀና መንገድ የሚሄድ እርሱ ያገለግለኛል።"

መዝ 101፥6

የገርነት ሽልማቶች

ዓላማ 7 "ገሮች ምድርን ይወርሳሉ . . ." የሚለውን የጌታ የተስፋ ቃል ለማብራራት።

በመዝ 37፥11 "ገሮች ምድርን ይወርሳሉ። በብዙ ሰላም ደስ ይላቸዋል" ያላል። በዚህ ጥቅስ ውስጥ ሁለት የገርነት ሽልማቶች ተጠቅሰዋል። አንዱ ለወደፊት የሚሆን ሲሆን፣ ይህም በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ገርነትን ያገኙ ንጉሱ ሲመጣና የእግዚአብሔር መንግስት በሙላት ሲገለጥ የሚወርሱ ሲሆኑ ሌላው ሽልማት ደግሞ አሁን የሚገኝ ነው። ይህም በብዙ ሰላም ደስ መሰኘት ነው። እንዳንድ ጊዜ የዚህ አለም ሰዎች የሚፈልጉትን ነገር በብዙ ጥረት እና ትግል ያገኛሉ። ነገር ግን በእግዚአብሔር መንግስት ቅዱሳን በየዋህነታቸው በረከታቸውን ከጌታ ዘንድ በቀላሱ ይወርሳሉ። ኢየሱስ ይህንኑ በማቴ 5፥5 ላይ በተናገረው በተራራው ስብከቱ ላይ አረጋግጦታል።

(15). ማቴ 5፥5 አንብብ። "የዋሆች ብፁአን ናቸው ምድርን ይወርሳሉና" ሲል ኢየሱስ ምን ማለቱ ነው?

ሀ. የገርነት መንፈስ በውስጣችን ካለ ትልቅ ሰላም ሊሰጠን በሚችል በብዙ ምድራዊ በረከቶች እንባረካለን ማለት ነው።

ሐ. የገርነት ፍሬ ያላቸው ኢየሱስ በምድር ላይ መንግስቱን በሚወርስበት ጊዜ ከክርስቶስ ጋር አብረው ይሆናሉ።

በየእለቱ ኑሮአችን ለስዎች በምናሳያቸው የገርነት መንፈስ የምናገኘው ምላሽና እንደ ሽልማት የሚቆጠሩ ነገሮች አሉ። እስኪ በሕይወትህ ውስጥ የገርነት ፍሬ ለውጥ ያመጣበትን ጊዜ አስብ። መንፈስ ቅዱስ በሕይወትህ ውስጥ ይህን ፍሬ ስሙላት እንዲያፈራ ጠይቀው። ከዚያ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ታዛዥ፣ ለመማር ፈቃደኛ እና ቁጣህን ስተገቢ መንገድ መቆጣጠር የምትችልና ከሌሎች ጋር ባስህ ግንኙነት ቸርና አስተዋይ ትሆናለህ።

የመከራ ፈተና

አጭር መልስ - እያንዳንዱን ጥያቄ በአጭሩ መልስ።

1. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እነዚህ ምልክቶች ምንን እንደሚያመላክቱ ግለፅ።

ሀ. እርግብ _____
ለ. የመስዋዕቱ ስግ _____
ሐ. በግ
መ. እነዚህ ምልክቶች የሚወክሉት ባህርያቶች ምን ምንድናቸው?

2. የተገራ ፈረስ የትኛውን የገርነት ገፅታ ይወክላል?

3. ፕራኦተስ ስአረስቶትል አባባል ሁልጊዜ በትክክለኛ ጊዜ _____ ፣ነገር ግን ትክክለኛ ባልሆነ ጊዜ _____።

4. ትሁት መሆን የ_____ተቃራኒ ነው።

5. ደካማውን ወንድም በምንመልስበት ጊዜ ሁሉ እርማትን ከ_____ ጋር ማቀናጀት አስብን።

ምርጫ - ከእያንዳንዱ ጥያቄ በፊት ያለውን ትክክለኛ መልስ እክብብ።

6. ከእነዚህ ውስጥ የፕራኦተስን ትርጉም ጥሩ አድርጎ የሚወክለው የትኛው ነው?

ሀ. ገርነትና ትህትና
ለ. ገርነትና ደካማነት
ሐ. ጥንካሬና ሀይል
መ. ገርነትና ዕናት

7. ገርነት እንደ መንፈስ ፍሬ የመገዛትን፣ የመማርን መንፈስ እና _____ ገፅታዎችን ያካትታል።

ሀ. የአሳቢነት
ለ. የጨካኝነት
ሐ. የቁጣ
መ. የተገራ የመሆንን

8. የእግዚአብሔር በክፉት ላይ መቆጣት የምን ምሳሌ ሲሆን ይችላል?

ሀ. ሀያልኛ ቁጣ
ለ. ትክክልኛ ባልሆነ ጊዜ መቆጣት
ሐ. ትክክለኛ በሆነ ጊዜ መቆጣት
መ. ደካማነት

9. ስስ ኢየሱስ የተጠቀሱት ምሳሌዎች እርሱ በሃይል የተቋቋመው ምንን እንደሆነ ይገልጻሉ?

ሀ. በእባል ስንዳት የመጡትን ነው።
ስ. ማንኛውንም የእግዚአብሔርን ስምና ቤት የሚያረክስን ነገር ነው።
ሐ. ወደ እርሱ ስእርዳታ የሚመጡ ንጹኢተኞችን ነው።
መ. ስድብንና በግል ሕይወቱ ላይ የሚመጡ ክፋ ነገሮች ነው።

10. ልብን ስደህንነት የሚያዘጋጀው የገርነት መንፈስ ከምን ጋር ሊገናኝ ይችላል?

ሀ. እረኞቹን ከሚከተሉ በጎች።
ለ. ከሚገራ እንስሳ።
ሐ. ደረቅ መሬትን ስዘር የሚያዘጋጅ ገበሬ።
መ. ይቀ መሣሪርትን ከሚያርም መምህር።

11. የምትገዛ ሚስት የማያምን ባሏን ስጌታ ምን በማድረግ ልታድነው ትችላስች?

ሀ. ውቅያዊ ማንነቷን በማሳመር።
ለ. ድኅነት እንደሚያስፈልገው እስኪያምን ድረስ በማነጋገር።
ሐ. የቤተ ክርስቲያንን እገልግሎት በሕይወቷ ቀዳሚ ቦታ በመስጠት።
መ. የዋህና የረጋ መንፈስ በውስጧ በማኖር።

12. ሁለቱ የገርነት (የየዋህነት) ሽልማቶች ስላምና_____ናቸው።

ሀ. ብልጽግና
ሀ. የእግዚአብሔርን መንግስት መውረስ
ስ. በቤተክርስቲያን ያስ ታላቅ እገልግሎት
ሐ. በሰዎች መካከል የሚኖር ክብር

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስ

8. ትተውት ስተለዩት ሰዎች ይቅርታን ስመነላቸው።

1. ሀ. ሐስት ሐ. ሐሰት ሠ. እውነት ስ. ሐሰት
ለ. እውነት መ. እውነት ረ. እውነት

9. የአንተ መልስ። እንዲህ ብለህ መለስህ ይሆናል፣ አስታራቂ፣ ለራስ ሳይቆሙ ጌታ እንዲቆምልን መፍቀድ፣ ሌሎችን ወደ ወንጌል እውነት የሚመራ ጠንካራ የምስክርነት ሰው፣ ፍቅር ማሳየት፣ ስለሰው ሞድ መሰኘት፣ ስዎችን ሁሉ መታገስ፣ ወይም ሌሎች።

2. የአንተ መልሶች። እነዚህ የኔ መልሶች ናቸው።

ሀ. ለእግዚአብሔር ፈቃድ መግዛት ወይም የመማር መንፈስ።
ለ. እሳቢነት፣ ሌሎቹን ስለፍቅር መሸከም
ሐ. ብርታት፣ ጥንካሬ፣ ውሳኔ
መ. እርማት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ገርነትንና ዕናትን ማቀናጀት (በደል የተገኘበትን ሰው ለማቅናት በሚፈለግበት ጊዜ)።
10. በልብህ ውስጥ ክርስቶስን ቀድስ።

3. የእግዚአብሔር ቁጣ ሁልጊዜ በኃጢአትና በክፋት ሳይ ሲሆን የራሱ በሆኑትና በሚከተሉት ሳይ ግን ፍቅርና የዋህነትን ያሳያቸዋል።

11. ይህንን በገርነትና በማክበር እድርገው።

4. ለእባቱ ፈታድ ታዘዘ ሲያስሩት ለመጡት ወታደሮች ራሱን ሰጠ።

12. ለ

5. እንዱ ምሳሌ የደቀመዛሙርቱን እግር ማጠብ ቢሆን ይህም የአገል ጋይነት ምሳሌ ነው።

13. ሀ

6. የአንተ መልስ። የኔ መልስ ይኸው። እግዚአብሔር ለፈቃዱ ተገዥ እንድንሆን ይፈልጋል። የዋህነት እንደ መንፈስ ፍሬ ከጥንካሬ ጋር ይሞሃዳል፣ የወንጌል መልእክት በየዋህነት መመስከር አለበት።

14. ለ

7. ሀ. ትህትና
ለ. የዋህና፣ ዝግተኛ (ፀጥተኛ)
ሐ. ድኅነት፣ ልብን፣ የእግዚአብሔርን ቃል
መ. ኃጢአት
ሠ. የዋህነት

15. ለ

9 ራስን መግዛት
የዲሲፕሊን ፍሬ
ትምህርት

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ጥቅምት 8 ቀን በ1871 ዓ.ም. በአንድ ምሽት ወይዘሮ አሳሪ የምትባል ሴት ትንሽ ኩራዝ አብርታ ላሞቿን ለማለብ ወደ በረት ገባች። ላሟ ኩራዙን ስትረግጠው የሚበራው ኩራዝ ወደቆ እሳቱ በነፋስ እማካኝነት በፍጥነት ወደ ገለባዎቹ ተዛመተ። ከዚያም በረቱ ሁሉ በአንድ አፍታ ተቀጣጠለ፣ እሳቱ ከ24 ሰዓታት ለሚበልጡ ጊዜያት ያህል ቆየ። የታላቋን የቺካጎ ከተማ የንግድ ማእከላትና በ3 ተኩል ስኬር ማይልስ ቦታ ላይ የሚገኙትን 17,450 ህንፃዎችን አወደመ። ቢያንስ 300 ያህል ሰዎች ሲሞቱ 90,000 ሰዎች ያለመጠለያ ቀሩ፣ 200 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ ንብረትም ወደመ። ይህ ሁሉ የሆነው እንዲት ላም በረገጠችው ትንሽ ኩራዝ ነው።

እሳት አስፈላጊ ነው፣ እናም በቤታችንና በፋብሪካዎች በተገቢው ሁኔታ ከተጠቀምንበት ብዙ እገልግሎት ይሰጣል። ነገር ግን ከቁጥጥር ውጭ ከወጣ የነካውን ሁሉ የሚያጠፋ ክፉ ጠላት ነው። እንደ ትልቅ የኃይል ምንጭ ተገቢ የሆነ ቁጥጥር በእሳት አጠቃቀማችን ላይ አስፈላጊ ነው።

ለው በተገቢ ሁኔታ እንዲቆጣጠረውና እንዲጠቀምበት ሆኖ ከሙሉ አእምሮ፣ አካል ለሜትና መንፈስ ጋር የተፈጠረ ነው። ይህ ኃይል በመንፈስ ቀዱስ ቁጥጥር ስር ሲውል መቻሉ የሚያስደንቅ እይደለም። በዚህ ትምርት ውስጥ ዘጠነኛ የሆነውን የመንፈስ ፍሬ ራስን መግዛት እንመለከታለን። ይህም የመገራት ፍሬ ነው። ሰው በሕይወቱ መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን መምሰል እንዲያመጣ ሲፈቅድ በሁሉም የኑሮ አቅጣጫ ራስን መግዛት ያሳድጋል።

በክርስትና ሕይወትህ ውስጥ ብዙ መገራት ወይም ዲሲፕሊን ያስፈልግሃልን? ራስን የመግዛት ፍሬ ለዚህ መፍትሄ ነው። ራስን የመግዛት ፍሬ በመንፈስ ቁጥጥር ስር መሆን ስለሆነ የምታደርገውን ሁሉ ሙሉ በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ሥር ለማድረግ ራስህን ትሰጣለህ።

የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል
- ራስን የመግዛት ምንነት
- ራስን መግዛት ሲገለፅ
- ራስን መግዛት በመሳሌ

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

- መጽሐፍ ቅዱሳዊና ዓለማዊ የሆነውን የራስን መግዛት ፍቺ መግለፅ።
- በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ራስ መግዛት ለሕይወታችን እንዲያድግ ምን ማደረግ እንዳለብን መግለፅ።
- የልከኝነትን፣ ራስን የመካድንና የመታቀብን ፍቺዎች መስጠት።

- ራስን የመግዛትንና የልከኝነት መርሆዎችን የሚደግፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መለጠት።

የክፍለ ትምህርቱ መመርያዎች

1. ያለፉትን ትምህርቶች ስታጠና በነበረበት መልክ ይህንንም ትምህርት አጥና። በትምህርቱ ዋና ክፍል የተጠቀሱትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አንብብ። የማጥኛ ጥያቄዎችን ሁሉ መልስ በጥ እና የሚያታውቃቸውን ቁልፍ ቃላት ፍቺ እጠና።
2. ለዚህ ትምህርት ድጋፍ (መነሻ) የሆነውን ሮሜ 8ን አንብብ
3. የፈተና ሙክራውን እንብብና መልስህን አመሳክር።

የትምህርቱ ዝርዝር

ራስን የመግዛት ምሳሌነት

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ፍቺዎች

ዓላማ 1 መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሀሳብ የሆነውን ራስን የመግዛት ፍቺ ለመስጠት።

"የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትእግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ ገርነት፣ ራስን መግዛት ነው" (ገላ 5፥22-23)።

እማኞች ክድጎነት ቀጥሎ ራሳቸውን በመግዛት እንዲኖሩ የእግዚአ ብሔር እቅድ ነው። "ይህም ዐጋ ኃጢአተኝነትንና አስማቂ ምኞትን ክደን፣ የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንና የመድኃኒችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን፣ ራሳችንን በመግዛትና በዕድቅ፣ እግዚአብሔርንም በመምሰል በእሁኑ ዘመን እንድናር ያስተምረናል" (ቲቶ 2፥11-12)። የመንፈስ ፍሬ የሆነው ራስን መግዛት ለክፉ ፍላጎት ወይም ደስታ ራስን መካድ ነው። ራስን መግዛት በገላ 5፥21 ከተጠቀሱት ሁለቱ የሥጋ ስራዎች የስካራምነትና ዘፋኝነት ተቃራኒ ነው።

ኢንክራትያ ራስን መግዛት ተብሎ የተተረጎመው የግሪኩ የመጀመርያ ቃል ሲሆን በሶስት ቦታዎች ተጠቅሷል። እነሱም በገላ 5፥22፣ የሐዋ 24፥25 እና 2ጴጥ 1፥6 ናቸው። በገላ 5፥22 የተጠቀሰው ዘጠነኛ የሆነውን የመንፈስ ፍሬ ለመግለፅ ነው። በየሐዋ 24፥25 ጳውሎስ ቃሉን ከፍሊክስ ጋር ሲነጋገር ስለ ፅድቅ፣ ራስን ስለመግዛትና ሊመጣ ስላለው ፍርድ ስመግለጽ ተጠቅሞበታል። በ2ጴጥ 1፥5-6 ቃሉ በወጋ ዝርዝር ውስጥ ተጠቅሷል።

"በእምነታችሁ በጎነትን ጨምሩ፣ በበጎነትም እውቀትን፣ በእውቀትም ራስን መግዛትን . . .።"

የኢንክራትያ ዋና ሀሳብ ጥንካሬ፣ ሀይልና ራስን መግዛት ነው። ይህም ራስን የመግዛት ህግ ነው። ማድረግ ያለብን ነገር በመንፈስ ቅዱስ

ቁጥጥር ስር ራሳችንን ማስገዛት ነው። የመንፈስ ፍሬ የሆነው ራስን መግዛት ራስን መግራት ነው።

ራስን ከመግዛት ጋር የተያያዘው ግስ ኢንክራቲአማይ ሲሆን በ1ቆሮ 9፥25 ላይ ሽልማትን ለማግኘት ከሚደረግ የሯጮች ጥብቅ ልምምድን ለመግለፅ ተጠቅሷል። ጳውሎስ በውሁርቹ ውስጥ ብዙ ጊዜ የሯጭንና የወታደርን መመሳሰል ዕርዋል። ሁለቱም እይነት መስኮች ስፖርትና ውትድርና ልምምድን የሚጠይቁ ናቸው። ጳውሎስ የቆሮንቶስ ሰዎችን እንዲህ ሲል ያበረታታቸዋል። "እንዲሁም ታገኙ ዘንደ ሩጡ" (ቁ. 24) በመቀጠልም "ስለዚህ እኔ ያለአባብ እንደሚሮጥ ሁሉ እንዲሁ አልሮጥም፣ ነፋስን እንደሚነስም ሁሉ አልጋደልም፣ ነገር ግን ስሌሎች ክስበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ስጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛለሁ" ብሏል (ቁ.26-27)። ጳውሎስ በዚህ ቦታ የሚናገረው ራሱን በጅራፍ ማስቃየትን ሳይሆን ስውነቱን እግዚአብሔርን ደስ ከሚያሰኙ ነገሮች መግታቱንና መቆጣጠሩን ነው።

አለልጣኙ በሚያየው ወቅት ብቻ ልምምድን የሚያደርግ ሯጭ ሽልማቱን አያገኝም። የትራፊክ ፖሊስ ሲያይ ብቻ የትራፊክ ቀዩን መብራት የሚታዘዝ ሹፌር ራሱን መግዛት አልተለማመደም። እነዚህ የተጠቀሱት ሁሉ እውነተኛ ውስጣዊ ስውጥ ሳይኖር ትእዛዛን ለመፈፀም ብቻ የሚደረግ ውጭያዊ የማስመስል ተግባር የሚያሳዩ ናቸው።

ኢንክራቲአማይ የሚለው ግስ በ1ቆሮ 7፥9 ላይ ክርስቲያን ስጋዊ ፍላጎቱን በተመለከተ ከሚለማመደው ራስን መግዛት ጋር ይያያዛል። ባላገቡት እንዲህ ይላል፡ "ነገር ግን በምኞት ከመቃጠል መጋባት ይሻላልና ራሳቸውን መግዛት ባይችሉ ያግቡ።" ባለፈው ትምህርታችን እንደተመለከትነው ፕሬሉተስ (እርጋታ) ክቁጣ ራስን መግዛትን ያካትታል። ይህም ማለት በትክክለኛ ጊዜ መቆጣትና ትክክለኛ ባልሆነ ወቅት ግን ያለመቆጣት ነው። ኢንክራትያ በአብዛኛው የሚያመለክተው ክቁጣ ይልቅ የፍትወት ፍላጎትን መቆጣጠርን ነው። ይህም የስጋን ፍላጎትን መቆጣጠርንና በመብላትም ሆነ በመጠጣት ልክኛ መሆንን ነው። በሌላ አባባል ራስን መግዛት የራስን ፍላጎት በቁጥጥር ውስጥ ማስገባት ማለት ነው።

(1). መጽሐፍ ትዳሳዊውን ራስን መግዛት በተመለከተ የትኛው ፍቺ ጥሩ ገላጭ ነው?

ሀ. በስሜት መታጠል
ለ. ደስታ የሚሰጥን ነገር ለመብላት እንቢ ማለት
ሐ. በየእለቱ ልማድ ራስን መግዛት
መ. በክፉት ወይም የግል ጥቅም ላይ መሠልጠን
ሠ. ክጠንካራ ፍላጎት የተነሳ ራስን መቅጣት
ረ. ፈተናን ለመወጣት ሃይል
ሰ. በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ራስን መምራት

(2). ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ቆሮ 9፥25-27 ያስተማረው የክርስቶስ ተከታይ ምን መሆን እንዳለበት ነው?

ሀ. ራሳችንን በመቅጣት ደስታን ከሚሰጡ ልምምዶች መገታት።
ለ. ጥብቅ በሆነ ልምምድ ራሳችንን በመግዛት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት

ምድራዊ ፍቺ

ዓላማ 2 መንፈሳዊ ሰላልሆነ ሰው ጳውሎስ የሰጠውን ገለፃ የሚመስል ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የሆነ ፍቺን ለመለጠት።

ፕሳቶ ኢንክራትያን ራስን መግዛት ወይም ራስን ማሸነፍ ወይም በራስ ላይ መሠልጠን ብሎታል። ይህም ሰው በፍላጎቱና ደስታን በመውደድ ላይ ያለው የበላይነት ነው። መስመር የለቀቀና ገደብ የሌለው የምግብና የግብረ ሥጋ ፍላጎትና ልምምድ ተቃራኒ ነው ብሎታል። በጽንፈኝነት መልክ ከወሰድነው እትብለ፣ እትቅመስ፣ እትንካ ወደሚለው እክራሪነት ወይም ፍጹም ወደሆነ መታቀብ ይወስደናል ሲል አስጠንቅቋል። እንዲህ ዓይነቱ ሙሉ መታቀብ ከእዲስ ኪዳን ራስን መግዛት የተለየ ነው። ይህንን ሀሳብ በስለጠ በዚሁ ክፍል መጨረሻ ላይ እንመለከተዋለን።

እሪስቶትል ራሱን የሚገዛ ሰውን ሲገልፅ ጠንካራ ፍላጎት ያለው ነገር ግን በቁጥጥሩ ስር ማድረግ የሚችል ብሎታል። ራስን መግዛት የተሳነውን ሰው ሆን ብሎ ሳይሆን ፈተናን ለመቋቋም እቅም ከማጣት የተነሳ ስህተት እንደሚሰራ ስው ያያዋል።

በጥንታዊቷ ግሪክ ኢንክራትያ የሚለው ቃል እንድ ንጉሥ የሆነ ሰው ሕገቡን ሲያስተዳድርና ሲገዛ የግል ጥቅሙንና ፍላጎቱን ተፅእኖ እንዲያሳድር ካስመፍቀድ ባህሪ ጋር ተያይዞ ነው የተገለፀው።

(3). ሮሜ 7፥14-20ን እንብብ። ጳውሎስ መንፈሳዊ ሰላልሆነ ሰው የሰጠው መግለጫ ከተጠቀሱት ከየትኛው ጋር ይመሳሰላል?

ሀ. እነራሪነትን ያዘለ መታቀብ
ለ. በግል ፈላጎት የሚይመራ ገዥ
ሐ. ራሱን መግዛት ስለማይችለው ስው እሪስቶትል የሰጠው መግለጫ
መ. በምግብ እና በግብረ ሥጋ ፍላጎት መዘፈቅን እስመልክቶ ፕሳቶ የሰጠው ምሳሌ

ራስን የመግዛት ምስጢር

ዓላማ 3 በሮሜ 8፥5-9 መሰረት በክፉ ፍላጎት ላይ ራስን የመግዛትን ምስጢር ለመማር።

ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌ 5፥18 በወይን ጠጅ መስከርን እና በመንፈስ ቅዱስ መሞላትን ያነፃፅራል። "መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ

እትስከሩ ይህ መባከን ነውና።" ራስን ያለመግዛት ወደራስ ማተኮርና ኃጢአት የሆኑትን የስጋ ፍላጎት ወደ መፈጸም ይወስደናል። ትክክለኛው መድሀኒት በመንፈስ መሞላት ነው። በመንፈስ የተሞላ ሰው በመንፈስ ቁጥጥር ስር ስለሆነ ራሱን ለመግዛት በድካሙ ላይ እርዳታ ያገኛል። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህ እንዴት እንደሚሰራ ገልያታል።

> እንደ ስጋ ፈቃድ የሚኖሩ የስጋን ነገር ያስባሉና፣ እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን የመንፈስን ነገር ያስባሉ። ስለ ስጋ ማሰብ ሞት ነውና፣ ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ህይወትና ሰላም ነው። ስለ ስጋ ማሰብ ስእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና፣ ለእግዚአብሔር ህግ እየገዛምና፣ መገዛትም ተስኖታል፤ በስጋ ያሉትም እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙት አይችሉም። (ሮሜ 8፥5-9)

በጳውሎስ ገለፃ እና በዮሐ 3፥6 ባለው ቃል መካከል ያለውን መመሳሰል ታያለህን? ከስጋ የተወለደ ስጋ ነው፣ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው። ያለ መንፈስ ቅዱስ እርዳታ ተፈጥሮአዊ ፍላጎታችን ኃጢአት የሆኑትን ፍላጎቶቻችንን ለማሟላት የተሰጠ ነው። ነገር ግን ስመንፈስ በምንወለድበት ጊዜ በውስጣችን ያለው እዲሱ ፍጥረት፣ መንፈስ ስእኛ የሚፈለገውን እንድንፈልግ ያደርገናል። ስለዚህ ጊዜም እንኳን ሐዋርያው ጳውሎስ ትኩረት የሰጠው በየቀኑ በመንፈስ ስመሞላት የኃጢአትን ምኞት መግደልንና የመንፈስ ቅዱስን ፍላጎት መፈጸምን እንደሆነ እናያለን።

(4). ስራስህ እባባል በክፉ መሻት ላይ የበላይነትን ሚስጢር ማግኘት ምን እንደሆነ ግለፅ።

ራስን መግዛት ሲያስፈልግ

ሚዛናዊ ሕይወት

ዓላማ 4 ሚዛናዊ የሆነ ሕይወት ወይም ራስን የመግዛት ሕይወት ትክክለኛ መግለጫዎችን ለመለየት።

የሚዛናዊነት መመርያ በዩኒቨርስ ውስጥ ከተፈጥሮ ህግጋት እንዱ ነው። የእግዚአብሔር በተፈጥሮ ላይ ያለው ፍፁም የበላይነት በእዮብ መጽሐፍ ተጠቅሷል።

> ቁም፣ የእግዚአብሔርንም ተአምራት አስብ። በውኑ እግዚአብሔር እንዱት እንደሚያገዛቸው፣ የደመናውንም ብርሃን እንዱት እንደ ሚያዛቸው፣ የደመናውንም ብርሃን እንዱት እንደሚያበራ እውቀሃልን? (እዮ 37፥14-16)

ሚዛናዊነት በመጽሐፈ መክ 3፥1-8 ተጠቅሷል። በዘፈው "ለሁሉ ዘመን አለው ፣ ከሰማይ በታችም ለሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ አለው" ብሏል (ቁ. 1)።

የእግዚአብሔር ፍሳጎት ክርስቲያኖች ሚዛናዊ የሆነ ኑሮ እንዲኖሩ ነው። ይህም መንፈሳዊ፣ አካላዊ፣ አእምሮአዊ እና ስሜታዊ ሚዛንን ያካትታል። ለምሳሌ ሐዋርያው ጳውሎስ 1ቆሮ 12፣ 13 እና 14ን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በቤተክርስቲያን ውስጥ ከፍቅር ጋር የተስተካከለ ወይም ሚዛናዊ ልምምድ መሆን እንዳለበት ለማሳሰብ ነው የጻፈው። በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የመንፈስን ስጦታዎች ያለአግባብ የመጠቀም ልምምድ ነበር። በተሰሎንቄ ግን የበዛ ቁጥጥር ከመኖሩ የተነሳ ሚዛናዊነት ተጓድሎ ነበር። እነዚህ እማኞች የመንፈስን ስራ በተለይም የሚያንፀውን የትንቢት ስጦታ እያስቆሙና እየናቁ ነበር። (1ተስ 5፥19-20ን ተመልከት)። እነዚህ ሁለት ምሳሌዎች በሕይወታችን ሁሉ ሚዛናዊነት እንደሚያስፈልግ ያስገነዝቡናል።

እግዚአብሔር ለሰው የሰጠውን ህይል - ለምሳሌ ማስብ መቻል፣ ስሜት፣ ፈቃዳችንን መለማመድ የመሳሰሉት ከአግባብ ውጭ ሊውሉ ይችላሉ። ስለዚህም ነው የመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ራሳችንን ለመግዛትና እነዚህን ህይሎች በሚዛናዊነት ለመጠቀም የሚያስፈልገን።

ሚዛናዊ ሕይወት ራስን መግዛት እና ልከኛ መሆን ነው። የእነዚህ ቃላቶች ትርጉም መለመር የለቀቀ አገላለፅ ወይም ባህሪይን ማለወገድ ማለት ሲሆን በትክክለኛ መለመር ውስጥ መሆንን ያመለክታል። ቀደም ብለን እንደጠቀስነው ይህ ማለትም ከሁሉ መቆጠብ ለምሳሌ ለጋ ከመብላት ወይም ከጋብቻ ማለት አይደለም። በ1ጢሞ 4፥3-4 ሐዋርያው ጳውሎስ ጢሞቴዎስን የእስመሳይና ውሸታሞች ትምህርት የሆነውን አትቅመስ፣ አትንካ የሚል ትምህርት እንዳይሰማ ያስጠነቅቀዋል።

> መጋባትን ይከለክላሉ፣ እምነውም እውነትን የሚያውቁ ከምስጋና ጋር ይቀበሉ ዘንድ እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ መልካምን ነውና፣ ከምስጋና ጋር ቢቀበሉት የሚጣል ምንም የለም፣ በእግዚአብሔር ቃልና በፀሎት የተቀደሰ ነውና።

በእርግጥም ክርስቲያን ሙሉ ለሙሉ ሊያስወግዳቸው የሚገቡ ነገሮች አሉ። እነዚህም በትምህርት እንድ የጠቀስናቸው የሲጋ ፍሬዎች ናቸው (ገላ 5፥19-21፣ ሮሜ 1፥29-31፣ ሮሜ 3። 12-18 እና ማር 7፥22-23ን ተመልከት)። ነገር ግን እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ምሪት በእግዚአብሔር ቃል መሰረት በጨዋነት እንድንደሰት ብዙ መልካም ነገሮችን ፈጥሮልናል። እስኪ መጽሐፍ ቅዱስ በተወሰኑ የህይወት ዙርያዎች ምን እንደሚል እንመልከት።

1. *ሕንደበትን መቆጣጠር* - ራስን መግዛት እንደበታችንን በመቆጣጠር ይጀምራል። ያዕ 3፥1 እንዲህ ይነግረናል። "በቃል የማይስናከል ማንም ቢኖር እርሱ ስጋውን ሁሉ ደግሞ ሊገታ የሚችል ፍፁም ሰው ነው።" ያዕቆብ በመቆጠልም እንደበትን መቆጣጠር እስቸጋሪ ነገር እንደሆነ ይነግረናል።

(5). ያዕ 3፥2-12ን እንብብ። እንደበታችንን ስመቆጣጠር የመንፈስ ቅዱስ እርዳታ እንደሚያስፈልገን የሚያሳየን የትኛው ቃል ነው?

በሕይወቱ ራስን የመግዛት ፍሬን የሚሻ ሰው መንፈስ ቅዱስ እንደበቱን እንዲቆጣጠርለት በመፍቀድ መጀመር ይኖርበታል። መንፈስ ቅዱስ እንደበታችንን ከገዛ ሕይወታችንን በሙሉ ይገዛል። በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር የሆነ እንደበት እንደ እምሳክና ጌታን እመስግኖ እንደገና በእምሳሉ የተሰሩትን ሰዎች እይረግምም።

2. *የሲጋ ፍሳጎትን መቆጣጠር* - መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ጉዳይ ብዙ ይናገራል። የባልና ሚስት ግንኙነት የተቀደስ እና የተባረከ ነው። በ1ቆሮ 7 ሐዋርያው ጳውሎስ በጋብቻ ውስጥ ተገቢ የሆነ ቁጥጥር እንዲኖር ትምህርት ሰጥቷል። በመቀጠልም እንዲህ ብሎዋል። ያሳገቡ እና መበለቶች "ራሳቸውን መግዛት ባይችሉ ያግቡ በምኞት ከመቃጠል ማግባት ይሻላል።" መቆጣጠር የሚለው ቃል ኢንክራቶማይ ከሚለው ቃል የመጣ ሲሆን የመንፈስ ፍሬ ከሆነው ራስን መግዛት ጋር እንድ እይነት ግስ ነው የተጠቀመው። ሳያገቡ መቅረት የሚፈልጉ ሰዎች የመንፈስ ኢንክራቶማይ፣ በመንፈስ ቅዱስ ህይል የስጋ ፍላጎትን መግዛት ያስፈልጋቸዋል። የዚህ ቁጥጥር አስፈላጊነት በ1ተስ 4፥3-8 ግልፅ ተደርጎል። "ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም መቀደሳችሁ ነውና ከዝሙት እንድትርቁ፣ እግዚአብሔርን እንደማያውቁ አህዛብ በፍትወት ምኞት እይደለም እንጂ፣ ከእናንተ እያንዳንዱ የራሱን ዕቃ በቅድስናና በክብር ያገኝ ዘንድ እንዲያውቅ እስቀድመን ይግሞ እንደመሰከርንላችሁ፣ ጌታ ስለዚህ ነገር የሚበቀል ነውና ማንም በዚህ ነገር እይተላለፍ፣ ወንድሙን እያታልል። ስርኩስት ሳይሆን እግዚአብሔር በቅድስና ጠርቶናልና። እንግዲህ የሚጥል ሰውን የጣለ እይደለም መንፈስ ቅዱስን በእናንተ የሰጠውን እግዚአብሔርን ነው እንጂ"

(6). በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል መሰረት በስጋዊ ፍላጎት ራሱን መግዛት የነደለው ሰው ትልቁ እደጋ የሚሰራው ኃጢአት በማን ላይ በመሆኑ ነው?

ሀ. በእግዚአብሔር ላይ
ለ. በሰውነቱ ላይ
ሐ. በሌላ ሰው ላይ

3. *ልምዶቻችንን ልከኛ ማድረግ* - በ1ቆሮ 6፥12-20 ሐዋርያው ጳውሎስ በስጋችን ላይ ጌታን ማክበርን ትኩረት ሰጥቷል። በዚህ ክፍል ውስጥ ስለገዘሙት ብቻ ላይሆን ማንኛውም ስጋን የሚያረክስ እግዚአብሔርን እንደማያከብር ተናግሯል።

"ሁሉ ተፈቅዶልኛል፣ ሁሉ ግን አይጠቅምም። ሁሉ ተፈቅዶልኛል፣ በእኔ ላይ ግን አንድ ነገር እንኳ አትስለጥንብኝም። መብል ለሆደ ነው፣ ሆድም ለመብል ነው፣ እግዚአብሔር ግን ይህንንም ያንንም ያጠፋቸዋል" (ቁ. 12-13)።

(7). በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ውስጥ ራስን በሁሉም የሕይወት እቅጣጫ ስለመግዛት የሚናገረው የትኛው ቃል ነው?

ከመጠን በላይ መብላትና ሰካር መጽሐፍ ቅዱስ ያስጠነቀቃቸው ኃጢአታዊ ባህርያት ናቸው። "የመደን ጠጅ ከሚጠጡ ጋር አትቀመጥ ለሰጋም ከሚሳሱ ጋር ሰካርና ሆዳም ይደኸያሉና" (ምሳ 23:20-21)። እኛ ብዙ በመብላት ከመጠን በላይ የሰውነት ክብደት ይዘን እንዲት ሰካራሙን እንኮንናለን? ብዙዎቻችን በአመጋገባችን ላይ ራሳችንን መግዛትን እንድንማር የመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ያስፈልገናል።

4. *ጊዜን በአግባቡ መጠቀም* - ምናልባት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሰጋ ፍላጎትን ለለማስደሰት የተጠቀሰው ምሳሌ ለራሱ እንዲህ ያለው ሞኙ ሀብታም ነው። "እንቺ ነፍሴ ለብዙ ዘመን የሚቀር ብዙ በረከት አለሽ፣ ዕረፊ፣ ብዮ፣ ጠጪ፣ ደስ ይበልሽ እላታለሁ" (ሉቃ 12፥19)። ኢየሱስ ተግሳጹ ለለመጠበቅ በሰጠው ትምህርት ላይ የጊዜን በአግባቡ መጠቀም አስፈላጊነት ትኩረተ ሰጥቶታል (ሉቃ 12፥35-48)። ሚዛናዊ የሆነ ሕይወት ለሰራ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ለማንበብ፣ ለማረፍና ለመዝናናት ጊዜ አለው። ታታሪ ሰራተኛ ሆኖ ለቤተሰቡ ጊዜ የሚይሰጥ ሰው የጊዜ አጠቃቀምን አልተማረም። ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ሲል የመክረናል። "እንግዲያስ እንንቃ በመጠንም እንኑር እንጂ እንደ ሌሎች እናንቀላፋ። የሚያንቀላፉ በሌሊት ያንቀላፋሉና፣ የሚሰክሩም በሌሊት ይሰክራሉና፣ እኛ ግን ከቀን ሰለሆንን . . . በመጠን እንኑር" (1ተሰ 5፥6፣ 8)።

5. *አእምሮን መግዛት* - "ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት. ምኞቱንም እንዲፈጽም ለስጋ አታስቡ" (ሮሜ 13፥14)። "በቀረውስ ወንድሞቼ ሆይ፣ እውነተኛ የሆነውን ነገር ሁሉ፣ ጭምትነት ያለበትን ነገር ሁሉ፣ ዕድቅ የሆነውን ነገር ሁሉ፣ ንፁህ የሆነውን ነገር ሁሉ፣ ፍቅር ያለበትን ነገር ሁሉ፣ መልካም ወሬ ያለበትን ነገር ሁሉ፣ በጎነት ቢሆን ምስጋናም ቢሆን እነዚህን አስቡ" (ፊልጵ 4፥8)። እነዚህ ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አእምሮዋችንን እንዴት መግዛት እንዳሰብን ይነግሩናል። ክፉ እንዳናስብ ነገር ግን በጎ እንድናስብ ያስተምረናል። በእሁድ ዘመን በዓለም ላይ ጌታ የሰጠንን ኃላፊነት እንድንረሳ የሚያደርጉ እእምሮን የሚሰርቁ ብዙ ነገሮች አሉ። የምታነበው፣ በቴሌቭዥን የምታመ ለክተው፣ የምታዳምጠውና ራስህን የሰጠህለት ነገር ሁሉ እእምሮን በመግዛት ላይ ተፅእኖ አለው። ሀሳባችን እርሱን ደስ በሚያሰኝ ነገር ላይ እንዲሆን የመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ያስፈልገናል።

(8). ከእነዚህ ቃላቶች ውስጥ የትኞቹ ናቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን የራስን መግዛት ሃሳብ ሊያሳዩ የሚችሉት?

ሀ. መሰመር የለቀቀ ባህሪይ ወይም እናኋር
ለ. ልከኝነት
ሐ. ራስን ከሁሉ ነገር በማቀብ ደስታ መንፈግ
መ. ሚዛናዊነት
ሠ. መኮከለኝነት
ረ. የስጋ ፍላጎት

9. ከሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ሚዛናዊ ወይም ራስን ለለመግዛት የክርስትና ሕይወት የሚናገሩ ትክክለኛ ዐረፍተ ነገሮች የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ሚዛናዊ ሕይወት በጣም ብዙ ወይም ትንሽ ዝግጥር የሌለው ነው።
ለ. ራስን ደስታ መንፈግ ራስን ለመግዛት አስፈላጊ ነው ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ማንኛውንም አይነት ደስታ እንድናሰወግድ ስለሚያስተምረን።
ሐ. ክርስቲያን ራስን መግዛት ከፈለገ ከእንዳንድ ነገሮች ራሱን መቆጠብ አለበት።
መ. ራስን መግዛት አስፈላጊ የሆነበትን የሕይወት አቅጣጫ ስንመለከት ምላስን መቆጣጠር አነሰተኛ ሰፍራ ነው ያለው።
ሠ. ራስን የመግዛት አንዱ ሚስጢር በምንም ነገር ያለመረታት ነው።
ረ. በስጋዊ ፍላጎት ራሱን መግዛት ለማይቻል ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ የተሰጠው መፍትሄ ማግባት ነው።
ሸ. ማንኛውም ድርጊት ልከኝነት ካለው ይፈቀዳል።
ቀ. ወደ ኃጢአት የሚመሩ ነገሮች ለማሰብ እንቢ በማለት እእምሮአችንን መግዛት ይቻላል።
በ. ጊዜን በአግባቡ መጠቀም ማለት ለሰራ፣ ለእምልኮና ለመዝናናት የምናውለውን ጊዜ ሚዛናዊ ማድረግ ማለት ነው።
ተ. ከመጠን በላይ የሚበላ ሰው ከሰካራም የተሻለ ራሱን ይገዛል።

ቅዱስ ሕይወት

ዓላማ 5 መንፈስ ቅዱስ በአንተ ውስጥ ቅድስናን ፍሁም የሚያደር ግበትን ሂደት ለመግለጽ።

ከምንም ነገር በላይ እግዚአብሔር ቅዱስ እንድትሆን ይፈልጋል። ይህም ለመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ጊዜ ትኩረት ተሰጥቶታል።

> እኔ አምላክችሁ እሆን ዘንድ ከግብፅ ምድር ያወጣኋችሁ እግዚአብሔር ነኝ እንግዲህ እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተ ቅዱሳን ሁኑ (ዘሌ 11፥45)።

> የእስራኤል ጌታ አምላክ ይባረክ ጎብኝቶ ለህዝቡ ቤዛ አድርጎአልና፣ . . የመዳን ቀንድ አስነሰቶአል። . . በዘመናችን ሁሉ ያለ ፍርሀት በቅድናና በዕድቅ በፊቱ እንድናገለግለው ሰጠን (ሉቃ 1፥68-69፣ 74-75)።

> እንግዲህ፣ ወዳጆች ሆይ፣ የዚህ ተሰፋ ቃል ካለን፣ በእግዚአብሔር ፍርሃት ቅድስናን ፍሁም እያደረግን ሰጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ሁሉ ራሳችንን እናንፃ (2ቆሮ 7፥1)።

> ከሰው ሁሉ ጋር ሰላምን ተከታተሉ ቅዋደሱም ዘንድ ፈልጉ፣ ያለ እርሱ ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና (ዕብ 12፥14)።

መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን የሚሰራ ኃይል ሲሆን ቅድስናን በውስጣችን ፍሬም በማድረግ ክርስቶስን በሕይወታችን ህያው ያደርገዋል። ይህንንም የሚያደርገው በውስጣችን ራስን መግዛትን በማፍራት ነው። ጭለማና ብርሀን (ክፋትና ደግነት) ሲቀላቀሉ እንደማይችሉ ያሳየናል። ራሳችንን ከኃጢአተኛው ዓለም እንድንለይና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ኑሮ እንድንኖር መሻት በውስጣችን ይፈጥራል።

በዚህ ትምህርት ውስጥ ቀደም ሲል ለክርስቲያን ራስን መግዛት ማለት በመንፈስ ቁጥጥር ስር መሆን ማለት እንደሆነ ጠቅሰናል። ይህንን ነው ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 8፥8-10 የተናገረው። "በስጋ ያሉትም እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙ አይችሉም። እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፣ በመንፈስ እንጂ በስጋ አይደላችሁም። የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም። ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ቢሆን ሰውነታችሁ በኃጢአት ምክንያት የሞተ ነው። መንፈሳችሁ ግን በፅድቅ ምክንያት ህያው ነው።"

ስለዚህ የመንፈስ ፍሬ የሆነው ራስን መግዛት የስጋ ሰራ የሆነውን ኃጢአትን ይቃወማል። ከዳንክና በመንፈስ ቅዱስ ስር ከሆንክ ከስጋ ስራ ባርነት ነፃ ወተተሃል። ነገር ግን በምድር ባለህበት ጊዜ ሁሉ ሰጋዊ ፍላጎትህን መቆጣጠር መስማመድ ይኖርብሃል። ስጋ በእንተ ሳይ ለመሰልጠን የሚቻለውን ሁሉ ያደርጋል። ነገር ግን ራስህን ለመንፈስ ቅዱስ ባስገዛህ ጊዜ ሰጋ በእንተ ሳይ ስልጣን እንዳይኖረው ይጠብቅሃል። ይህ እንግዲህ ራስን መግዛትን ውጤታማ እንዲሆን ያደርገዋል።

ቅዱስ መሆን ማለት ክርስቶስን መምሰል ማለት ነው። በገላ 5፥22-23 የተጠቀሱትን የመንፈስ ፍሬዎች ራሳችንን ለመንፈስ ባስገዛን መጠን በውስጣችን የሚያድጉት የክርስቶስ ባህርያት ናቸው። ራስን የመግዛት ባህሪ ራሳችንን ክዓስም ለይተን ለእግዚአብሔር እንድናቀርብ የሚያስችለን ባህሪ ነው። ይህም ቅድስና በውስጣችን ፍፁም እንዲሆን የሚያስችል ሂደት ነው። ቅዱስ መሆን ማለት ራስን መግዛት ማለት ነው፣ ራስን መግዛት ማለት ደግሞ በመንፈስ ቁጥጥር ውስጥ መሆን ማለት ነው።

(10). መንፈስ ቅዱስ በሕይወትህ ውስጥ ቅድስናን ፍፁም የሚያደርግበትን ሂደት በአጭሩ ግለፅ።

ራስን መግዛት በምሳሌ

ዓላማ 6 ለየትኛው የሕይወትህ አቅጣጫ ራስህን ለመግዛት የመንፈስ ቅዱስ እርዳታ እንደሚያስፈልግህ ለመመርመር።

የኢየሱስ ምሳሌ

መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደእኛ እንደተፈተነ ይነግረናል (ዕብ 4፥15)። ይህም ፍፁም የሆነ ራስን የመግዛት ምሳሌ ነው እስኪ ሉቃስ ኢየሱስ በሰይጣን ሲፈተን የጻፈውን ዝርዝር እንመልከት። ይህንንም በሉቃ 4፥1-13 እናገኘዋለን።

1. ኢየሱስ በሚፈተንበት ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ነበር።

2. ሰይጣን በኢየሱስ ሕይወት ድካም ስማግኘት ፈለገ። ስእርባ ቀን እንደያመ ስላወቀ እንደሚርበው አወቀ። ሰለዚህም ፈተናውን የምግብን ነገር በማንሳት ቀረበ።

3. ኢየሱስ ራሱን ለምግብ ፍላጎት አሳልፎ ሳይሰጥ፣ የጠላቱን ፈተና ለመመከት ከቃሉ ጥቅሶችን ጠቀሰ።

4. ሰይጣንም ፈተናውን በቀጠለ ቁጥር ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቃል የሚለውን በመጥቀስ ሰይጣንን ያሳሰበው ነበር።

5. ሰይጣንም ፈተናውን በጨረሰ ጊዜ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ወደ ገሊላ ተመለሰ።

በዚህ ምሳሌ እንደምንገነዘበው ኢየሱስ ከሰይጣን የተሰነዘረበትን ፈተና ለመቋቋም የተደገፈው በገዛ ኃይሉ እልነበረም። ስመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ለመንፈስ ሀይል ነበር። ሀሳቡን በእግዚአብሔር ቃል ላይ በማድረግ እንምሮውን እንደተቆጣጠረ ልታይ ትችላለህ። ሰይጣን የተናገረው ነገር ሁሉ በእርሱ ላይ ተፅእኖ እልነበረውም። ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ራሱን ሙሉ ለሙሉ ገዝቷል።

የመሪነት መስፈርቶች

በእዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን መሪ ስመሆን የሚያስፈስገው እንዱ መስፈርት ራስን መግዛት እንደሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቅሷል።

1. 1ጢሞ 3፥1-2 - ኤጲስ ቆጶስ ልከኛና ራሱን የሚገዛ መሆን አስበት።

2. 1ጢሞ 3፥8 - ዲያቆናት ስብዙ የወይን ጠጅ የማይነመጁ መሆን አለባቸው።

3. 1ጢሞ 3፥11 - የዲያቆን ሚስትም ልከኛ ልትሆን ይገባል።

4. ቲቶ 1፥7-8 - ኤጲስ ቆጶስ እንደ እግዚአብሔር መጋቢ ራሱን የሚገዛ፣ ቅዱስና የማይነቀፍ ሊሆን ይገባዋል።

5. ቲቶ 2፥2፣6 - ሽማግሌች ልከኞች፣ ራሳቸውን የሚገዙ እንዲሆኑ፣ እንዲሁም ጎበዛዝት ልከኞችና ራሳቸውን የሚገዙ እንዲሆኑ እንዲበረታቱ ያስፈልጋል።

6. ቲቶ 2፥3-5 - እሮጊቶች ቆነጃጅቶችን ማስተማር እንዲችሉ ራሳቸውን መግዛት ይኖርባቸዋል።

(11). በኢየሱስ ምሳሌ ውስጥ ራስህን መግዛትና ስይጣንን መቃወም የሚያስችልህ ምን ዓይነት ትምህርቶች ታያለህ?

(12). ለመሪዎች ራሳቸውን መግዛት አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው?

(13). ይህንን ትምህርት ለማጠናቀቅ ራስህን መግዛት እንድትለማመድ የመንፈስ ቅዱስ እርዳታ የሚያስፈልግህን አቅጣጫ ለማወቅ ራስህን መርምር። ይህንንም ተግተህ በመፀለይ በየእለቱ ተለማመደው።

በእነዚህ ነገሮች ላይ ራሴን እገዛለሁ	ሁልጊዜ	እንዳንድ ጊዜ	ፈጽሞ	እልፎ አልፎ	የመንፈስ ቅዱስን እርዳታ እፈልጋለሁ
የመብላት ልማድ					
የአልኮል መጠጥ					
ጊዜዬን					
የስጋ ፍላጎት					
አእምሮዬ					
ክፉ መሻት					
መጥፎ ልምድ					
እንደበቴን					

የመከራ ፈተና

ምርጫ። ለእያንዳንዱ ጥያቄ አንድ ትክክለኛ የሆነ መልስ ምረጥ።

1. ራስን የመግዛት ሌላው ቃል

ሀ- ራስን መውደድ
ለ. ራስን ደስታ መንፈግ
ሐ. መታቀብ
መ. ራስን መግራት

2. ሁለቱ ክመስመር የወጡ የስጋ ፍላጎቶች

ሀ- መበላትና መጠጣት
ለ. መጠጣት እና ዘፋኝነት
ሐ. መካከለኝነትና ልከኝነት
መ. ጥሩ ሥልጠናና ሩጫ መሮጥ

3. ኤንክራትያ የሚያመለክተው ምንን መቆጣጠር ነው?

ሀ. የሥጋ ፍላጎትን
ለ. ቁጣ
ሐ. ሴሎች ስዎችን
መ. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን

4. ራስን በመጨቆን ደስታ መንፈግ የሚያመለክተው።

ሀ. ራስን መግዛትን ነው።
ለ. ብዙ ስጋ መብላትንና የወይን ጠጅን መጠጣትን ነው።
ሐ. ክስጋ፣ ክወይን ጠጅና ከጋብቻ መቆጠብን ነው።
መ. ሥነ ምግባር የጎደለው የግብረ ሥጋ ግንኙነት

5. መጽሐፍ ቅዱስ መሪዎች ልክኞች መሆን አለባቸው ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ነው?

ሀ. በሴሎች ላይ ስልጣናቸውን መጠቀም
ለ. ምንም ነገር ክልክ በላይ አለማድረግ
ሐ. ደስ ክሚያሰኝ ተግባር መቆጠብ
መ. ጊዜያቸውን ሁሉ ስስራቸው መስጠት

6. ራስን መግዛት የሚጀምረው ምንን በመቆጣጠር ነው?

ሀ. እንደስትን
ለ. የስጋ ፍላጎትን
ሐ. ጊዜን
መ. አእምሮን

7. ከእነዚህ ውስጥ ስመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ራስን የመግዛት ፍሬ እንዲኖርህ ለማድረግ የሚጠቅም ትክክለኛው መግለጫ የትኛው ነው?

ሀ. ሕይወትህን እንዲገዛ ራስህን ለመንፈስ ቅዱስ መስጠት እና ሕይወትህን በሚገባ ስመምራት ለእርሱ ድምፅ ንቁ መሆን።
ለ. ራስን መግዛት የሚያሳጣህን የስይጣንን ፈተና ለመቋቋም በራስህ አቅም እና ጉልበት መተማመን።

8. ጊዜያችንን ለስራ፣ ለእምልኮና ለመዝናናት በምናውልበት ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ማድረግ እንዳለብን ያስተምረናል?

ሀ. አብዛኛውን ጊዜያችንን ከእምልኮ ጋር በተያያዘ ሁኔታ እንድናውለው።
ለ. ስእያንዳንዱ ሚዛናዊ የሆነ ጊዜ እንድንሰጥ።
ሐ. በመጀመርያ ለስራ ከዚያም ለእምልኮ ትኩረት እንድንስጥና መዝና ናትን እንድናስወግድ።

እውነት - ሐሰት በል። ዐረፍተ ነገሩ እውነት ከሆነ 'እ' የሚለውን ፊደል ሐሰት ከሆነ ደግሞ 'ሐ' ብለህ በተስጠው ክፍት ቦታ ላይ ጻፍ።

_____9. ሰሮሜ 7 ጳውሎስ መንፈሳዊ ያልሆነን ስው ፈተናን ለመቃወም ፈቃደኛ ያልሆነ ስው ብሎታል።

_____10. ራስን የመግዛት ሚስጢር በመንፈስ መገዛት ነው።

_____11. የተስተካከለ ሕይወት ከመስመር በወጣ ባህሪይ ይታወቃል።

_____12. ልከኝነት የሚለው ቃል ከአልኮል መቆጠብን ያመለክታል።

_____13. ቅድስና ራስን ከመግዛት ውጭ አይቻልም።

_____14. ሰመጽሐፍ ቅዱስ አባባል ራስን የመግዛት ፍሬ የሚያስ ፈልጋቸው መሪዎች ብቻ ናቸው።

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስ

7 በእኔ ላይ ግን አንድ ነገር እንኳ እይሰሰጥንብኝም። (ቁ. 12)

1. ሐ፣ መ፣ ረ እና ስ

8. ለ፣ መ እና ሠ

2. ለ

9. ሀ. እውነት
መ. ሐሰት
ስ. ሐሰት
በ. ሐሰት
ሰ. ሐሰት
ሠ. እውነት
ሸ. እውነት
ሐ. እውነት
ረ. እውነት
ቀ. እውነት

3. ሐ

10. የእንተ መልስ እዚህ ከተጠቀሱት ውስጥ ሊመሳሰል ይገባል። ራሳችንን ከአሰም ሰይተን ስእግዚአብሔር ማቅረብ የምንችለው ራስን በመግዛት ፍሬ ነው። ይህንንም ስማድረግ ሕይወታችንን ለመንፈስ ቅዱስ በማስገዛት የክርስቶስን ባህሪ በውስጣችን እንዲፈጥር መፍቀድ ይኖርብናል።

4. የእንተ መልስ። ምስጢሩ ሕይወቴን እንዲመራ በመንፈስ ቅዱስ መመራት ነው አላለሁኝ። ከዚያም እርሱ ደስ የሚያሰኘውን ለማድረግ እፈልጋስሁ።

11. የእንተ መልስ። ይህ ምሳሌ የሚያሳየኝ ሁልጊዜ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንደሚያስፈልገኝና ጠላትን ለመቋቋም አእምሮዬን በእግዚ እብሔር ቃል ላይ ማድረግ ነው።

5. ማንም ስው እንደበተኑን ሊገራ አልቻለም (ቁ. 8)

12. መሪዎች ለሌሎች ምሳሌ ስሰሆኑ ራሳቸው ራስን መግዛት ካልተለማመዱ በስተቀር ሌሎቹን ሊያስተምሩ አይችሉም።

6. ሀ

13. የእንተ መልስ። አሰታውስ መንፈስ ቅዱስ ራስህን ለእርሱ እስካልስጠህ ድረስ በውስጥህ ራስን የመግዛት ፍሬ እንዲያፈራ አያስገድድህም።

10 ትምህርት

ፍሬ ማፍራት
ይህን የሚቃወም ሕግ የለም

በዚህ ክርስ መጀመሪያ ላይ ኢየሱስ ስለገበሬው ስለወይኑ፣ እንዲሁም ስለ ቅርንጫፎቹ የተናገረውን ምሳሌ እይተን ነበር። በዚህ ምሳሌ ውስጥ እግዚአብሔር አብ እንደ ገበሬ ሲሆን፣ ኢየሱስ የወይን ግንድ ነው፣ እኛ በእርሱ የምንኖር ደግሞ ቅርንጫፎች ነን። ቅርንጫፉ በግንዱ ላይ እስካለ ድረስ የሕይወት ምንጭ የሆነውን ነገር ከግንዱ ይወስዳል፣ ቅርንጫፉ እንዲያድግና ፍሬ እንዲያፈራ ይህንን የሕይወት ምንጭ ማግኘት አለበት። አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ገበሬው ብዙ ፍሬ ያፈራ ዘንድ ያጠራዋል። ከወይኑ ጋር ያልተጣበቀው ቅርንጫፍ ተቆርጦ ይቃጠላል።

የእግዚአብሔር እቅድ ለእኔና ለአንተ ፍሬ የምናፈራ ክርስቲያኖች እንድንሆን ነው። በሌላ አባባል ቅርንጫፍ የተጣበቀውን የወይን ግንድ እንደሚያንፀባርቅ ሁሉ እኛም በየእለቱ ኑሮዋችን የክርስቶስን ባህሪ እንድናንፀባርቅ ይፈለጋል። የእርሱ መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን እንዲኖርና በገላ 5:22-23 የተጠቀሱትን የመንፈስ ፍሬዎች እንዲያፈራ መንፈሱን በመስጠት ይህንን እንዲቻል ያደርጋል።

በዚህ ትምህርት ዘጠኝን የመንፈስ ፍሬ እየከለስን በብሉይ ኪዳን ህግና በክርስቲያን ነፃነት እንዲሁም በመንፈስ ፍሬ መካከል ያለውን ግንኙነት እንመለከታለን። ብዙ ነገሮችን የሚቃረኑ ህጎች ቢኖሩ ፍሬ ማፍራትን ወይም ክርስቶስን መምሰልን ግን የሚቃረን ህግ የለም። መንፈስ ቅዱስ በሕይወትህ ሲሰራ ጤናማ ቅርንጫፍ ፍሬ እንደሚያፈራ በሕይወትህ እንዲሁ ይሆናል።

የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- ህግና የክርስቲያን ነፃነት
- የመንፈስ ፍሬን እንከልስ

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህንን ትምህርት ስታጠናቅቅ እነዚህን ነገሮች ማድረግ መቻል ይኖርብሃል።

- ከህግና ከኃጢአት ባርነት ነፃ ለመውጣት በሰው ሕይወት ውስጥ ምን መካሄድ እንዳለበት መግለፅ።
- ክርስቲያናዊ ነፃነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ መግለፅ።
- የመንፈስ ቅዱስን ፍሬ ዘጠኝ ገጽታዎች መሠረታዊ ባህርያት ማጠቃለል መቻል።
- የክርስቶስ ባህሪ በሕይወትህ በሙላት እንዲኖር በመንፈስ ለመኖር መወሰን።

የክፍለ ትምህርቱ መመርያዎች

1. ለዚህ ትምህርት መንደርደርያ ይሆን ዘንድ ወደ ገላትያ ሰዎች የተፃፉትን ስድስቱን ምዕራፎች አንብብ።
2. በተለመደው መንገድ የትምህርቱን ዋና ክፍል አጥና። የተጠቀስትን ሁሉ መጽሐፎች አንብብ። እንዲሁም የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎችን መልስ። የትምህርቱ ዋና ትኩረት ክግል ሕይወት ጋር ማዛመድ ነው።
3. የሙከራ ፈተናውን ውሰድና መልስህን አመሳክር።
4. ክትምህርት 7 እስክ 10 ያለውን ክለስ።

የትምህርቱ ዝርዝር

ህግና የክርስቲያን ነፃነት

ከእስራት ነፃ መሆን

ዓላማ 1 ከእስራት ነፃ መውጣትን የሚገልፀውን ሀረግ ለመለየት።

የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትእግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ ገርነት፣ ራስን መግዛት፣ ነው። *እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ህግ የለም* (ገላ 5፥22-23)።

ህግ ለምን እንደተሰጠ አስበህ ታውቃለህን? ህጎች ባይኖሩ ኖሮ ህብረተሰቡ ምን ይሆን ነበር? ህጎች ባይኖሩ ኖሮ እያንዳንዱ እንደፈለገው ይሆን ነበር። የአንዱ ሰው ምርጫ ከሌላው ሰው ምርጫ ጋር እስካልተጋጨ ድረስ ይህ ችግር አይኖረውም። ነገር ግን እያንዳንዱ ዜጋ መፋለስን ወይም ግጭትን ለሚያመጣ ሁኔታ ውስጥ ሊኖር ይችል ነበር። አንዱ ተነስቶ መኪናውን በስተቀኝ ባለው በኩል ለመንዳት ቢወሰን ሌላው ደግሞ በስተግራ ለመንዳት ቢወሰንስ? እናም ሁለቱ አንዱ ወደሌላው ቢጠጋ ግጭት ሊፈጠር አይችልምን? ከዚያም የሚያስከትለውን መቻል ነበረባቸው።

ውሸትን፣ ስርቆትን፣ ግድያን፣ ትራፊክ መጣስ፣ ሌሎችን ማወክን፣ እንዲሁም በህብረተሰቡ ውስጥ የምናያቸው ሌላ ብዙ ክፉ ነገሮችን የሚቃረኑ ሕግጋት አሉን። ነገር ግን የመንፈስን ፍሬ የሚቃረኑ ህጎች የሉም! ይህም ከእስራት አርነት ለመውጣት ቁልፍ የሆነ ነገር ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች መልእክት የፃፈው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የህስት ትምህርት ስለነበረ ነው። አንድንድ ሰዎች ሰው ይህንኑቱን ካገኘ በኋላም ቢሆን የብሉይ ኪዳን ስርአትና ህጎች መከተል አለበት ብለው ያስተምሩ ነበር። ጳውሎስም ይህንን ትምህርት ማረም ፈልጎ ነበር። የገላትያ ሰዎች ደኅንነታቸው በክርስቶስ የማንዓት ስራ ላይ የተመሠረተና የእግዚአብሔር ነፃ የፀጋ ስጦታ እንደሆነ እንዲያውቁ ፈልጎ ነበር። ደህንነትን በስራ ሊያገኙትና እንዳንድ ነገሮችን በመስራት ሊጠብቁት አይችሉም።

የብሉይ ኪዳን ህግ ሰዎች ክፉ የሆነውን ነገር እንዳይሰሩ ሊከላከል አይችልም፣ ነገር ግን ክፉ ምን እንደሆነ ሲያስታውቃቸው ይችላል። ህጉን ለመታዘዝም ሆነ ላለመታዘዝ የእያንዳንዱ ህጉን የሚቀበል ሰው ሃላፊነት ነው። ሰው ህጉን ላለመታዘዙ ቢወሰን የሚያስከትለውን ጉዳትም መጠበቅ ይኖርበታል።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የእስራኤልን ህዝብ ታሪክ አንብበህ እንደሆነ እግዚአብሔር የመረጣቸው ህዝቦቹ ብዙ ጊዜ ህግን ካለመታዘዝ የተነሳ ብዙ መከራ እንደተቀበሉ ታውቃለህ። እግዚአብሔር ሰዎች በገዛ ጥረታቸው ህግን ሙሉ ለሙሉ ሊታዘዙ እንደማይችሉ ያውቅ ነበር። ስለዚህም ነው ለኃጢአታቸው ማስተሰርያ መሰዋእትን ያዘጋጀው። ነገር ግን ኢየሱስ ለአንዴና ለሁልጊዜ ለለእኛ መንፃት ራሱን ሲሰዋ ህግን ፈፅሞል። የብሉይ ኪዳን ህግ አሮጌ ኪዳን ሲሆን የክርስቶስ መሥዋዕትነት በእግዚአብሔርና ለሰው መካከል አዲስ ኪዳን እንዲኖረን ማድረግ አስችሏል። አዲሱ ኪዳን ለእግዚአብሔር ፀጋና ለኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ባለ እምነት አማካኝነት የኃጢአትን ይቅርታ እንዲገኝ አድርጎል። ይህም ነፃ ስጦታ ነው። ሰዎች በአሮጌው ህግ ሰር መሆናቸው ቀርቷል። በክርስቶስ አማካኝነት ከህግ ባርነት ነፃ ወጥተናል (ሔር 31፥31-34ን ተመልከት)።

ይህ ምን ማለት ነው? ሰዎች ከህግ ነፃ ስለወጡ እንደፈለጉ ሊኖሩ ይችላሉ ማለት ነውን? በእርግጥ አይደለም። ይህ ማለት የክርስቶስ መንፈስ ለሚኖርበት አዲሱ መንፈሳዊ ሰው በቁጥጥር ሥር ይሆናል። ይህ አዲስ ተፈጥሮ ግድ የሚለው ክፉ ወይም ራስን የመውደድ ፈላጎትን መፈጸም ሳይሆን እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት ነው የሚሻው። አዲሱ ተፈጥሮ እማኙን እግዚአብሔርን እንዲታዘዝና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ኑሮ ለመኖር ያስችለዋል።

ለገላትያ ሰዎች የተጻፈውን 6ቱንም ምዕራፎች ስታነብ በጹሑፉ ውስጥ የጳውሎስ ትኩረት የዳንነው በእምነት እንጂ በሕግ ስራ እንዳልሆነ መግለፅ ነው። በውስጣችን የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ላለን አዲሱ ሕይወት መመርያ ነው።

ኤፍ. ኤፍ. ብሩስ የተባሉት ሰው እንደተናገሩት "ከሕግ ነፃ መሆን ከስነምግባራዊ ግዴታችን ነፃ አያደርገንም። ይልቁንም የስነምግባር ግዴታችንን በህግ አስገዳጅነት ሳይሆን ነፃ በሆነው ለመንፈስ አሰራር የሚበረታታ ይሆናል" (1982፣ ገጽ 239-240)።

ይህንን እንዲህ ለማለት አናጠቃልለው።

1. በጌታ ኢየሱስ ላይ ባለ እምነት የዳነ ከብሉይ ኪዳን ህግ ሰታች አይደለም።
2. በደህንነት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ውስጥ ያድራል፣ አማኙ አዲስ ተፈጥሮ ያገኛል።
3. አማኝ ሕይወቱን ለመንፈስ ቅዱስ እስካስገዛ ድረስ የሚኖረው ክርስቲያናዊ ኑሮ ድልን የተቀዳጀ ነው።

4. የእማኙ ሳህሪ የሚወሰነው ራሱን ለመንፈስ ቅዱስ ባስገዛ መጠን ሲሆን እርሱም ከህግ እስራት ወይም ከእርጌው ተፈጥሮ እና መሻት እስራት ሰር እይደለም።

(1). በክርስቶስ ያለ አዲሱ ሕይወት መመርያ ምንድን ነው?

(2). ለሕግና ለክፉ መሻት እስራት ችግሮች መፍትሄው ምንድን ነው?

(3). ከሚከተሉት ውስጥ ከህግ እና ከኃጢአት ባርነት መላቀቅን የሚገለፀው እውነተኛ ሀረግ የትኛው ነው?

ሀ. በመንፈስ የሆነ ሕይወት
ለ. የፈለግኩትን የማድረግ ነፃነት
ሐ. ከግብረገባዊ ግዴታ ነፃ መሆን
መ. በክርስቶስ ላይ ባለ እምነት የሚገኝ ይህንነት
ሠ. የራስን ፍላጎት ማሟላት
ረ. በውስጤ መንፈስ ሲሰራ
ሰ. ሙሉ ለሙሉ ለህግ መገዛት
ሸ. የመንፈስን ፍሬ ማሳየት

የነፃነት ህግ

ዓላማ 2 ሁለቱን የነፃነት ህግ ገፅታዎች ለመጥቀስና ተግባራዊ እንዲሆኑ የሚያስችላቸው መንገድ ለመግለጽ።

ገላ 5 ጳውሎስ ስለህግና ነፃነት ያስተማረውን ያጠቃልላል (ሰቁ. 1) ጳውሎስ የገላትያ ሰዎች እንደገና በባርነት ቀንበር እንዳይያዙ ያስጠነቅቃቸዋል። የህግን ትእዛዝ መጠበቅና ስርአቶችን መፈፀምን ከቀንበር እስራት ጋር አነፃፅሮታል።

እንድ ሰው ወደኋላ ተመልሶ ህግን መጠበቅ ከጀመረ የተደንገጉትን ህጎች በሙሉ የመጠበቁ ግዴታ ይኖርበታል። ከህግ ውስጥ አንዱ ከፍል ቢጣስ ያው ሁሉም እንደተጣሰ ይቆጠራል። ነገር ግን ክርስቲያኖች በክርስቶስ ስማመን ከአዲሱ ኪዳን ሰር ስለሆንን ማንኛውም የሕግ ስርአቶችን ከመፈፀምና ከህግ ጋር ከተያያዙ ቀኖች ነፃ ነን። አዲሱ ኪዳን የተቻለው በክርስቶስ ደም ሲሆን ያም ለፅድቅ፣ ለሕይወትና ለነፃነት ነው። ወንጌል በገላ 6፥2 የክርስቶስ ህግ ተብሏል፤ ነገር ግን ይህ ህግ ኃጢአትን ሳይሆን እግዚአብሔርን የማገልገል የነፃነት ህግ ነው። ከመንፈሳዊ ነፃነታችን ጋር በተገቢ ሁኔታ የመኖር ኃላፊነት ስላለብን እንደሚገባ መኖር የምንችለው በውስጣችን ባለው መንፈስ ቅዱስ ነው።

የገላትያ ክርስቲያኖች በእንድ ጊዜ ህግንና ክርስቶስን ደስ ለማሰኘት ይሞክሩ ነበር። ያንን ነው ጳውሎስ በመልእክቱ የተናገረው። ወደ ሮሜ ሰዎች በፃፈው ሌላው መልእክቱ ይህንኑ ጉዳይ አንስቶ ነበር።

ስለዚህ ወንድሞቼ ሆይ፣ እናንተም በክርስቶስ ኢየሱስ ስጋ ለሕግ ሞታችኋል። ይህም ከሙታን ለተነሳው ለእርሱ፣ ለሌላው

ሆናችሁ ለእግዚአብሔር ፍሬ እንድናፈራ ነው። ኃጢአተኛ በሆነ ተፈጥሮ ቁጥጥር ሥር ሳሰን፣ ለሞት ፍሬ እንድናፈራ በሕግ የተቀሰቀሰው የኃጢአት መሻት በሥጋችን ላይ ይሰራ ነበር። አሁን ግን ቀድሞ ጠፍሮ እስሮን ለነበረው ሞተን፣ ከህግ ነጻ ወጥተናል፤ ይህም አርጌ በሆነው በተጻፈው ሕግ ሳይሆን፣ አዲስ በሆነው በመንፈስ መንገድ እንድናገለግል ነው። (ሮሜ 7፥4-6)።

ሰለዚህ ደረጃ በደረጃ ጳውሎስ የገላትያ ሰዎችን በመንፈስ ሰላለ ሕይወት ያሰተምራቸዋል። መጀመርያ መሰረታዊ እውነት ሰለሆነው በመንፈስ ሰሰመወለድ ጠቅሷል (4፥29)፤ ከዚያም በመንፈስ ሰለመኖር ይናገራል (5፥16)፤ በመጨረሻም የገላትያ ሰዎችን በመንፈስ እንዲኖሩ የመክራቸዋል (5፥25)።

የመልእክቱ ጣሪያ ጳውሎስ ዕገላ 5፥19-21 ሰሰጋና በመንፈስ ሰላለ ሕይወት ያነፃፀረው ነው። በትምህርት አንድ የሰራሃቸውን ሁለት ዝርዝሮች ፈልግና እንደገና አነጻጽራቸው። የጳውሎስ ትምህርት ሰውሰጣችን የሚያቋርጥ ጦርነት ትከከለኛ ሕይወት እንዳንኖር ያደርገናል የሚል አይደለም። ግልጽ አድርጎ የሚናገረው በሕግ የመመራትንና በራስ ጥረት ፍፁምነትን የማግኘትን ውጤት ነው። ጳውሎስ እንደሚናገረው የክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑት ሰጋን ከክፉ መሻቱና ምኞቱ ጋር ሰቀሉት። ሰለዚህም ሕይወታቸው የሚመራው ሰመንፈስ ቅዱስ ነው። የተወለዱት ከመንፈስ ነው፤ የሚኖሩትም በመንፈስ ነው። ይህ ነው የነፃነት ህግ።

(4). *የነፃነት ሕግ* ማለት ሰመንፈስ ቅዱስ ሀይል የእኛ_____የማገልገል ነፃነት _____ ግን ያሰማድረግ ነፃነት እሰን።

(5). የነፃነት ህግ እንዲቻል የሚያደርገውን ሂደት ግለፅ። _____

የመንፈስ ፍሬግ እንክልስ

ዓላማ 3 የመንፈስ ፍሬ በውስጥህ እንደሚታይ ሰመመርመርና በክርስትና ሕይወትህ ለማደግ የሚያሰፈልግህን ሰማወቅ።

ቀስ በቀስ ማደግ

ሜሪል ሲ. ቴኒይ በገላትያ ሰዎች መለእክት ላይ በዓፈው ማብራርያ እንዲህ ብሏል። የመልእክቱ ዋና ዓላማ የገላትያ ሰዎችን ፈተና እንዲያልፉ ማዘጋጀት ሳይሆን ለዘያው ሕይወት ማዘጋጀት ነው (1979፣ ገፅ 208)። ሰለዚህ በመንፈስ ፍሬዎች ላይ ሰለተዘጋጀው ሰለዚህ ኮርሰም ይዘንኑ ማለት እንችላለን። የኮርሱ ዋና ዓላማ በውስጥህ የመንፈስ ፍሬ በመሳት እንዲኖር ፍላጎት መፍጠር ነው። አስታውስ የመንፈስ ፍሬ *ሰአማኙ ውስጥ ቀስ በቀስ የሚያድግ የኢየሱስ ክርስቶስ ባህሪ ነው።*

ግባችን ኢየሱስን መምሰል ነው። ቢ.ኤስ . ሌዊስ እንደሚለው "ሞዴላችን ኢየሱስ ነው፤ የነልገታው ኢየሱስ ብቻ ሳይሆን ሰወላጆቹ

ቤት ያገሰገለው፣ በመንገድ የተጓዘው፣ በብዙ ህዝብ መካከል ያገሰገሰው፣ በጥያቄና በተቃውሞ የተዋከሰው፣ ጊዜ እሰኪያጣ ድረስ የተጣበበው ኢየሱስ ነው። ይህ ነው በሰው ሁኔታ ውስጥ የኖረውና የሰራው እምላካዊ ሕይወት" (1976፣ ንፅ 11)።

አንዳንድ ጊዜ በምሰባኩ ስር ተንበርክኩ ኢየሱስን ለመከተል ቃል መግባት በተግባር ከመተርጎም ይልቅ ይቀላል። በሰራ ቦታ የኢየሱስ ባህሪ ይታይብሃልን? በመንገድስ? ብዙ ህዝብ ባለበትስ ቦታ? ተገቢ ያልሆነ ጥያቄ በመጣብህ ጊዜስ የኢየሱስ ባህሪ ባንተ ይታያልን? ሰዎች በተቃወሙህስ ጊዜ? ፈተና በተጋዳደረህ ጊዜስ? ውሸንብርና ሁከት ባለበት ጊዜ ሁሉ የኢየሱስን ባህሪ ታሳያለህን? በማንኛውም ሁኔታ ኃያል የነሆነ ረዳት እንዳለህ በፍፁም እትርሳ። በመንፈስ ሰንመላለስ ኢየሱስ እንደኖረ እንድንኖር ያሰችለናል፣ እናም የኢየሱስ ወበት በውሰጣችን ይታያል።

መሪ ሀሳቦች

ለማጠቃለል ዘጠኙን የመንፈስ ፍሬ እንከልስና የዚህን ጥናት መመርያ የሆኑትን መሪ ሀሳቦች እንመልከት።

❶. *ፍቅር* - የመጀመርያው የመንፈስ ፍሬ እንዱ ገጽታ እጋቼ ፍቅር ነው። ይህም ራሰን መካድ፣ ጥልቅና ኢየሱስ በመስቀል ባሳየውና በእግዚአብሔር ፍቅር ይገሰፃል። በ1ቆሮ 13 የተገሰፀው ፍቅር ትእግስተኛ፣ ደግ፣ የራሱን የማይፈልግ ነው። አይቀናም፣ እይመካም፣ እይታበይም፣ የማይገባውን እያያርግም፣ በቀላሱ እይበሳጭም፣ ከእውነት ጋር ደስ ይሰዋል። ይህ ፍቅር በደልን አይቆጥርም፣ በክፉም ደስ እይሰውም። ለሌላ የመንፈስ ፍሬ እቅጣጫ የሰጠነው ፍቺ ምን ያህሱ ለፍቅርም ሲሰራ እንደሚችል ታያለህን? ይህ ሁሱም ባህርያት የሚመነጩበት የኢየሱስ ባህሪ ነው።

❷. *ደስታ* - ይህ ባህሪ መለኮታዊ ዐጋ ሲሆን ደስተኝነትን፣ እርጋታን፣ በመንፈስ ያሰን ከፍተኛ ሀሴት ያሰከትላል። ይህም በጌታ ላይ ያስ እምነት ውጤት በመሆኑ፣ ውጪያዊ የሕይወት ሁኔታ ተፅእኖ እያሳድርበትም። ይህ ደስታ የሚመጣው ከድኅነት ማስትም በእኛ ፋንታ የሚሰራውን የእግዚአብሔር ሀይል በማወቅና በቃሱና በፀሎት በሚኖረን እስት ተስት የሆነ የእግዚአብሔር ሀይል ነው። ለክርስቲያን በመከራና በደስታ መካከል የጠበቀ ግንኙነት እለው። የእግዚአብሔር ደስታ በእስቸጋሪ ጊዜ ጥንካሬን ይሰጣል።

❸. *ሰላም*- መንፈስ ቅዱስ የሚስጠው ደስታ ፍውም ዐጥታ፣ ዝግታ፣ እንድነት፣ ሰምምነት፣ ዋስትና፣ መተማመንና መሸሸጊያን ያካትታል። ይህም የመንፈሳዊ ድኅነት፣ ከእግዚአብሔር ጋር ትከክል መሆናችንን ማወቅ እና እግዚአብሔር ፍላጎታችንን እንደሚያሟላልን ያለን ዋስትና ነው። በድኅነት ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላምን እንሰማመዳሰን። የእግዚአብሔር ሰላም ቁጣን፣ በደልንና ጭንቀትን የሚተካ የውስጥ ሰላም ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ከሰዎች ሁሱ ጋር በሰላም እንድንኖር ሰላምን እንድንሻና እንድንከተል ያበረታታናል። ከሰዎች ጋር ሰላምን መመስረት እስታራቂ መሆንን ይጠይቃል።

4. *ትዕግስት* - ይህ የመንፈስ ፈሬ እቅጣጫ የሚናገረው በትእግስት መፅናትን ነው። ትእግስት በመከራ ጊዜ የማይፈርስና እጅ የማይሰጥ ትጋትና ጽናት ነው። ይህም በዘፀ 34፡8 የተገለፀውን በእግዚአብሔር ላይ ያለውን ርህራሄ፣ ለጋስነት፣ ለቁጣ መዘግየትን፣ ታማኝነትን፣ ለእኛ ያለውን ፍቅር አለመለወጥና ይቅር ባይነት ባህሪው ላይ ይታያል። ይህ ሁሉ ትእግስተኛ የሆነ ስው መግለጫ ነው።

5. *ቸርነት* . ቸርነትን ያለው ስው ከውስጥ ንፅህና የሚወጣ ለጋስነት፣ ርህራሄ፣ አሳቢነትና መልካምነት ይታይበታል። መልካም የሆነውን ሁሉ የመስራት ፈቃደኝነት አለው። ቸርነት ከበጎነት ጋር፣ ማስትም የውስጥ ቸርነትን ከማሳየት ጋር ይተሳሰራል።

6. *በጎነት* - ይህ የቸርነት፣ ማለትም መልካም የመስራትን ልምምድ ወይም መግለጫ ባህሪይ ነው። ይህም ሌሎችን ማገልገልንና ለጋስነትን ያካትታል። በጎነት ደግነትንና ጥንካሬን፣ እንዲሁም ወደንስህ የሚመራን ግላዊንና መገራትን ያካትታል።

7. *ታማኝነት* - ይህ በእምነት ስው ውስጥ የሚታይ መልካም ነገር ሲሆን ከመታመን፣ ነቀፋ የሌለው፣ ከስህተት የጎፃ፣ ከታዛዥነት፣ ከታማኝነትና ከቅንነት ጋር የተያያዘ ነው። ታማኝነት ኢየሱስ እንደሚያድነን ከማመንና ሙሉ ለሙሉ ራሳችንን እርሱን በማወቅና ለእርሱ በመሰጠት ላይ የተመበረተ ነው። ታማኝ ስው እውነተኛ ነው፣ ትክክለኛ የሆነውን ነገር ለመስራትና ቃሉን ለመጠበቅ የታመነ ነው። እንደባላደራ ለመኖርና የእግዚአብሔርን ስራ እንደፈቃዱ ለመስራት የታመነ ነው። ጊዜው፣ እውቀቱና ንብረቱ ሁሉ የጌታ እንደሆነ በማወቅ አጠቃቀማቸውን በማስተዋልና በጥንቃቄ ያደርጋል።

8. *ገርነት* - ሶስቱ የገርነት ዋና ሀሳቦች 1) ለእግዚአብሔር ፈቃድ ራስን ማስገዛት 2) የመማር መንፈስ 3) አሳቢ (አስተዋይ መሆን) ናቸው። ገርነት ቁጣን መቆጣጠርንና መቼ መቆጣት እንዳለብንና እንደሌለብን ማወቅን ያጠቃልላል። ክርስቶስ ከእግዚአብሔር በግ ጋር፣ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ከእርግብ ጋር እንዲሁም እማኞች ከበግ ጋር መመሳሰላቸውን በክርስቲያን ሕይወት ያለውን ገርነት ባህሪ ያሳያል።

9. *ራስን መግዛት* - የመጨረሻው የመንፈስ ፍሬ ራስን መግዛት ወይም በራስ ላይ የበላይ መሆን ማለት ነው። ይህም ጥብቅ በሆነ ስሽልማት በሚዘጋጅ እትሌት ተመስሏል። ራስን መግዛት፣ የፍትወት ምኞትን መቆጣጠርን፣ በእለት ተእለት ልማድ ልከኝነትንና የራስን ደስታ አለመፈለግን ያካትታል። ክርስቲያን የተበተካከለ ሕይወት እንዲኖር እንጂ ከመስመር እንዳይወጣ ይበረታታል። በእንደበታችን፣ በስጋችን ፍላጎት፣ በጊዜ አጠቃቀማችን፣ በእስተሳሰባችን፣ በመብላትም ሆነ በመጠጣት ራሳችንን ልንገዛና ልከኛ ልንሆን ይገባናል። በርግጥም ራሳችንን መግዛት የሚቻለው በውስጣችን ባለው አዲስ ተፈጥሮ ማለትም ራሳችንን ለመንፈስ ቅዱስ በማስገዛት የሚገኝ ነው። ቅድስና የተሞላው ኑሮ ለመኖር ራስን መግዛት አስፈላጊ ነው። ውጤቱም በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ውስጥ መሆንንና ስፈቃዳችን ራሳችንን ለመንፈስ ቅዱስ ማስገዛት ይሆናል።

(6). በስተግራ ያሉትን የመንፈስ ፍሬዎች በስተቀኝ በኩል ካሉት መግለጫዎቻቸው ጋር እዛምድ።

ሀ. የቸርነት ተግባር ወይም መገለጫ፣ ሌሎችን ማገልገልንና ለጋስነትን ያካትታል።
ለ. ራስን መስጠት፣ የመማርን መንፈስና አስተዋይነት (አሳቢነትን) ያካትታል።
ሐ. በሁኔታዎች ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔር ላይ ባስ እምነት የተመስረተ ታላቅ ደስታ።
መ. ጥብቅ የሆነ ልምምድ፣ ልከኝነት፣ ራስን መግዛትና ሚዛናዊነትን ያካትታል።
ሠ. ታላቅ ወጥታ፣ እንድነት፣ ስምምነትና ዋስትና።
ረ. ሁሉንም ባህርያት የሚያጠቃልል እና በኢየሱስ መስቀል ላይ መሞት ይገልጻል።
ሰ. የውስጥ ለስላሳነት ወይም ምቹነት ርህራሄና መልካምነት
ሸ. መታመን፣ ታማኝነት፣ ትህትናና ጥሩ ባላደራነት
ቀ. ፅናት፣ በትእግስት መቆየትና መረጋጋት

1. ፍቅር
2. ደስታ
3. ስላም
4. ትእግስት
5. ቸርነት
6. በጎነት
7. እምነት
8. ገርነት
9. ራስን መግዛት

(7). በማስታወሻ ደብተርህ በቃልህ እስክታጠናው ድረስ ገላትያ 5፡22-23 መፃፍ ተስማመድ። ከዚያም በቃልህ ለሌላ ስው ጥቀሱን ጥቀስ።

(6). ይህንን በማስታወሻ ደብተርህ የመንፈስ ፈሬዎች በሕይወትህ ይታዩ እንደሆነ በጥልቅ ራስህን ስመመርመር ጊዜ ውስድ። በዚህ ትምህርት ውስጥ የተማርካቸውን ስመተግበር የምትሰማመድባቸውን መንገዶች እስብ። በሕይወትህ የመንፈስን ፍሬ ለመግለፅ የሚያስፈልግህን በታዎች መርምር።

የመንፈስ ፍሬ			
ባህሪ	አጠር ያለ የባህሪ ገለፃ	ይህ ባህሪ በሕይወቴ መኖሩን ማረጋገጫ	ለማደግ ያለኝ ፍላጎት

ይህንን ቻርት ባጠናቀቅክ ጊዜ ይህንን የክርስቶስ ባህሪ በውስጥህ በሙላት እንዲያፈራ ራስህን በፀሎት እሳልፈህ ሰጥ። እስታውስ በፀጋ ባደግክ ጊዜና በውስጥህ ያለውን መንፈስ ቅዱስን በታዘዝክ ጊዜ የመንፈስ ፍሬ ቀስ በቀስ ማፍራት ክርስቶስን ወደ መምስል ማደግ ነው። ብዙ ጊዜ ልትወድቅ ትችላለህ። ነገር ግን ራስህን ያለማቋረጥ ለመንፈስ ቅዱስ ባስገዛህ ጊዜ ብዙ ፍሬ የምታፈራ ቅርንጫፍ እንድትሆን ይረዳሃል።

ትምህርቱን ሐዋርያው ጳውሎስ በሚለው እንደመድማለን።

> ነገር ግን እላለሁ፣ በመንፈስ ተመላለሱ . . . በመንፈስ ብንኖር በመንፈስ ደግሞ እንመላለስ . . . በመንፈስ ግን የሚዘራው ከመንፈስ የዘላለምን ህይወት ያጭዳል (ገላ 5፡16፣ 25፣ 6፡8)።

የመከራ ፈተና

እውነት ሐሰት - ዐረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ "እ" ሀሰት ከሆነ "ሐ" ብለህ በተሰጠው ክፍት ቦታ ፃፍ።

_____1. ስለመንፈስ ፍሬ ስንናገር የምንጠቅሰው ዘጠኝ አቅጣጫ ያለውን አንድ ፈረ ነው።

_____2. የመንፈስ ፍሬና የክርስቶስ ባህሪያት የሚሉት ቃላቶች አንድን ሀሳብ ይገልፃሉ።

_____3. የክርስቲያን ነፃነት ማለት ክርስቲያን የጌታን ትእዛዝ መቃወምና ደስ የሚያሰኘውን ማድረግ መቻል ማለት ነው።

_____4. ድኅነት ከክርስቶስ ስለምነት ከተገኘ ሰኋላ የሚጠበቀው ግን ጥሩ በመስራት ነው።

_____5. የብሉይ ኪዳን ሀግ ዓላማ ሰዎች እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙ እንዲችሉ ማድረግ ነው።

_____6. በክርስቶስ ላስን አዲሱ ሕይወት መመሪያ የሚሆነን በውስጣችን የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ ነው።

_____7. የመንፈስ ነፃነት ለሀግና ስኃጢአት መሸት እስራት መልስ ይሆናል።

_____8. አዲሱ ኪዳን እግዚአብሔርን የማገልገል ነፃነት እንጂ ኃጢአትን ማገልገል አይደለም።

_____9. ክርስቲያኖች አሁንም ቢሆን የብሉይ ኪዳን ስርአትና ሀግን እንዲያከብሩ ይጠበቅባቸዋል።

_____10. ሰው ራሱን ለመንፈስ ቅዱስ እስከበጠ ድረስ እግዚአብሔርን በሀግ ሳይሆን በፈቃድ እንደሚያገለግል ያሳያል።

_____11. የመንፈስ ፍሬ ቀስ በቀስ ስእማኙ ውስጥ የሚያድግ የክርስቶስ ባህሪ ነው።

_____12. የመንፈስ ፍሬ አማኙ ወዲያው እንደዳነና መንፈስ ቅዱስ በውስጡ መኖር ሲጀምር በሙላት በውስጡ ይገኛል።

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስ

5. በመንፈስ መወለድ፣ በመንፈስ መኖርና በመንፈስ መመላለስ

1. መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ይኖራል።

6. ሀ. 6 መ. 9 ስ. 5
ስ. 8 ሠ. 3 ሸ. 7
ሐ. 2 ረ. 1 ቀ. 4

2. በውስጣችን የሚኖር የመንፈስ ነፃነት

7. የእንተ መልስ።

3. ሀ፣ መ፣ ረ እና ሸ

8. የእንተ መልስ።

4. እግዚአብሔርን፣ ኃጢአት

የሙከራ ፈተና መልሶች

ክፍለ ትምህርት 1

1. ሐሰት
2. ሐሰት
3. ሐሰት
4. እውነት
5. እውነት
6. እውነት
7. እውነት
8. ሐሰት
9. እውነት
10. እውነት
11. እውነት
12. ሐሰት

13. ሀ. 2 ለ. 3 ሐ. 1

14. የክርስቲያን ባህርያት

15. ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት/ታማኝነት፣ ገርነት/ የውሃት፣ ራስን መግዛት

18. ብዙ ፍሬ በማፍራት

ክፍለ ትምህርት 2

1. ለ
2. ሀ
3. መ
4. መ
5. ለ
6. ሀ
7. መ
8. ለ
9. ሐ
10. ለ
11. ሀ
12. ሀ

ክፍለ ትምህርት 3

1. ሀ. 1
   ለ. 2
   ሐ. 2
   መ. 1
   ሠ. 2
   ረ. 2
   ሰ. 3
2. ሐሰት
3. እውነት
4. ሐሰት
5. እውነት
6. እውነት
7. ሐሰት
8. እውነት
9. እውነት
10. እውነት
11. ሐሰት
12. ሐሰት
13. እውነት
14. የእንተ መልሰ።

ክፍለ ትምህርት 4

1. ሀ፣ ሰ፣ ሠ፣ ረ፣ ሸ፣ ቀ እና በ
2. ሐ
3. ሰ
4. ሐ
5. ሀ
6. ሀ
7. ሐ
8. ለ
9. ሐ
10. ሀ

ክፍለ ትምህርት 5

1. ሀ፣ ለ፣ ሠ
2. ሐ
3. ሀ
4. ለ
5. ረ
6. ሐ
7. እውነት
8. እውነት
9. ሐሰት
10. ሐሰት
11. እውነት
12. እውነት
13. ሐሰት
14. ሐሰት
15. እውነት

ክፍለ ትምህርት 6

1. ከሚከተሉት የትኞቹም ይሆናሉ።
   የንጽህና ሕይወት፣ ልሰላሴ፣ ደግነት፣ ርኅራኄ፣ መልካምነት ወይም ጣፋጭነት፣ ትክክለኛ ወይም መልካም የሆነውን የማድረግ ፈቃደኝነት።

2. ቸርነትን፣ መልካምነትንና ደግነትን ማድረግ ወይም መለማመድ።

3. የፍቅር ባሪያ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ጌታውን ለማገልገል እንደሚመርጥ፣ እኛም ድኅነት ሰናገኝ የሕይወታችን ጌታ የሆነውን ኢየሱስን ለማገልገል መርጠናል። ቸርነትንና መልካም ነገርን ለሌሎች በማድረግ እናገለግለዋለን።

4. ሐ
5. ሀ
6. ሰ
7. ሐ
8. ሀ
9. ሐ
10. መ
11. ለ
12. ሐ

ክፍለ ትምህርት 7

1. ለ
2. ሐ
3. ሀ
4. ሐ
5. ለ
6. መ
7. መ
6. ለ
8. ሀ
10. ሐ
11. ለ
12. መ
13. ሐ
14. ለ

ክፍለ ትምህርት 8

1. ሀ. መንፈሰ ቅዱስ
   ለ. ኢየሱስ ክርስቶስ
   ሐ. የክርስቶስ ተከታዮች
   መ. ገርነት /የዋሃት

2. መገዛት
7. ሀ
11. መ

3. መቆጣት፣ አለመቆጣት
8. ሐ
12. መ

4. ትዕቢት ወይም ኩራት
9. ለ

5. ገርነት / የዋሃት
10. ሐ
6. መ

ክፍለ ትምህርት 9

1. መ
2. ለ
3. ሀ
4. ሐ
5. ለ
8. ሀ
7. ሀ
8. ለ
9. እውነት
10. እውነት
11. ሐሰት
12. ሐሰት
13. እውነት
14. ሐሰት

ክፍለ ትምህርት 10

1. እውነት
2. እውነት
3. ሐሰት
4. ሐሰት
5. ሐሰት
8. እውነት
7. እውነት
8. እውነት
9. ሐሰት
10. እውነት
11. እውነት
12. ሐሰት